# መጽሐፈ ሄኖክ



## "ወለመዋዕል አርአየኒ ዑርኤል መልአክ"

## ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የተቀበልነው የአንድምታ ትርጓሜ


<u>አሳታሚ፡-</u>

ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት

፳፻ወ፫ዓ.ም.



ብፁዕ ወቅዱስ ዶክተር አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፣
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት
ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት ፤

# መ ግ ለ ጫ

"ምርሐኒ እግዚኦ ፍኖተ እንተ ባቲ አሐውር" መዝ ፻፵፪.፰

የኢትዮጰጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተክርስቲያን እንደ መሆኗ ሁሉ በዓለም ከምትታወቅባቸው ዐበይት መገለጫዎች ውስጥ በዋቢነት የሚጠቀሱት ቢጥንታውያን ብሔራዊውን ሊቃውንት ሲወርድ ሲዋረድ ተጠብቀው ከቆዩት የብሉያት አንድምታ ትርጓሜ በዓለም እስከ አሁን የሌለው ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብቻ ተጠብቆ የቆየው መጽሐፈ ሄኖክ ነው።

በብሂለ አበው "ቅድመ ይዝክር ስሞ ለበዐለ መጽሐፍ" እንደተባለው የያሬድ ልጅ ሄኖክ ትውልዱ ከቀደሙት አባቶች ሲሆን የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ ከቁጥር ፲፬ -፲፮ እንደጻፈው ከአዳም ጀምሮ እስከ ራሱ ማለትም እስከ ሄኖክ ድረስ ሲቆጠር ሰባት ትውልድ ይሆናል።

ይኸውም :-

፩. አዳም
፪. ሴት
፫. ሄኖስ
፬. ቃይናን
፭. መላልኤል
፮. ያሬድ
፯. ሄኖክ ናቸው።

እርሱም ባለ ዘመኑ ሁሉ በፍጹም እምነት እግዚአብሔርን እያገለገለ ወንዶችንም ሴቶችንም ልጆች ወልዶ በምድር ላይ የኖረበት እድሜው ፫፻፷፭ ዓመት መሆኑ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፭ ቁጥር ፳፫

ሄኖክም አካሄዱን (በጎ ሥራውን) ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ ሞትን እንዳያይ እግዚአብሔር ስለወሰደው (ስለሰወረው) አልተገኘም።

እርሱም ስለ መላእክት አኗኗር፣ ስለጥፋት ውሀ ከጥፋት ውሃ በኋላ ስለሚኖረው ቀጣይ ዘመን፣ ስለ ፀሐይ፣ ስለ ጨረቃና ከዋክብት መመላለስ (ዑደት) ስለ መሲሕ (ክርስቶስ) ወደ ዓለም መምጣትና ከቅድስት ድንግል (ማርያም) መወለድ ፣ ዓለምን ስለማዳኑና ስለ ዕለተ ምጽዓት ፍርድ አሰጣጥ የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ ከቁጥር ፲፬ - ፲፮ በጻፈው መሠረት ተገልጾለት ተናግሯል።

ይህ ሆኖ ሳለ እንደሌለ ሆኖ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት የማይታወቅና የማይገኝ መጽሐፈ ሄኖክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያናችን ሊቃውንት ከጥንት ጀምሮ በጉባኤ ቤት ለደቀመዛሙርቶቻቸው ሲያስተምሩት እንደኖሩ ይታወቃል። አሁን ግን እግዚአብሔር የፈቀደው ጊዜ ደርሶ በሊቃውንት ታይቶና ተመርምሮ በማሳተሚያ ድርጅታችን አማካኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጅቶና ታትሞ ለትምህርትም ሆነ ለታሪክ እንዲጠበቅ ማድረጋችንን ስንገልጽ መንፈሳዊ ደስታ ይሰማናል።

"ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ"

አባ ጳውሎስ (ዶክተር) ቀዳማዊ ፣ ፓትርያርክ
ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
የዓለም አብያተ ክርስትያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንትና የዓለም
ሃይማኖቶች ምክር ቤት ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት፤



የቅኔና የመጻሕፍተ ብሉያት መምህር የነበሩት

መጋቤ ምስጢር ጌራወርቅ ጥበቡ

# መቅድም

ዘሄኖክ ፡ ነቢይ ፤
ሄኖክ ፡ ማለት ፡ ተሐድሶ ፡ ማለት ነው ፤ አዳም ፡ በምግብ ፡ ምክንያት ፡ ብልየትን ፡ እንዳመጣ ፤ ሄኖክም ፡ ከምግብ ፡ ተከልክሎ ፡ ተሐድሶን አምጥቷልና ፤ አንድም ፡ ዛሬ ፡ በብሉይ ፡ ሥጋ ፡ ጋነት ፡ እንደ ገባ ፡ እኛም ፡ ኋላ ፡ ተነሥተን ፡ በሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንገባለንና ፡ በሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ ተነሥተን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለመግባታችንም ፡ ምሳሌ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ አስቀ ድሞ ፡ በጎረ ፡ ገነት በምግባር ፤ በሃይማኖት ፤ ጸንቶ ፡ ኖረ ፤ መላእክት ፡ ፍጥረታትን ሁሉ ፡ አሳይተውት ፡ ፀሐይን ፡ ጨረ ቃን ፤ ከዋክብትንም ፤ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ጽፏል ፤ ይህንም ፡ ሄኖክን ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ ለመ ዝለፍ ፡ አስነሥቶታል ። እሊህ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡ ከሴት ፡ ርቀን ፤ ንጽሐ ፡ ጠብቀን ፡ እንኖራለን ፤ ብለው ፡ ተሳሉ ፤ ደቂቀ ፡ ቃየል ፡ የወገብ ፡ ድባ ፡ እያደረጉ ፡ ራቁታ ቸውን ፡ ሁነው ፡ ሲንጠላጠሉ ፡ አይተው ፡ ሂደው ፤ ተጋብተዋል ፤ አንድም ፡ ለጉዳያቸው ፡ ከወጡ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አለሌ ፤ እንደ ፡ ባዝራ ፡ ይንጠላጠሉ ፡ ጀመሩ ፤ ይህን ፡ አይተው ፡ በሐፀ ፡ ዝሙት ፡ ተነደፉ ፤ በዚህ ፡ ምክን ያት ፡ ተስነካክለዋል ፤ መነኮሴ ፡ ለመፍቅደ ፡ ደብር ፡ ወጥቶ ፡ በግብረ ፡ ዓለም ፡ ተስቦ ፡ እንዲ ቀር ፤ በአያቱ ፡ በቤተ ፡ መላልኤል ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፤ ሁለት ፡ ራእይ ፡ አይቷል ፤ ሰማይ ፡ ይትሀየድ ፡ ወይትነጻሕ ፡ ብሎ ፡ የማየ ፡ አይ ኅን ፡ ነገር ፡ ተናግሯል ፤ ወጽአ ፡ ላሕም ፡ ፀዐዳ ፡ ብሎ ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ የሚ ደረገውን ፡ ተናግሯል ፤ ይህንም ፡ ሄኖክን ፡ ዘውእቱ ፡ ሳብዕ ፡ እም አዳም ፡ ይለዋል ፤ አዳም ፤ ሴት ፤ ሄኖስ ፤ ቃይናን ፤ መላልኤል ፤ ያሬድ ፤ ሄኖክ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ተጽፎ ፡ ሲነበብ ፡ ሲተረጎም ፡ ከነቢያት ፡ እስከ ፡ ሐዋርያት ፡ ደረሰ ፤ ሐዋርያት ፡ መጻሕፍትን ፡ ለቀሌምንጦስ ፡ ሲሰጡ ፤ ሄኖክን ፡ በልባቸው ፡ ቈጥረው ፡ በአፋቸው ፡ ሳይቈጥሩት ፡ ቀርተዋል ፤ ስለ ምን ፡ ቢሉ ፤ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ጽርዓውያን ፡ አምነዋል ፤ ሄኖክ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጾለት

ግሥቶ[፭] : ብሏል ፤ ከዚህም : እንዲህ : አለ ፤ ከንጉሥ : እስከ: ኗደሬ፣ ከጳጳስ : እስከ : አጸዌ : ኖኀት : ማለት : የለምና ፤

ወይሑሩ : ወይትባረኩ ፤

ያበርሁ : ሲል :ነው ፤ ያበራሉ ፤ አንድም : በክብር : ይከናወናሉ፤

ወይበርህ : ሎሙ : ብርሃነ : አምላክ፤

የፀሐይ ፣ የጨረቃ : ብርሃን : አያበራላቸውም ፤ የእርሱ : ብርሃን ያበራላቸዋል : እንጂ ፤ አንድም ተወሕደውት ፣ (ተዋሕደውት) : ወርሰውት : ይነሣሉ ፤

፱ ፤ ወናሁ : መጽአ : በትእልፊት : ቅዱሳን : ከመ : ይግበር : ፍትሐ : ላዕሌሆሙ : ወያኀጕሎሙ : ለረሲዓን : ወይትዋቀስ : ኵሉ : ዘሥጋ ፤

በከፉዎቹ : ሊፈርድባቸው ፤ ለበጎዎቹ : ሊፈርድላቸው : ከብዙ : ቅዱሳን : መላእክት : ጋራ : መጣ፤ ምነው : መጽአ : አለ፡ ቢሉ : በምጽአት : እንዳለ : ሆኖ ፤ አንድም : ካልቀረ : ብሎ ፤ አንድም : ለማስፈራት: ይመጣል: ከማለት : መጣ: ማለት : ያስፈራልና ፤ አንድም : ይመጽእ : ሲል : ነው ፤ መላእክትን:አስከትሎ: ይመጣል፤

በእንተ : ኵሉ : ዘገብሩ : ወረሰዩ : ላዕሌሁ : ኀጥአን : ወረሲዓን ፤

ገብሩ : ኃጥአን ፤ ረሰዩ : ረሲዓን፤ ሲል : ነው ፤ ኃጥአን : ስለ ሠሩት ፣ ረሲዓን : ስላደረጉት ፣

ሥጋዊውን : ደማዊውን ፣ ሁሉ: ይወቅሳል ፤

፲ ፤ ጠየቁ : ኵሎ : ዘውስተ : ሰማይ : ግብረ : እፎ : ኢይመይጡ : ፍናዊሆሙ : ብርሃናት : ዘውስተ : ሰማይ : ከመ : ኵሉ : ይሠርቅ : ወየዐርብ ፤

በሰማይ : ያሉ : ፀሐይ ፣ ጨረቃ ፣ ከዋክብት : ሥራቸውን : እንዳይለውጡ ፣ አወቅሁ : ተረዳሁ ፤

ሥሩዕ:ኵሉ :በበዘመኑ፤ ወኢይትዐደዉ እምትእዛዞሙ ፤

የዘጠና : አንድ : መጋቢ ፣ የወር : መጋቢ፣ የሺሕ : አለቃ : አለና: ሁሉ : በየዘመኑ : የተሠራ : የተወሰነ : ነው ፤ ከትእዛዛቸውም : አይተላለፉም ፤

፲፩ ፤ ወርእይዋ : ለምድር ፤

የሰማይን : ጨርሶ : ለምድር : አመጣ ፤ ምድርን : እዩዋት ፤

ወለብዉ : እምግብር : ዘይትገበር : ላዕሌሃ ፤

በላይዋ : ከሚሠራው : የተነሣ፤ አንድም : የሚሠራውን: አብነት : አድርጋችሁ : ልብ : አድርጉ ፤

እምቀዳሚ : እስከ : ተፍጻሜቱ : ከመ : ኢይትመየጥ : ኵሉ : ግብሩ : ለአምላክ : ዘያስተርኢ፤

በቀዳሚ : ካለው : ጀምሮ : ወኵሎ: ፈጺሞ : እስካለው : ድረስ : ልብ : አድርጉ ፤

እንዘ : ያስተርኢ ፤

፭ ፤ ፩ ቆሮ. ፲፭ ፥ ፵፩

፲፭ ፤ ወአንትሙሰ ፡ ተንሥሡ ፡ ምጽላለ ፤ ወጽላሎተ ፡ በእንተ ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፤
እናንተ ፡ ግን ፡ ዋዕየ ፡ ፀሐይ ፡ ስለጠና ፡ የጎጆ ፤ የዛፍ ፡ ጥላ ፡ ትፈልጋላችሁ ፤ አንድም ፡ ምጽ ላለ ፡ የድንኳን ፤ ወጽላሎተ ፤ የቤት ፡ ጥላ ፤ ትፈልጋላችሁ ፤
ወምድርኒ ፡ ትውዒ ፡ እሙቀተ ፡ ሐሩር ፤
ምድርም ፡ ከሐሩር ፡ ትኩሣት የተነሣ ፡ ትቃጠላለች ፤
፲፮ ፤ ወአንትሙሰ ፡ ኢትክሉ ፡ ከይ ዶታ ፡ ለምድር ፤ ወኢኰኵሓ ፡ በእንተ ፡ ዋዕያ ፤
እናንተ ፡ ግን ፡ ስለዋዕይዋ ፡ ምድ ርንና ድንጋይን ፡ መርገጥ ፡ አትች ሉም ፤ አንድም ፡ ዝርዝር ፡ ያደ ረጉ ፡ እንደሆነ ፡ የምድርን ፡ ዐለ ቷን ፡ መርገጥ ፡ አይቻላችሁም ፤
፲፯ ፤ ጠየቁ ፡ እፎ ፡ ዕፀው ፡ በሐ መልማለ ፡ አቍጽል ፡ ይትከደኑ ፡ ወይፈርዩ ፤
እንጨቶች ፡ ሁሉ ፡ በቅጠል ፡ ልም ላሜ ፡ እንዲሸፈኑ ፤ ኋላም ፡ እንዲ ያፈሩ ፡ አወቅኹ ፤
፲፰ ፤ ወለብዉ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ወአእምሩ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ ለክሙ ፡ ለእ ሎንቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ዘሕያው ፡ ለዓለም ፤
እሎንተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ለዘለዓለሙ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ የሚኖር ፡ እርሱ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ፈጠረላ ችሁ ፤ የእነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ፈጽማችሁ ፡ እወቁ ፤
፲፱ ፤ ወምግባሩ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለለዓመት ፡ ዘይከውን ፤
በየጊዜው ፡ የሚደረገው ፡ ሥራው ፡ በፊቱ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤
ወኵሉ ፡ ምግባሩ ፡ ይትቀነዩ ሎቱ ፤ ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱ ፡ ይገዛሉ ፤
ወኢይትመየጡ ፤
ሥራቸውን ፡ አይለውጡም ፤
አላ ፡ በከመ ፡ ሠርዐ ፡ እምላክ ፡ ከመዝ ፡ ይትገበር ፡ ኵሉ ፤
ነገር ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ እንደሠ ራው ፡ ሁሉ ፤ እንዲህ ፡ ሲደረግ ፡ ይኖራል ፤
፳ ፤ ወርእዩ ፡ እፎ ፡ አብሕርት ፡ ወአፍላግ ፡ ኅቡረ ፡ ይፌጽሙ ፡ ኵሎ ፡ ግብሮሙ ፤
ባሕሮችና ፡ ፈሳሾች ፡ ሥራቸውን ፡ እንዳይለውጡ ፤ በክረምት ፡ እን ዲመሉ ፤ በበጋ ፡ እንዲጐድሉ ፤ አንድም ፡ አፍላግ ፡ በአብሕርት ፡ ላይ ፡ እንዲሄዱ ፤ ዓባይ ፡ በጣና ፡ ላይ ፡ እንዲሄድ ፤ አንድም ፡ ውቅ ያኖስ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ አፍላግ ፡ ስለተቀበለ ፡ አብሕርት ፡ ብሎታል ፤ ውቅያኖስ ፡ እንዲቀበል ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አፍላግ ፡ ወደእርሱ ፡ እን ዲሄዱ ፤ ግብራቸውን ፡ እንዳይለ ውጡ ፡ እዩ ፤ ወርኢኩ ፡ አፉሆሙ ፡ ለአፍላግ ፡ ወአፉሃ ፡ ለቀላይ ፡ ብሎ ፡ እንዲያመጣው ፤

ሦስተኛው አኪቢኤል ፤
ጣሚኤል ፤
አራተኛው ፡ ጣሚኤል ፤
ራሙኤል ፤
አምስተኛው ፡ ራሙኤል ፤
ዳንኤል ፤
ስድስተኛው ፡ ዳንኤል ፤
ኤዜቃኤል ፤
ሰባተኛው ፡ ኤዜቃኤል ፤
ሱሩቃያል ፤
ስምንተኛው ፡ ሱሩቃያል ፤
አስኤል ፤
ዘጠነኛው ፡ አስኤል ፤
አርሞርስ ፤
አሥረኛው ፡ አርሞርስ ፤
በጥርኤል ፤
አሥራ ፡ አንደኛው ፡ በጥርኤል
አናንኤል ፤
አሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ አናንኤል
ዘቂቢ ፤
አሥራ፡ ሦስተኛው፡ ዘቂቢ ፤
ሳምሳፒኤል፤
አሥራ ፡ አራተኛው ፡ ሳምሳ ፒኤል፤
ሰርትኤል ፤
አሥራ፡አምስተኛው፡ሰርትኤል ፤
ጡርኤል ፤
አሥራ፡ስድስተኛው፡ጡርኤል ፤
ዮምያኤል ፤
አሥራ፡ሰባተኛው፡ዮምያኤል ፤
አራዝያል ፤
አሥራ፡ስምንተኛው፡አራዝያል፡ ነው ፤

እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ሐበይቶሙ ፡ ለ፪ቱ፡ ፻ት ፡ መላእክት ፤
የሁለቱ ፡ መቶ ፡ አለቆች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤
ወባዕዳንሂ ፡ ኵሉ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ሌሎችም ፤ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ ፤
ከዚህ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ቈጠረ ፤
ሦስቱን ፡ ኋላ ፡ ያመጣቸዋል ፤
አንድም ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ፪ቱ ፡ ፻ት ፡ መላእክት ፡ ሐበይቶሙ ፤
አለቆች ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤ ሁለት ፡ መቶ ፡ ናቸው ፡ ወባዕዳን ፤ በየጊዜው ፡ የሚነሱ ፡ ናቸው ፤
፱ ፤ ወነሥኡ ፡ ሎሙ ፡ አንስትያ ፡
ከእነርሱም ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፤
ወኀረየ ፡ ኵሉ ፡ ለለርእሱ አሐተ ፡ አሐተ ፤
ሁሉም ፡ ለየራሱ አንዳንዲቱን መረጠ ፤
፲ ፤ ወወጠኑ ፡ ይባኡ ፡ ኀቤሆን ፡ ወተደመሩ ፡ ምስሌሆን ፤
ወደነእርሱም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፤ ከእነርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፤ በግብር ፡ አወቁአቸው ፤
፲፩ ፤ ወመሀርዎን ፡ ሥራያተ ፤
ሥር ፡ መማስን ፡ ቅጠል ፡ መበጠስን ፤
ወስብዐታተ ፤
ጋኔን ፡ መሳብን ፡ አስተማሩአቸው ፤
ወመቲረ ፡ ሥርው ፤

ወበቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ይትዐጸዉ ፡
ለዓለመ ፡ ዓለም ፤
በግዞት ፡ ቤትም ፡ ለዘለዓለሙ ፡
ተዘግቶባቸው ፡ ይኖራሉ ፤
፲፯ ፤ ወሶቤሃ ፡ ይውዒ ፡ ወይማስን ፡
እምይእዜ ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፤
እምይእዜ ፡ ከምጽዓት ፡ ጀምሮ ፡
ያንጊዜ ፡ ይቃጠላል ፡ ይጠፋል ፤
ምስሌሆሙ ፡ ኀቡረ ፡ ወይትዐሠሩ ፡
እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ትውልደ ፡ ትውልድ ፤
ከአጋንንት ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ እስከ ፡
ልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡
ድረስ ፡ ይጋዛሉ ፤
፲፰ ፤ ወአኅጕሉሙ ፡ ለኵሉሙ ፡
ነፍሳተ ፡ ተውኔት ፤
ዋዛ ፡ ፈዛዛ ፡ /ዘበሬታ/ ፡ የሚወዱ
ትን ፤ አንድም ፡ ጣዖት ፡ የሚያመ
ልኩትን ፡ ሰዎች ፡ አጥፋቸው ፤
ወለውሉደሙኒ ፡ ለትጉሃን ፡ እስመ
ገፍዕምሙ ፡ ለሰብእ ፤
ሰዎችን ፡ በድለዋቸዋልና ፤ ለኃ
ጢአት ፡ የሚተጉ ፡ የደቂቀ ፡ ሴት ፡
ልጆችንም ፡ አጥፋቸው ፤
ወአኅጕል ፡ ኵሉ ፡ ግፍዐ ፡ እምገጸ ፡
ምድር ፤
ግፉንም ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም
አጥፋ ፤
ወኵሉ ፡ ምግባር ፡ እኩይ ፡ ይኅልቅ ፤
ክፉ ፡ ሥራም ፡ ሁሉ ፡ ይጥፋ ፤
ወያስተርኢ ፡ ተክለ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ
ለዓለም ፤
የቅንነትና ፡ የጽድቅ ፡ ሥራ ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ይገለጽ ፡ አለ ፤ ምግባር ፡
ሃይማኖት ፡ ይገለጽ ፤
፲፱ ፤ ወይከውን ፡ ለበረከተ ፡ ግብር ፤
የሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለበ
ረከተ ፡ ሥጋ ፤ ለበረከተ ፡ ነፍስ ፡
ይሆናል ፤
ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ ለዓለም ፡ በፍሥሓ ፡
ይተከሉ ፤
ጽድቅና ፡ ቅንነት ፡ ለዘለዓለሙ ፡
በደስታ ፡ ይጸናሉ ፡ አለ ፤ ምግባር ፡
ሃይማኖት ፡ ይጸናሉ ፤
፳ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኵሉሙ ፡ ጻድቃን ፡
ይገኝዩ ፤
አሜሃ ፡ እንደማለት ፡ ያንጊዜ ፡ የኖኅ
ልጆች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዛሉ ፤
ወይከውኑ ፡ ሕያዋነ ፡ እስከ ፡ ይወ
ልዱ ፡ ዐሠርተ ፡ ምዕተ ፤
ሺሕ ፡ ልጆችንም ፡ እስኪ ፡ ወልዱ ፡
ድረስ ፡ ደኅንኞችን ፡ ይሆናሉ ፤
ያንጊዜ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ኖሮ ፡
አይደለም ፤ በፍጹም ፡ ቈጥሮ ፡
እንዲህ ፡ አለ ፤
፳፩ ፤ ወኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ውርዙቶሙ ፤
የሕፃንነታቸውን ፡ ዘመን ፤
ወሰንበተ ፡ ዚአሆሙ ፤
የዕርግናቸውን ፡ ዘመን ፡ ሰንበት
አለው ፤ በሰንበት ፡ እንዲያርፉ ፡
በርግናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ያርፉበ
ታልና ፤
ይፌጽሙ ፡ በሰላም ፤
በተድላ ፡ በደስታ ፡ ይፈጽማሉ ፤
፳፪ ፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡
ትትገበር ፡ ኵላ ፡ ምድር ፡ በጽድቅ ፤
በነዚያም ፡ ወራቶች ፡ ምድር ፡
ሁላ ፡ በእውነት ፡ ትታረሳለች ፤
ትቈፈራለች ፤

ዓቢይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊተኒ ።
ለኔም ፡ ገናና ፡ እግዚአብሔር ፡
ሰጥቶኛልና ፡ ዛሬ ፡ እኔ በሥጋዊ ፡
በደማዊ ፡ አንደበት ፡ በቃሌ ፡ የም
ናገረውን ፡ በመኝታዬ አየሁ ።
፴ ። እነ ፡ ስእለተክሙ ፡ ጸሐፍኩ ።
እኔ ፡ ልመናችሁን ፡ ጻፍሁላችሁ ።
፴፩ ። ወበራእይየ ፡ ከመዝ ፡ አስተ
ርአየኒ ።
በሕልሜ ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ።
እስመ ፡ ስእለትክሙ ፡ ኢትከውነክሙ ፡
ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ዓለም ።
ይህ ፡ ዓለም ፡ እንዲህ ፡ ጸንቶ ፡
በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ልመ
ናችሁ ፡ እንዳይደረግ ። ከመዝ ፡
ያስተርእየኒ ። እንዲህ ፡ ታየኝ ።
አንድም ፡ እስመ ፡ ኢትከልዕ ፡
ልመናችሁ ፡ አይደረግላችሁምና ።
፴፪ ። ወኮነኔ ፡ ፍጽምት ፡ ወጽእት ፡
ላዕሌክሙ ፡ ወኢይከውነክሙ ።
ፍጹም ፡ ፍርድ ፡ ፍጹም ፡
መቻያ ፡ በናንተ ፡ ታዘዘችባችሁ ።
ልመና ፡ አይደረግላችሁም ።
፴፫ ። ወእምይእዜ ፡ ኢተዐርጉ ፡
ውስተ ፡ ሰማይ ፡ እስከ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ።
ከዛሬም ፡ ጀምራችሁ ፡ ይህ ፡ እስኪ
ያልፍ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ደብር ፡
ቅዱስ ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ መዓርግ ፡
ወደ ፡ ሰማያዊ ፡ ግብር ፡ አትወ
ጡም ።
፴፬ ። ወውስተ ፡ ምድር ፡ ተነግረ ፡
ይእስርክሙ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መዋ
ዕለ ፡ ዓለም ።
በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ያስራችሁ ፡ ዘንድ ፡
በምድር ፡ ተነገረ ።
አንድም ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በምድር ፡
ያስራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ተነገረ ።
፴፭ ። ወእምቅድመ ፡ ዝንቱ ፡ ርኢ
ክሙ ፡ ኃጕለ ፡ ውሉድክሙ ፡ ፍቁራን ።
ከራሳችሁ ፡ ሞት ፡ አስቀድሞ ፡
የምትወዱዋቸውን ፡ የልጆቻች
ሁን ፡ ሞት ፡ አያችሁ ።
፴፮ ። ወአልብክሙ ፡ ጥሪያኒሆሙ ፡
አላ ፡ ይወድቁ ፡ ቅድሜክሙ ፡ በሰይፍ ።
ልጅነታቸው ፡ ለናንተ ፡ የላችሁም
ልጅ ፡ ላባቱ ፡ ጥሪት ፡ ነውና ። አን
ድም ፡ ቃየልናሆሙ ፡ ይላል ፡
ጥሪትናሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ። በፊ
ታችሁ ፡ በሰይፍ ፡ ተቀራድደው ፡
ያልቃሉ ፡ እንጂ ።
፴፯ ። ወስእለተክሙ ፡ በእንቲአክሙ ፡
ኢይከውን ፡ ወበእንቲአሆሙኒ ።
ስለናንተ ፡ የለመናችሁት ፡ ስለነሳ
ቸውም ፡ የለመናችሁት ፡ ልመና
አይደረግላችሁም ።
፴፰ ። ወአንትሙኒ ፡ እንዘ ፡ ትበክዩ ፡
ወታስቆቅዉ ።
ያው ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሚደረ
ግባችሁ ፡ እየለመናችሁ ፡ እያለቀሳ
ችሁ ፡ ነው ።
ወኢትትናገሩ ፡ ወኢምንተኒ ፡ ቃለ ፡
እምውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘጸሐፍኩ
ለክሙ ።
ከጻፍኩት ፡ መጻፍ ፡ ይህ ፡ ለኛ
ተደረገልን ፡ ብላችሁ ፡ ምንም ፡
ምን ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ አትናገ
ሩም ።

እኔ፡ግን፡ ፊቴን፡ደፍቼ ምድር ፡ ምድር ፡ አይ፡ነበር ፤ ለጊዜው ፡ እንዲህ ፡ያለ ፡ ራእይ ፡ አይቷል፤ ለኋላው ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ እሳት ፡ የረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፤ መጀመሪያ ፡ ያየው ፡ቤት፡የጻድቃን፡ ብሊት ፤ ዓለመ ፡ መላእክት፡ አሉ፡ አለ፣ ረድኤተ፡እግዚአብሔር፡ ካለ፡ መላእክት፡ አይለዩምና ፤ ምውቅ ከመ ፡ እሳት ፡ አለ ፣ በረድኤተ፡ እግዚአብሔር፡ጻድቃን ፡ ብሊት፡ ተጠብቀው፡የመኖራቸው ፣ ነፍሶሙሰ ፡ ለጻድቃን ፡ ውስተ እደ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢይለክፎሙ ፡ ሥቃይ[፪] ፡ እንዲል ፣ ወቈሪር፡ አለ፤በዓለሙ ፡ አሉበትና ፤ ወኢምንትኒ፡ፍግዓ ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገኘው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ በሱ ፡ የለም ፤ ኋላ ፡ ያየውን ፡ የጻድቃን ፡ ሐዲስ ፡ ዓለም፡ ይህ ፡ ይበልጣል ፡ አለ ፣ በባለሟልነት ይቀርባሉ፣ በክብር፡ ይበልጣሉና ፤ ወርኁት ፡ አለ ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት፡ከሠራ፡አይከለከልምና፤ ወለዘመጽአ ፡ ኅቤየ ፡ ኢይሰድዶ[፫]፡ እንዲል ፤ መንበረ ፡ ልዑል፡ አለ ፣አድሮባቸው ፡ ተዋህዷቸው ይኖራልና ፤ ወግልቡብ ፡ አለ ፣ በግላ ፡ አሪት ፡ መኖራቸውን ፡ መናገር፡ነው ፤ ታሕተ፡እኔጽር ፡ አለ ፣ ርደተ ፡ ገሃነም ፤ አምስት፡ ሺህ ፡ ካምስት ፡ መቶ ፡ዘመን ፡ እንደነበረባቸው ፡ መናገር ፡ ነው፤ አሜሃ ፡ ይትፌነዋ ፡ ነፍሳት ፡ ውስተ ፡ ገሃነም[፬]፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ መጀመሪያ ፡ ያየው ፡ የዓለመ ፡ ፍጡራን ፤ ምዉቅ ፡ አለ ፡ የሚሰጣቸው ፡ የባሕርይ ፡ ክብሩን ፡ ነውና ፤ ወቈሪር ፡ አለው፣ ሲቀበሉት ፡ ለእነርሱ ፡ የጸጋ ፡ ይሆንባቸዋልና ፤ አንድም፡ምውቅ፡ አለ፣ባለ፡መቶ፣ባለ፡ስሳ፡ አለና፤ ወቈሪር፡ አለ ፣ ባለ ፡ ሠላሳ ፡ አለና ፤ አንድም፡ምውቅ፡ወቈሪር፡ አለ ፣ እጅግም ፡ የማይፋጅ ፤ እጅግም ፤ የማይቀዘቅዝ፡ባዛ፡መሬት፡ ይወድዳል ፤ የምትወደድ፡መንግሥተ፡ሰማይን፡ያወርሳቸዋልና፡ ወኢምንትኒ ፡ ፍግዓ ፡ አለ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚገኝ፡ ተድላ፡ ደስታ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የለም፤ አንድም ፡ በዚያ ፡ የሌለ ተድላ ፡ ደስታ ፡ የለም ፤ ኋላ ፡ ያየው፡ ቤት ፡ የዓለመ ፡ፈጣሪ ፣ እርሱ፡ይበልጣል፡ አለ ፤ከዓለመ፡ ፍጡራን ፡ ዓለመ ፡ ፈጣሪ፡ ይበልጣልና ፡ የቀረው፡ አይለወጥም ፤

፪ ፣ ጥበብ ፫፥፩ ፤ ፫ ፣ ዮሐ. ፮፥፴፯

፬ ፣ ቄርሎስ

በወንዶችና : በሴቶች : በዚህ : ዓለም : ክፋትን : ያበዛሉ ፤ እንግዲህስ : ፍቅር : አንድነት : የላችሁም : በላቸው : አለኝ ፤

፰ ፤ ወነሥኡኒ : ውስተ : ፩ዱ : መካን : ኀበ : ሀለዉ : ህየ : ከመ : እሳት : ዘይነድድ ፤

እንደ : እሳት : የሚነድ : ደቂቀ ሴት : ወደአሉበት : አንድ : ቦታ : ወሰዱኝ : አለ ፤ መካነ : ኃጥአን ፤ አንድም : ስነ : ፍጥረት ፤

ወሶበ : ይፈቅዱ : ያስተርእዩ : ከመ ሰብእ ፤

ከመ : እሳት : ብሎ : ነበርና : ሰዎች : ናቸው : ለማለት : እንደ : ሰው : ይታያሉ : አለ ፤ አንድም : ለንጻሬ : የበቁ : ጻድቃን : ሊያዩዋቸው : በወደዱ : ጊዜ : እንደ : ሰው : ያዩዋቸዋል ፤

፱ ፤ ወወሰዱኒ : ውስተ : መካነ : ዘአውሎ : ወውስተ : ደብር : ዘከተማ : ርእሱ : ይበጽሕ : እስከ : ሰማይ ፤

ጥልቅ : ነፋስ : ወዳለበት : ቦታ ወሰዱኝ ፤ ጫፉ : እስከ : ሰማይ : የሚደርስ : ተራራ : አየሁ ፤ ስነ : ፍጥረት : ነው ፤ አንድም : መካነ : ኃጥአን : ላገኛቸው : መከራ : ፍጻሜ : እንደ : ሌለው : ለማጠየቅ ፤

፲ ፤ ወርኢኩ : ፩ተ : መካናተ : ብሩሃተ ፤

አንድ : መካነ : ኃጥአንን ፤ ሦስቱን : መካነ : ጻድቃንን : አየሁ ፤ ሦስት : አለ : ባለ : መቶ ፤ ባለስሳ ፤ ባለ : ሠላሳ : ስለኖረባት ፤ አንድም : ወጣኒ ፤ ማዕከላዊ ፤ ፍጹማዊ : ስለኖረባት : መካነ : ኃጥአንን : ብሩህ : አለው : በጻድቃን : አስጠግቶ ፤

ወነጐድጓድ : ውስተ : አጽናፍ ፤

በመካነ : ጻድቃን : አጠገብ : ባለ : በመካነ : ኃጥአን : ነጐድጓድ : አለ ፤

ወኀበ : ዕመቀ : ቀስተ : እሳት ፤

በጥልቀነቱ : ዘንድ : ቀስተ : እሳት : አለ ፤

ወሐፅ : ወምጕንጳቲሆሙ ፤

የኃጥአን : ጕራንጕሬያቸው : አለ ፤ ሰይፈ : እሳት : መባርቅት አለ ፤ መቅሠፍተ : ኃጥአንን : በምሳሌ : ያሳየዋል ፤

ወሰይፈ : እሳት : ወመባርቅት : ኵሉ ፤

የእሳት : ሰይፍ : መብረቆችም ሁሉ : አሉ ፤

፲፩ ፤ ወነሥኡኒ : እስከ : ማየ : ሕይወት : ዘይትናገር ፤

ድምጽ : ያለው : የመጣያ : ውኃ : ወዳለበት ፤ አንድም : ዘይትነገር : ቢል : በኔ : ቃል : የሚነገር : ማየ : ሕይወት : እስካለበት : ድረስ ፤ አንድም : በሰው : አድሮ : የሚናገር : ማየ : ሕይወት : መንፈስ : ቅዱስ ፤ አንድም : ዘይትነገር : በኔ : ቃል : የሚነገር : ማየ : ሕይወት : መንፈስ : ቅዱስ : እስከሚሠጥበት : ዘመን : ድረስ : አደረሱኝ ፤

ወእስከ : እሳተ : ዓረብ ፤

ሰማይ ፡ የጸናበትንም ፡ አራቱን ነፋሳት ፡ አየሁ ፤

፲፰ ፤ ወርኢኩ ፡ ከመ ፡ ነፋሳት ፡ ይረብብዋ ፡ ለልዕልና ፡ ሰማይ ፤

ልዕልት ፡ ሲል ፡ ነው ፣ ልዕልት ሰማይን ፡ እንደ ፡ ካስማ ፡ የያዟት ፡ ነፋሳትን ፡ እንደ ፡ ምሰሶ ፡ ሁነው ፡ አየሁ ፤

፲፱ ፤ ወእሙንቱ ፡ ይቀውሙ ፡ ማዕከለ ሰማይ ፡ ወምድር ፤

ከእነሳቸውም ፡ በምድርና ፡ በሰ ማይ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ አዕማድ ፡ (ምሰሶዎች) ፡ ሁነው ፡ ቁመው ፡ አየሁ ፤

ወእሙንቱ ፡ ውእቶሙ ፡ አዕማደ ፡ ሰማይ ፤

እነሳቸውም ፡ የሰማይ ፡ ምሰሶዎች ናቸው ፤

፳ ፤ ወርኢኩ ፡ ነፋሳተ ፡ እለ ፡ ይመ ይጥዋ ፡ ለሰማይ ፤

ሰማይን ፡ የሚሽከሙ ፡ ነፋሳትን አየሁ ፤

ወእለ ፡ ያዐርቡ ፡ ክበበ ፡ ፀሐይ ፡ ወኵሎ ፡ ከዋክብተ ፤

ፀሐይን ፡ ከዋክብትን ፡ የሚያገቡ ፡ ነፋሳትን ፡ አየሁ ፤

፳፩ ፤ ወርኢኩ ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ፡ ነፋሳተ ፡ ዘይፀውሩ ፡ ደመናተ ፤

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ደመናትን ፡ የሚ ሸከሙ ፡ ነፋሳትን ፡ አየሁ ፤

፳፪ ፤ ወርኢኩ ፡ ፍናወ ፡ መላእክት ፤

ጐልቄ ፡ መላእክት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የመላእክትንም ፡ ቍጥር ፡ አየሁ ፤

ወርኢኩ ፡ ውስተ ፡ ጽንፈ ፡ ምድር ፡ ጽንዐ ፡ ዘሰማይ ፡ መልዕልተ ፤

ጠፈር ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የጸናበትን ፡ አድማስን ፡ አየሁ ፤ አንድም ፡ በላይ ፡ ሁኜ ፡ ጠፈር ፡ የጸናበት ፡ አድማስን ፡ አየሁ ፤

፳፫ ፤ ውኀለፍኩ ፡ መንገለ ፡ አዜብ ፡ ወይነድድ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ኀበ ፯ቱ ፡ አድባር ፡ ዘእምዕብን ፡ ክቡር ፣

ወኀለፍኩ ፡ መንገለ ፡ አዜብ ፡ ኀበ ፡ ፯ቱ ፡ አድባር ፡ ዘእምዕብን ክቡር ፡ ዘይነድድ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በመዓ ልትም ፡ በሌሊትም ፡ የሚያበራ ፡ ነው ፤ ከከበረ ፡ በአዜብ ፡ እኩል ፡ ወዳለ ፡ ተራራ ፡ ሄድኹ ፤ አንድም ፡ የዕንቍ ፡ ተራራ ፡ ወዳለበት ፡ ሄድኹ ፤

፳፬ ፤ ፫ቱ ፡ ዘመንገለ ፡ ጽባሕ ፡ ወ፫ቱ ፡ ዘመንገለ ፡ አዜብ ፤

ሦስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፣ ሦስቱ ፡ በዓዜብ ፡ በኩል ፡ ናቸው ፤

ወዘመንገለ ፡ ጽባሕሰ ፡ ዘእምዕብነ ፡ ኅብር ፤

ከሦስቱ ፡ አንዱ ፡ ብዙ ፡ መልክ ካለው ፡ ዕንቍ ፡ ወገን ፡ ነው ፤

ወ፩ዱ ፡ ዘእምዕብነ ፡ ባሕርይ ፤

አንዱ ፡ ባሕርይ ፡ ከሚባል ፤

ወአሐዱኒ ፡ ዘእምዕብነ ፡ ፈውስ ፣

አንዱ ፣ ደመ-ረጭ ፣ (ደመአርድ)፡ የሚባል ዕንቍ ፡ ያለበት ፡ ነው ፤

ወዘመንገለ ፡ አዜብ ፤

## ጉባኤ

፵ ፤ ወአነ ፡ ሄኖክ ፡ ርኢኩ ፡ አር
ዐያ ፡ ባሕቲትየ ፤
እኔ ፡ ሄኖክ ፡ የብቻዬን ፡ ነገር
የብቻዬን ፡ ምሥጢር ፡ አየሁ፤
አንድም ፡ ሳይናበብ ፡ ብቻዬን ፡
ምሥጢር ፡ አየሁ ፤
አጽናፈ ፡ ኵሉ ፤
በጽንፈ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
አየሁ፤
ወአልቦ ፡ ዘርእየ እምሰብእ ዘከመ ፡
አነ ፡ ርኢኩ ፡
እኔ ፡ እንዳየሁት ፡ ያየ ፡ የለም
አለ፤ ራእዩ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ነውና፤
አንድም ፡ እርሱ ፡ ያየውንም ፡
ያየ ፡ የለምና ።

## ምዕራፍ ፳

፩ ፤ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አስማቲ
ሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይተግሁ ፡ ቅዱሳን ፡
መላእክት፤
ለቅዳሴ ፤ ለተልዕኮ ፤ ለተራድኦ
የሚተጉ ፤ የቅዱሳን ፡ መላእክት ፡
ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤
፪ ፤ ዑራኤል ፡ ፩ዱ ፡ እመላእክት
ቅዱሳን ፤
ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡
ዑራኤል ፡ ነው ፤ ዑራኤል ፡ ማለት ፡
ብርሃነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡
ነው ፤
እስመ ፡ ዘረዓም ፡ ወዘረዓድ ፤
በመብረቅ ፡ በነጐድጓድ ፡ የተሾመ ፡
ነውና ፤

፫ ፤ ሩፋኤል ፡ ፩ዱ ፡ እመላእክት ፡
ቅዱሳን ፡ ዘመናፍስተ ፡ ሰብእ ፤
ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡
ሩፋኤል ፡ ነው ፤ ሩፋኤል ፡ ማለት ፡
ፈውስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለት ፡
ነው ፤ ዘመናፍስተ ፡ ሰብእ ፡ አለው ፡
በሰው ፡ ነፍሳት ፡ ወይም ፡ በሰው ፡
ቍስል ፡ የተሾመ፤
፬ ፤ ራጉኤል ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት፡
ቅዱሳን ፤
ከከበሩ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡
ራጉኤል ፡ ነው ፤ ራጉኤል ፡ ማለት ፡
ራእየ ፡ እግዚአብሔር ማለት ፡
ነው ፤
ዘይትቤቀሎ ፡ ለዓለም ፤
ይህን ፡ ዓለም ፡ የሚያሳልፍ ፤
ወለብርሃናት ፤
ፀሐይን ፡ ጨረቃን ፡ የሚያሳልፍ፤
ፍጡራንንስ ፡ በፍጡር ፡ እጅ ፡ አያ
ሳልፋቸውም ፡ ብሎ ፡ ዲያብሎስን ፡
የሚበቀል ፤
ወለብርሃናት ፤
አጋንንትን ፡ የሚበቀል ፤ እስመ
ለሊሁ ፡ ሰይጣን ፡ ይትሜሰል ፡
ከመ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ እንዲል[፩] ፤
አንድም ፡ ህየንተ ፡ ብርሃናት ፡ ቢል ፡
ስለ ፡ ጻድቃን ፡ ዲያብሎስን ፡ የሚ
በቀል ፤
፭ ፤ ሚካኤል ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ፡
ቅዱሳን ፤
ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡
ሚካኤል ፡ ነው ፤ ሚካኤል ፡ ማለት፡
መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ማለት ፡
ነው ፤ ዕፁብ ፡ ነገርም ፡ ይለዋል ፤

፩ ፤ ፪ኛ ቆሮ. ፲፩ ፡ ፲፬

በፍጹም ፡ ተናግሮ ፡ ሰባት ፡ አለ ፤ ከዋክብት ፡ አላቸው ፡ በጥንተ ፡ ግብራቸው ፡ ነው ፤

ከመ ፡ አድባር ፡ ዓበይት ፡ ወከመ ፡ ዘእሳት ፡ እንዘ ፡ ይነድዱ ፡፡

እሳት ፡ እንደ ፡ ተያያዛቸው ፡ እንደ ፡ ታላላቆች ፡ ተራሮች ፡ የሚነዱ ፡ ደቂቀ ፡ ሴትን ፡ ከዚያ ፡ አንድነት ፡ ሁነው ፡ አየሁ ፤

፲ ፤ ይእተ ፡ ጊዜ ፡ ዕቤ ፡ በእንተ ዓይ ፡ ኃጢአት ፡ ተአሥሩ ፤

ያን ፡ ጊዜም ፡ በምን ፡ ኃጢአት ፡ ታሥረው ፡ ተግዘዋል ?

ወበእንተ ፡ ምንት ፡ ዝየ ፡ ተገድፉ ፤

በምንስ ፡ ኃጢአታቸው ፡ በዚህ ወድቀዋል ? አልሁ ፤

፲፩ ፤ ወይቤለኒ ፡ ዑርኤል ፡ ፩ዱ ፡ እመላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ ዘምስሌየ ፡ ውእቱ ፡ ወይመርሐኒ ፤

ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ ወደደውም ፡ ሥራ ፡ የሚመራኝ ፡ ከከበሩ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱ ፡ ዑራኤልም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፤

ወይቤ ፡ ሄኖክ ፡ በእንተ ፡ መኑ ፡ ትሴአል ፡ ወበእንተ ፡ መኑ ፡ ትጤይቅ ፡ ወትጽሕቅ ፡፡

ሄኖክ ፡ ስለማን ፡ ትጠይቃለህ ? ስለማንስ ፡ ልትረዳ ፡ ትተጋለህ ? አለኝ ፤

እምከዋክብት ፡ እለ ፡ የኃልፉ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፤

ከደቂቀ ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ሳይቀሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ የተጋዙ ፡፡ አንድም ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያለፉ ፡ ናቸው ፤

፲፪ ፤ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ መላእክት እለ ፡ ኃለፉ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ልዑል ፤

እኒህ ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፡ ያፈረሱ ፡ የሴት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤

ወተአሥሩ ፡ በዝየ ፡ እስከ ፡ ይትፌጸም ትእልፊተ ፡ ዓለም ፡ ኍልቈ ፡ መዋዕለ ኃጢአቶሙ ፤

የኃጢአታቸው ፡ ዘመን ፡ ቍጥር የሚሆን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ቍጥር ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ተግዘዋል ፤

፲፫ ፤ ወእምህየ ፡ ሖርኩ ፡ ካልዓ መካነ ፡ እምዝ ፡ ዘይጌርም ፡፡

ከዚያም ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ወደሚያስፈራ ፡ ወደሌላ ፡ ቦታ ፡ ሔድኹ ፤

፲፬ ፤ ወርኢኩ ፡ ግብረ ፡ ግሩመ ፤

በዚያም ፡ የሚያስፈራ ፡ ሥራ ፡ አየሁ ፤

እሳት ፡ ዓቢይ ፡ በህየ ፡ ዘይነድድ ፡ ወያንበለብል ፤

በዚያም ፡ ቦታ ፡ ፈጽሞ ፡ የሚቃጠል ፡ ታላቅ ፡ ቋያ ፡ አለ ፤

ወምሰርት ፡ ቦቱ ፤

መጋዝ ፡ አለበት ፤

ወወሰኑ ፡ እስከ ፡ ቀላይ ፡ ፍጹም ፤

ጥርሱ ፡ በምልዓት ፡ ፍጹም ፡ እስከሆነ ፡ እስከ ፡ ውቅያኖስ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ወምሰርት ፡ ሰይፍ ፡ አለ ፤ ወሰኑ ፡ ጫፉ ፡ በምልዓት ፡ ፍጹም ፡ እስከ ፡ ሆነ ፡ እስከ ፡ ውቅያኖስ ፡ ነው ፤

ወእፅባነ ፡ ክቡራነ ፤ ወሠናያነ ፤
ያማሩና ፡ የከበሩ ፡ ድንጋዮችንም፡
አየሁ ፤
ወኵሉ ፡ ክቡር ፤
ሁሉም ፡ ጽሩያን ፡ ናቸው፤
፬ ፤ ወስቡሕ ፡ ራእዮሙ ፤
መልካቸው ፡ የበራ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፤
ወሠናይ ፡ ገጸሙ ፡
አካላቸው ፡ ጽሩይ ፡ ነው ፤ ፊታቸ
ውም ፡ ያማረ ፡ ነው ፤
ወሠለስቱ ፡ መንገለ ፡ ጽባሕ ፤
ሦስቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ናቸው ፤
ወጽኑዓን ፡ ፩ዱ ፡ ዲበ ፡ ፩ዱ ፤
አንዱን ፡ ካየሁት ፡ በኋላ ፡ ያየ
ሁት ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ጽኑ
ዓን ፡ ናቸው ፤ አንድም ፡ ጽው
ናን ፡ ቢል ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ፡
የተያያዙ ፡ የተደራረቡ ፡ ናቸው ፤
፭ ፤ ወሠለስቱ ፡ መንገለ ፡ ሰሜን ፡
፩ዱ ፡ ዲበ ፡ ፩ዱ ፡ ጽኑዓን ፤
ሦስቱም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡
አንዱን ፡ ካየሁ ፡ በኋላ ፡ ያየሁት ፡
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ጽኑዓን ፡
ናቸው ፤ አንድም ፡ ጽውናን ፡ ቢል ፡
አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡
ጣት ፡ የተያያዙ ፡ ናቸው ፤
ወቈላት ፡ ዕሙቃት ፡ ወጠዋያት ፤
ጠማማ ፡ ጥልቅ ፡ የሆኑ ፡ ቈላዎች ፡
አሉ ፡ አለ ፤ በኃጢአት ፡ በክህደት ፡
ፍጹማን ፡ የሆኑ ፡ የሚኖሩባት ፡
ብሔረ ፡ አሕዛብ ፡ አለ ፤
አሐቲ ፡ ለአሐቲ ፡ ኢይትቃረባ ፤
አሐቲ ፡ ወአሐቲ ፡ እንደማለት ፤
አንዲቱና ፡ አንዲቱ ፡ አይቀራረ
ቡም ፤ አንድም ፡ ኢትቀርባ ፡ ቢል ፡
አንዲቱ ፡ አንዲቱን ፡ አትቀርባ
ትም ፤ አሕዛብ ፡ በግብርም ፡ በኃጢ
አትም ፡ አይቀራረቡም ፡ ሥራ
ቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነውና ፤
፮ ፤ ወሳብዕ ፡ ደብር ፡ ማእከሎሙ
ለእሉንቱ ፤
በመካከላቸው ፯ተኛ ፡ ተራራ ፡
አለ ፤
ወኑኃሙስ ፡ ይትማሰሉ ፡ ኵሎሙ ፡
ከመ ፡ መንበረ ፡ አትራኖስ ፤
ቁመታቸውም ፡ እንደ ፡ አፍርንጂ ፡
ወምበር ፡ የተካከለ ፡ የተመሳሰለ ፡
ነው ፤ ለጊዜው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
አሳይቶታል ፤ ለኋላው ፡ ምሳሌ ፡
ነው ፤ መጀመሪያ ፡ ያየው ፡ ተራራ ፤
ገነት ፡ ናት ፤ በዚያ ፡ ያሉ ፡ አዳ
ምና ፡ ሔዋን ፡ ናቸው ፤ ሁለተኛ ፡
ያየው ፡ ተራራ ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡
ነው፤ በዚያም ፡ ያሉ ፡ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ ናቸው ፤ ሦስተኛ ፡ ያየው ፡
ተራራ ፡ ሐመረ ፡ ኖኅ ፡ ናት ፤
በዚያ ፡ ያሉት ፡ ኖኅ ፡ ከነልጆቹ ፡
ናቸው ፤ አራተኛ ፡ ያየው ፡
ተራራ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ነው ፤
በዚያ ፡ ያሉ ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡
ናቸው ፤ አምስተኛ ፡ ያየው ፡
ደብረ ፡ ዘይት ፡ ነው ፤ በዚያ ፡
ያሉ ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞን ፡ ናቸው ፤

ስድስተኛ ፡ ያየው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ያሉ ፡ ባርቅ ፡ ዲቦራ ፡ ናቸው ፤ ሰባተኛ ፡ ያየው ፡ ቀራንዮ ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ ያሉ ፡ ጌታ ፡ ሐዋ ርያት ፡ ናቸው ፤ ሳብዕ ፡ ያለው ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ለተ ራራው ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፤ ማእከል ፡ አለው ፤ በምሥራቅ ፡ ያሉ ፡ ገነት ፤ ደብር ፡ ቅዱስ ፤ ሐመረ ፡ ኖኅ ፡ ናቸው ፤ በምዕራብ ፡ ያሉ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፤ ደብረ ፡ ታቦር ፤ ቀራንዮ ፤ ናቸው ፤ መካከሉ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ነው ፤

፯ ፤ ወየዐውድዎ ፡ ዕፀው ፡ መዓዛ ፤

መዓዛ ፡ ያላቸው ፡ እንጨቶች ፡ ከበውታል ፤ ማለት ፡ ሕገጋቱ ፡ ከበውታል ፤

ወሀሎ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ዕፅ ፡ አልቦ ፡ ግሙራ ፡ አመ ፡ ፄነወኒ ፡ ወኢአሐዱ እምውስቴቶሙ ፤

በመካከላቸውም ፡ አንድ ፡ እን ጨት ፡ አለ ፤ በሽተተኝም ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሳቸው ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ የሸተተኝ ፡ የለም ፤ አንድም ፡ ኢታምልክ ፡ በመካከላ ቸው ፡ አለ ፤ ከሕግጋቱም ፡ ሁሉ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በመስጠት ፡ ኢታ ምልክን ፡ የሚመስለው ፡ የለም ::

፰ ፤ ወባዕዳንሂ ፡ ዘከማሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘይምዕዝ እምኵሉ ፡ መዓዛ ፤

ኢኮነም ፡ ካለ ፡ ባዕድሂ ፤ ባዕዳ ንሂም ፡ ካለ ፡ ኢኮኑ ፡ ባለ ፡ በቀና ፡ ነበር ፤ በሸተተኝ ፡ ጊዜ መዓዛ ፡ ካላቸው ፡ ዕፀው ፡ እንደ እርሱ ፡ የሚሸት ፡ የለም ፤ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ካላቸው ፡ ሕገጋት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በማስጠት ፡ እንደ ፡ ኢታምልክ ፡ ያለ ፡ የለም ፤

፱ ፤ ወቈጽሉሂ ፡ ወጽጌሁ ፤ ወዕፀ ፡ ኢይጸመሂ ፡ ለዓለም ፤

ቅጠሉ ፤ አበባው ፤ እንጨቱ ፤ ለዘለዓለም ፡ አይጠወልግም ፤ ማለት ፡ በኢታምልክ ፡ የሚገኘው፡ ጸጋ ፤ ክብር ፤ አይጠፋም ፤ ማለት፡ ነው ፤

፲ ፤ ወፍሬሁኒ ፡ ሠናይ ፤

ፍሬውም ፡ ብዙ ፡ ነው ፤

ወፍሬሁስ ፡ ከመ ፡ አስካለ ፡ በቀልት፤ ፍሬውም ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ፍሬ ፡ ንብብር ፡ ነው ፤ ማለት፡ በኢታ ምልክ ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ በፊት ፡ ለማየት፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፤ ማለት፡ ኢታምልክ ፡ በዓይነ ፡ ልቡና ፡ ለማየት ፡ ደስ ፡የሚያሰኝ ፡ ነው፤

፲፩ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ዕቤ ፡ ነዋ ፡ ዝንቱ ፡ ሠናይ ፡ ዕፅ ፡ ወሠናይ ፡ ለርእይ ፡ ወአዳም ፡ ቈጽሉ ፡ ወፍሬ ሁኒ ፡ ሞገስ ፡ ጥቀ ፡ ለርእየ ፡ ገጽ፤

ያን ፡ ጊዜም ፡ ይህ እንጨት ፡ እነሆ ያማረ ፡ ነው ፤ ቅጠሉ ፡ ጽፍቅ ፡ ነው ፤ ፍሬው ፡ ንብብር ፡ ሊያዩትም ፡ ፈጽሞ ፡ የተወደደ ነው ፡ አልሁ ፤

፲፪ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ አውሥአኒ ፤ ሚካኤል ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ፡

በዘመናቸው ፡ መከራና ፡ ኃዘን ፣ መቅሠፍትና ፡ ድካምም አያገኛ ቸውም፣ (አይዳስሳቸውም) ።
፰፱ ። ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ባረክዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ስብሐት ፡ ንጉሥ ፡ ዘለ ዓለም ።
እንደዚህም ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮ ፡ ሰጥ ቷቸዋልና ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ የሚሆን ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታን ፡ አመሰገንሁት አለ ።
እስመ ፡ አስተዳለወ ፡ ከመዝ ለሰብእ ጻድቃን ወከመዝ ፡ ፈጠረ ።
እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ወዳጆቹ ፡ ስለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ኢታምልክን ፡ አዘጋጅቷልና ።
ወይቤ ፡ የሀብዎሙ ።
ይህን ፡ ዕፀ ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ አሏልና ፣ ማለት ፡ በኢታምልክ ፡ የሚገኘውን ፡ ሥርዓት ፡ ያስተም ሯቸው ፡ ዘንድ ፡ አስተምሯቸው ፡ ብሎ ፡ አሏልና ፡ አመሰገንሁት ።
አንድም ፡ ሳብዕ ፡ ደብር ፡ ቀራን ዮን ፡ ማዕከል ፡ አለው ፤ በም ሥራቅ ፡ ያሉ ፡ ገነት ፣ ደብር ፡ ቅዱስ ፣ ሐመረ ፡ ኖኅ ፡ ናቸው ፤ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ያሉ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፣ ደብረ ፡ ዘይት ፣ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ናቸው ፤ መዓዛ ፡ ያላቸው ፡ ዕፀው ፡ ከበውታል ፡ ማለት ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታት ፡ መከራ ፡ ከበውታል ፣ መከራ ፡ የሚቀበሉ ፡ ጌታን ፡ አብነት ፡ እያደረጉ ፡ ነውና ፤ በውስጣቸው ፡ ከእርሳቸው ፡ መዓዛ ፡ የሚበልጥ ፡ ዕፀ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በማሰጠት ፡ ከሰማዕታት ፡ የሚበ ልጥ ፡ የጌታ ፡ መስቀል ፡ አለ፤ በሸተተ ፡ ጊዜ ፡ በመዓዛ ፡ የሚመ ስለው ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ በማስጠት ፡ የሚመስ ለው ፡ የለም ፤ ጻድቃን ፡ ሰማዕ ታት ፡ እንከበርበት ፡ ብለው ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ግን ፡ እከብር ፡ አይል ፡ ክቡር ፤ እጸድቅ ፡ አይል ፡ ጻድቅ ፡ ነውና ፤ ቅጠሉ ፣ አበ ባው ፣ እንጨቱ ፡ አይጠወልግም ፣ ማለት ፡ በመስቀል ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ አይጠፋም ፣ ፍሬው ፡ ንብ ብር ፡ ነው ፤ ማለት ፡ በመስቀል ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ለፊት ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፡ ማለት ፡ መስቀል ፡ ለዓይነ ፡ ሕሊና ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፣ ያንጊዜ ፡ ከሊቃነ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ የዚህን ፡ ዕፅን ፡ ነገር ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህ ? ማለት ፡ የጌታን ፡ መከራ ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለህ ? አለኝ ፣ ማወቅስ ፡ ሁሉንም ፡ ሳውቅ ፡ እወዳለሁ ፣ ይልቁንም ፡ የዚህን ፡ ዕፀ ፡ ነገር ሳውቅ ፡ እወዳለሁ ፤ ማለት ፡ ማወቅስ ፡ የጻድቃን ፡ የሰማዕታ ትን ፡ መከራ ፡ ሳውቅ ፡ እወዳለሁ፤ ይልቁንም ፡ የጌታን ፡ መስቀል ፡ ሳውቅ ፡ እወዳለሁ ፤ ራሱ ፡ የጌታን ፡ ዙፋን ፡ የሚመስለው ፡

ጥበብ ፡ ማደሪያዋን ፡ አላገኘችም፤ ወደ ፡ ማደሪያዋ ፡ ወደ ፡ መላእክት፡ ልቡና ፡ ተመለሰች ፤ ተነሥታ ቸው ፡ ኑሪ ፡ ማለት ፡ አይደ ለም ፤ እንደያዟት ፡ ቀሩ ፡ ሲል፡ ነው ፤

ወተጽዕነት ፡ ማዕከለ ፡ መላእክት ፤

በመላእክት፡ መካከል ፡ አደረች፤

፫ ፤ ወዓመፃ ፡ ወጽአት ፡ እመዛግብቲሃ፤

ክህደት፣ ኃጢአት ፣ ከዲያብሎስ ከአጋንንት ፡ ተገኘች ፤

ዘኢፈቀደት ፡ ረከበት ፤

ያልወደደችውን ፡ አገኘች ፣ መውደድስ ፡ ወዳዋለች ፤ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በሕጉ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ ይበድላል ፡ ስላሳሉት ፤ አንድም ፡ ዘፈቀደት ፡ ቢል ፡ የወደደችው ፡ ሕሊና ፡ አዳምን ፡ አገኘች ፤ አንድም ፡ ዘኢፈቀዳ ፡ ቢል ፡ ሕሊና ፡ ፈጣሪ ፡ ያልወደዳት ፡ ኃጢአት አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ አገኘች ፤

ውኀደረት ፡ ውስቴቶሙ ፡ ከመ ፡ ዝናም ፡ በበድው ፤ ወከመ ፡ ጠል ፡ በምድር ፡ ጽምዕት ፣

ዝናም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፣ ጠል ፡ በተጠማች ፡ ምድር ፡ እንዲወደድ ፡ በእነርሱ ፡ ተስማማች ፤

፬ ፤ ወርኢኩ ፡ ካልዓነ ፡ መባርቅተ ፡ ወከዋክብተ ፡ ሰማይ ፤

ሌሎች ፡ መባርቅትን፣ የሰማይ ፡ ከዋክብትን፡ አየሁ ፡ አለ ፤ የመምህራን፡ ምሳሌ ፡ መባርቅትን ፤ የአርድዕትን ፡ ምሳሌ ፡ ከዋክብትን ፡ አየሁ ፤

፭ ፤ ወርኢኩ ፡ ከመ ፡ ይጼውዖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ በበአስማቲሆሙ ፡ ወይሰምዕዎ ፤

ሁሉንም ፡ በየስማቸው ፡ ሲጠራቸው ፣ እነሱም ፡ ሲሰሙት ፡ አየሁ ፡ አለ ፣ መምህራንን ፡ አርድዕት ፡ (ደቀ መዛሙርት)፡ ሲላቸው ፡ ሰማሁ ፤

፮ ፤ ወርኢክዎ ፡ ለመዳልወ ፡ ጽድቅ ፡ ከመ ፡ ይዴለዉ ፡ በብርሃናቲሆሙ ፡ በራሕበ ፡ መካናቲሆሙ ፤

ልቡናቸውን ፡ በአዕምሮ ፡ አስፍተው ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ በፍትሐ፡እግዚአብሔር ፡ ሲመጠን፣ ዋጋቸውን ፡ሲሰጣቸው ፡ አየሁ ፤

፯ ፤ ወዕለተ ፡ ኩነቶሙ ፤

በማኅፀን ፡ ከጨዋነት ፡ ወደ ፡ መምህርነት ፡ ወደ ፡ ነቢይነት ፡ የተመለሱበትን ፡ ቀን ፡ አየሁ ፤ እንደ ፡ ኤርምያስ ፣ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡ ቀደስኩከ ፡ እምከርሠ ፡ እምከ ፡ እንዳላቸው ፤

ወሚጠቶሙ ፤

ከጨዋነት ፡ ወደመምህርነት ፡ ወደነቢይነት ፡ የተመለሱበትን አየሁ ፤ እንደ ፡ ዮናስ ፡ እንደ አብድዩ ፤

መብረቅ ፡ መብረቀ ፡ ይወልድ ፤

መብረቅ ፡ መብረቅን ፡ ይወልዳል ፡ አለ ፣ መምህር ፡ መምህርን ፡ ያስገኛል፤

መሆንን፡ መተው ፡ አይችሉም፤
አንድም፡ መምህራኑ፡ ለአርድዕት
አብነት ፡ መሆንን ፣ አርድዕት ፡
ለመምህራን ፡ ምሳሌ ፡ መሆንን ፡
መተው ፡ አይችሉም ፤ አንድም
ምስሌሆሙ ፡ ቢል ፡ መምህራን
ከአርድዕት ፡ ጋራ ፣ አርድዕት ፡
ከመምህራን ፡ ጋራ ፡ መኖር ፡
መተውን ፡ አይችሉም ፤
፲፮ ፤ ወዝ ፡ ካልዕ ፡ ምሳሌ ፡ ዲበ ፡
እለ ፡ ይክህዱ ፡ ስሞ ፡ ለማኅደረ ፡
ቅዱሳን፤
የቅዱሳን ፡ ማደሪያ ፡ የሚሆን ፡
የክርስቶስን ፡ ስም ፡ በሚክዱ ፣
ወለእግዚእ ፡ መናፍስት ፤
የእብን፡ ስም ፡ በሚክዱ ፡ ሰዎች
የተነገረው ፡ ሁለተኛ ፡ ነገር ፡
ይህ ፡ ነው ፤
፲፯ ፤ ኢሰማየ ፡ የዐርጉ ፣
ወደ ፡ ሰማይ ፡ አይወጡም ፤
ወኢምድረ ፡ ይበጽሑ ፤
ወደ ፡ ምድርም፡ አይደርሱም ፤
ኑሯቸው ፡ በኅዋው ፡ ነው ፤ ላገ
ኛቸው ፡ መከራ ፡ ፍጻሜ ፡ እን
ደሌለው ፡ ለማጠየቅ ፡ ነው፤
ከመዝ ፡ ይከውን ፡ ክፍለ ፡ ኃጥአን ፡
እለ ፡ ይክህዱ ፡ ስሞ ፡ ለእግዚእ ፡
መናፍስት ፤
የመላእክትን ፡ ጌታ ፡ ስም ፡
የሚክዱ ፡ የኃጢአተኞች ፡ ዕድል ፡
እንዲህ ይሆናል ፤
እለ ፡ ከመዝ ፡ ይትዐቀቡ ፡ ለዕለተ
ሥራሕ ፡ ወምንዳቤ ፣
ፍጹም ፡ መከራ ፡ በሚደረግበት ፡
ቀን ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡
ከብዙ ጣር ፡ ጋር ፡ ለመከራ ፡
ቀን ፡ ይጠበቃሉ ፤
ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ ይነብር ፡
በመንበረ ፡ ስብሐት ፡ ኅሩይ ፣
በዚህች ፡ ቀን ፡ ኅሩይ ፡ ክርስቶስ
በጌትነቱ፡ ዙፋን ፡ ይቀመጣል ፤
፲፰ ፤ ወየኀሪ ፡ ምግባሪሆሙ ፡ ወም
ዕራፎሙ ፡ ወኍልቍ ፡ አልቦሙ ፣
ሥራቸውንም ፡ ቦታቸውንም ፡
ይመረምራል ፤ ቍጥር ፡ የላቸ
ውም ፣ በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡
ለሚኖሩት ፡ አነዋወር ፡ ፍጻሜ
የለውም ፡
፲፱ ፤ ወመንፈሶሙ ፡ በማዕከሎሙ ፡
ትጸንዕ ፡ ሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ለኅሩየ ፡
ዚእየ ፤
በመካከላቸው ፡ ያለች ፡ ልቡናቸው፡
የመረጥሁት ፡ ክርስቶስን ፡ ባዩት ፡
ጊዜ ፡ ትጸናለች ፤
፳ ለእለ ፡ ይሰክዩ ፡ ስምየ ፡ ቅዱስ ፡
ወስቡሐ ፤
ስሜን ፡ የሚማፀኑ ፣ ስሜን ፡
ያመኑ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፤
፳፩ ፤ ወበይእቲ ፡ ዕለት ፡ አነብሮ ፡
ለኅሩየ ፡ ዚእየ ፡ በማዕከሎሙ ፤
በዚያችም ፡ ቀን ፡ የመረጥሁት
ክርስቶስን ፡ በመካከላቸው ፡ አኖረ
ዋለሁ ፡ አለ ፤
፳፪ ፤ ወእዌልጣ ፡ ለሰማይ ፣
ሰማይን ፡ አሳልፋታለሁ ፤
ወእገብራ ፡ ለበረከት ፣

የሰው ፡ ተሥዕሎተ ፡ መልክዐ ፡ አንድ ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ ከኪሩቤል እንደ ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ አለ ፤ እንደ ፡ ገጸ ፡ ሰብእ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ነው ፡ አለ ፤ ገብርኤል ፡ ማለት ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ማለት ፡ ነውና ፤

፳፩ ፤ ወተስእልክዎ ፡ ለአሐዱ ፡ እመ ላእክት ፡ ቅዱሳን ፡ ዘየሐውር ፡ ምስ ሌየ ፡ ወኵሎ ፡ ኅቡአተ ፡ ዘአርአየኒ ፡ በእንተ ፡ ዝኩ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፤

ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሚኖር ፡ የተሰወ ረውንም ፡ ሁሉ ፡ የገለጠልኝ ፡ ከከ በሩ ፡ መላእክት ፡ አንዱን ፡ ከሰው ፡ የተወለደ ፡ የዚህን ፡ የክርስቶስን፡ ነገር ፡ ጠየቅሁት ፤

፳፪ ፤ ወእቤሎ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ወእምአይቴ ፡ ይከውን ፡ ውእቱ ፡ ወበ እንተ ፡ ምንት ፡ ምስለ ፡ ርእሰ፡ መዋዕል ፡ የሐውር ፤

ይህ ፡ ማነው ? ከወዴትስ ፡ ተገኘ ? ከብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ስለምን ፡ ተቀመጠ ፡ ብዬ ፡ ጠየ ቅሁት ፡

፳፫ ፤ ወአውሥአኒ ፡ ወይቤለኒ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፡ ዘሎቱ ፡ ኮነ ፡ ጽድቅ ፤

ትንቢት ፡ የተነገረለት ፡ ከሰው ፡ የተወለደው ፡ ክርስቶስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።

ወጽድቅ ፡ ምስሌሁ ፡ ኃደረ ፤

ትንቢት ፡ የተፈጸመለት ፤ አን ድም ፡ ትንቢት ፡ የተነገረለት ፡ የተፈጸመለት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለኝ ።

አንድም ፡ ወጽድቅ ፡ ምስሌሁ ፤ የባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፤

ወኵሎ ፡ መዛግብተ ፡ ዘኅቡዕ ፡ ውእቱ ፡ ይከሥት ፡ እስመ ፡ እግዚአ መናፍስት ፡ ኪያሁ ፡ ኀረየ ፤

አብ ፡ ክርስቶስን ፡ መርጧልና ፤ ክርስቶስ፡ የተወሐደው ፡ ሥጋን መርጧልና ፤ እርሱ ፡ የተሠወ ረውን ፡ ምሥጢር ፡ ይገልጣል፤

፳፬ ፤ ወዘክፍሉ ፡ ኵሎ ፡ ሞአ ፤

ዕድሉ ፡ ሥጋ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፤

በርትዕ ፡ ለዓለም ፤

ለዘለዓለም ፡ በሚገባ ፡ ነው ፤ ተዋሕዶ ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ወዘኵሎ ፡ ሞዐ ፡ ይላል ፤ ኃጣውእን ፡ አጋንትን ፡ ድል ፡ ያደረገ ፡ በለበ ሰው ፡ ሥጋ ፡ ነው ፤

፳፭ ፤ ወዝንቱ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ዘርኢከ ፡ ያነሥኦሙ ፡ ለነገሥት ወለኃያላን ፡ እምስካባቲሆሙ ፡ ወለ ጽኑዓን ፡ እመናብርቲሆሙ ፤

ይህ ፡ ያየኸው ፡ ወልደ ፡ አዳም ኃያላኑን ፡ ከሹመታቸው ፡ ይሽ ራቸዋል ፤ ጽኑዓኑንም ፡ ከዙ ፋናቸው ፡ ያወርዳቸዋል ፤

፷፮ ፤ ወይፈትሕ : ልንማተ : ጽኑ ዓን ፤

የኃያላኑን : ሥልጣን : ሲያሳል ፈው : አየሁ : ሲል : ነው ፤ ልንማት : ጽኑዓን : ቢል ፤ ጽኑ ጽኑውን : ሥልጣን : ያሳልፋል ፤

ወያደቅቅ : አስናነ : ኃጥአን ፤

የኃጥአንንም : ጥርሶች : ይሰብ ራል : ማለት : ሥልጣናቸውን : ያጠፋል ፤

ወይገፈትዖሙ : ለነገሥት : እመና ብርቲሆሙ : ወእመንግሥቶሙ ፤

ነገሥታቱንም : ከዙፋናቸው : እየገለበጠ : ይጥላቸዋል ፤ ከመ ንግሥታቸውም : ይለያቸዋል ፤

እስመ : ኢያሌዕልዎ : ወኢይሴብሕዎ : ወኢይገንዩ ፤

አክብረው : አላመሰገኑትምና : ለእርሱም : አይገዙለትም ፤

ወእምአይቴ : ተውህበት : ሎሙ : መንግሥት ፤

መንግሥት : ከወዴትም : እንደ ተገኘች : አውቀው : ከእርሱም : እንደተገኘች : አውቀው : አይገዙ ለትም ፤ መንግሥት : ከወዴት : አገኘን : ይመስላቸዋል?

፷፯ ፤ ወገጸ : ጽኑዓን : ይገፈትዕ : ወይመልዖሙ : ኃፍረተ : ወጽልመተ : ይከውኖሙ : ማኅደሪሆሙ ፤

የጸኑ : ሰዎች : ሰውነትን : ያጠፋል ፤ ኃፍረትንም : ይመላቸ ዋል ፤ ማደሪያቸው : ጨለማ : ይሆንባቸዋል ፤

፷፰ ፤ ወዕፄያት : ይከውንዎሙ : ምስካቢሆሙ ፤

መኝታቸው : ትሎች : ይሆናሉ : አለ ፤ ዕፄሁ : ዘኢይነውም : ወእሳቱ : ዘኢይጠፍዕ : ያለው : ነው ፤

ወኢይሴፈዉ : ከመ : ይትነሥኡ : እምስካባቲሆሙ ፤

ከመቃብርም : ይነሡ : ዘንድ : ተስፋ : አላደረጉም ፤ ትንሣኤያ ቸው : ዘለኃሣር : ስለሆነ : ነው : እንጂ : መነሣትስ : ይነሣሉ ፤ አንድም : ከገሃነም : እንወጣለን : ብለው : ተስፋ : አያደርጉም ፤

እስመ : ኢያሌዕሉ : ስሞ : ለእግዚአ መናፍስት ፤

የመላእክትን : ጌታ : ስም : ከፍ : ከፍ : አላደረጉምና ፤

፷፱ ፤ ወእሙንቱ : ኮኑ : እለ : ይኴ ንኑ : ከዋክብተ : ሰማይ ፤

እነሱም : ጻድቃንን : የሚበድሉ ሁነዋልና ፤

ወያሌዕሉ : እደዊሆሙ : ውስተ : ልዑል ፤

ቃላቸውንም : ወደ : እግዚ አብሔር : ያደርሳሉና ፤

ወይከይዱ : ዲበ : የብስ ፤

ይህችንም : ዓለም : ይገዛሉና ፤

ወየኃድሩ : ውስቴታ ፤

በዚህችም : ዓለም : በተድላ : በደስታ : ጸንተው : ይኖራሉና ፤

፸ ፤ ወኵሉ : ተግባሮሙ : ዓመፃ : ያሬእዩ ፤

# ምዕራፍ ፲፫

፩ ፤ ወበውእቱ ፡ መካን ፡ ርኢኩ ፡ ነቅዓ ፡ ጽድቅ ፡ ዘኢይትኋለቍ ፤
ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ የጽድቅ ፡ ምንጭን ፡ አየሁ፤ አንድም ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ የምሥጢር ፡ መገኛ ፡ ኦሪትን ፡ አየሁ ፤ አንድም ፡ ወንጌልን ፡ አየሁ፤

፪ ፤ ወበዐውዱ ፡ የአውድዎ ፡ ብዙኃን ፡ አንቅዕተ ፡ ጥበብ ፤
ጥበብን ፡ የሚገልጹ ፡ አንቅዕት (ምንጮች)፡ ዙሪያውን ፡ ይከቡታል ፤ አንድም፡ኦሪትን ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፤ ወንጌልን ፡ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳት ፡ ይከቡታል ፤

ወኵሎሙ ፡ ጽሙኣን ፡ ሰትዩ ፡ እምኔሁ፤
ከትምህርት ፡ ከዕውቀት ፡ የተጠሙ ፡ ሰዎች ፡ ከእርሱ ፡ ይጠጣሉ ፤

ወይትመልኡ ፡ ጥበበ ፤
ጥበቡንም ፡ ይማሩታል ፤

፫ ፤ ወማኀደሪሆሙ ፡ ምስለ ፡ ጻድቃን ፡ ወቅዱሳን ወኅሩያን ፤
ብሉያትን፡ ሐዲሳትን ፡ ተምረው ከግብር ፡ ገብተው ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ መኖሪያቸው ፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ ነው ፤

፬ ፤ ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ተጸውዐ ፡ ዝኩ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፡ በኀበ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፤
በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ዘንድ ፡ ከሰው ፡ የተወለደ ፡ ወልደ ፡ ሰብእ ፡ ክርስቶስ ተጠራ ፤

፭ ፤ ወስሙ ፡ መቅድመ ፡ ርእሰ ፡ መዋዕል ፤
መቅድም ፡ ርእስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፤ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ተባለ ፤ አንድም ፡ ከስድስቱ ፡ ዕለታት ፡ ከምትቀድም ፡ ከዕለተ እሑድ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ተባለ ፤

፮ ፤ ወዘእንበለ ፡ ይትፈጠር ፡ ፀሐይ ፡ ወተአምር ፤
ከፀሐይ ፡ ከጨረቃ ፡ አስቀድሞ፡ የነበረ ፡ ተባለ ፤ ወትእምርት ፡ ለብሔር፩ ፤ እንዲል ፤

ወዘእንበለ ፡ ይትገበሩ ፡ ከዋክብተ ፡ ሰማይ ፡ ተጸውአ ፡ ስሙ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፤
ፀሐይ ፡ ሳይፈጠር ፡ ጨረቃም ፡ ሳይፈጠር ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላእክትም ፡ ሳይፈጠሩ ፡ በመላእክት ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ስሙ ፡ ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ተባለ ፤

---

፩፤ ሲራ ፡ ፵ ፡ ፮

ከእግሩ ፡ በታች ፡ የወደቁ ፡ ድኩ
ማን ፡ ይሆናሉ ።
፱ ። ወይከውን ፡ በእማንቱ ፡ መዋ
ዕል ኢይድኅኑ ፡ ኢበወርቅ ፡ ወኢበ
ብሩር ።
በእነዚያም ፡ ወራቶች ፡ እንደዚህ፡
ይሆናል ። ወርቅ ፡ ብርም ፡
ሰጥተው ፡ ቢሆን ፡ አይድኑም ፡
ወኢይክሉ ፡ ድኂነ ፡ ወጕይየ ።
ሸሽቶ፡ መዳን ፡ አይቻላቸውም፤
፲ ። ወኢይከውን ፡ ሐዒን ፡ ለፀብዕ፤
በዕለተ ፡ ሞት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡
ብረት ፡ ጦር ፣ ጎራዴ ፡ ሁኖ ፡
አያድንም ።
ወኢልብስ ፡ ለድርዓ ፡ እንግድአ ፡
ልብስም ፡ ለደረት ፡ ጥሩር ፡
አይሆንም ፡ ኢይበቍዕ ፡ ብርት ።
አንድም ፡ ለልብስ ፡ ሲል ፡ ነው ።
ጽሩርም ፡ (ጥሩርም) ፡ ልብስ ፡
ሁኖ አያድንም ።
ወኢናዕክ ፡ ኢይበቍዕ ።
ዕይር ፡ ቅልቅል ፡ አያድንም ፣
ወኢይትኄለቍ ።
ካለ ፡ ከሌለ ፡ አይቈጠርም ፣
ወዓረር ፡ ኢይትፈቀድ ፡ አላ ፡ ኵሎሙ ፡
ይትከሐዱ ።
ዓረርም ፡ በዕለተ ፡ ሞት ፡ አይ
ሻም ፡ አይፈለግም ፡ ሁሉም ፡
ይካዳሉ ፡ እንጂ ።
፲፩ ። ወይትኀጐሉ ፡ ሀለዎሙ ፡ እም
ገጸ ፡ ምድር ፡ ሶበ ፡ ያስተርኢ ፡
ኅሩይ ፡ በቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለእግዚአ ፡
መናፍስት ።

ኅሩይ ፡ ክርስቶስ ፡ በመላእክት
ጌታ ፡ በአብ ፡ ፊት ፡ በተገለጸ ፡
ጊዜ ፣ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ጠላቶቹ ፡
ኃጥአን ፡ በዕለተ ፡ ሞት ፣ በዕለተ ፡
ምጽአት ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አላ
ቸው ።
፲፪ ። ወበህየ ፡ ርእያ ፡ አእይንትየ
ቈላ ፡ ዕሙቀ ፡ ወርኅው ፡ አፉሁ ፣
ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ባየሁ ፡
ጊዜ ፡ ጥልቅ ፡ ቈላን ፡ አየሁ ፡
አፉም ፡ የተከፈተ ፡ ነው ፣
መቃብርን ፡ አየሁ ።
፲፫ ። ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ የኃድሩ ፡
ዲበ ፡ የብስ ፡ ወባሕር ፡ ወደሰያት ፡
አምኃ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፣ በደሴትና ፡
በባሕርም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡
እጅ ፡ መንሻ ።
ወአስትዓ፤
ገጸ ፡ በረከት ፣
ወጋዳ ፡ ያመጽኡ ፡ሎቱ ፣
ጊብር ፡ ያቀርባሉ ፤ ወንድሙን፣
እናቱን ፣ አባቱን ፡ የማይቀብር፡
የለምና ።
ወዝክቱሰ፡ ቈላ ፡ ዕሙቅ፡ ኢይመልዕ፤
ይህም ፡ ጥልቅ ፡ ቈላ ፡ አይሞ
ላም ፡ ማለት ፡ ሞት ፡ ቢገድል
መቃብር ፡ ቢቀበል ፣ በቃኝ ፡
አይልም ።
፲፬ ። ወጌጋየ ፡እደዊሆሙ ፡ ይገብሩ፤
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሞትና ፡ መቃ
ብር ፡ ሳለ ፡ እጃቸው ፡ ኃጢአ
ትን ፡ ይሠራል ።

ፋርስ ፡ ትውጣቸዋለች ፤ አን ድም ፡ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፤ እለ ፡ ብልጣሶር፡ኃጢአት ፡ በሚ ሠሩበት ፣ ጣዖት ፡ በሚያመል ኩበት ፡ ወራት ፡ ይሰበሰባሉ ፤ አንድም ፡ ወይወድዩ ፤ የፋርስ፡ የሜዶንን ሰዎች ፡ ለማምጣት ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመልሳሉ ፤ የሐውስምሙ ፤ ነገሥታቱን ፡ ኑ ፡ ማርኩን ፡ ብለው፡ ያነዋውጧቸዋል ፤ ኃጢ አት ፡ መሥራት ፣ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ማርኩን ፡ ማለት ፡ ነውና ፤ መንፈስ ፡ ሀውክ ፤ በእለብልጣሶር ፡ ልቡና ፡ ኃጢ አት ፡ ሥሩ ፡ የሚል ፡ ሁከት ፡ ያለበት ፡ ልቡና፡ያድርባቸዋል ፤

ወየሀውክምሙ ፤

ነገሥታቱን ፡ ማርኩን ፡ ብለው፡ ያውኳቸዋል ፤ ኃጢአት ፡ መሥ ራት ፣ ጣዖት ፡ ማምለክ ፣ ማር ኩን ፡ ማለት ፡ ነውና ፤ አንድም፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ በሚጠፉ በት ፡ እስራኤልን ፡ በበደሉበት፡ ወራት ፡ እለቂሮስ ፡ እለ፡ ዳር ዮስ ፡ ይሰባሰባሉ ፤ ወይወድዩ ፣ የፋርስን ፡ የሜዶንን ፡ ጦር ፡ ለመ ሰብሰብ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመልሳሉ ፤ ወየሐው ስምሙ ፤ ያነዋውጧቸዋል ፤ ያለ ፡ ፈቃዳቸው ፡ እርዱን ፡ ብለው ፤ አንድም ፡ እለ ፡ ብልጣሶር ፡ ያነ ዋውጧቸዋል ፡ በሞት፣ መንፈስ፡ ሀውክ ፤ ውጋ ፡ ውጋ ፡ የሚል፡ የሁከት፡ ልቡና ፡ ያድርባቸዋል፤ ወየሀውክምሙ ፤ ያለ፡ ልባቸው፡ እርዱን ፡ ብለው ፡ ያውኳቸዋል ፤ አንድም ፡ እለብልጦሶርን ፡ በሞት ፡ ያነዋውጧቸዋል ፤ ከመ ፡ አንበሳ ፡ ወከመ ፡ አዝእብት ፣ እለ ፡ ቂሮስ ፡ እለ ፡ ዳርዮስ ፡ እንደ ፡ ተራበ ፡ ጅብ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ በማስፈራት ፡ ይመጣሉ ፤ ወየዐርጉ ፣ ወደፋርስ፡ ይዘምታሉ ፣ ወይከይድዋ ፡ ለም ድር ፣ እሳቸውን ፡ የመረጡ ፡ የባቢሎን ፡ ምድር ፤ አንድም ፡ እሳቸው ፡ የመረጧቸው ፡ የባቢ ሎንን ፡ ምድር ፤ አንድም ፡ ኅሩያን ፡ ዚአሁ ፡ ቢል ፣ ጌታ ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ መርጧቸው ፡ የነበሩ ፡ የባቢሎንን ፡ ምድር ፡ እለቂሮስ ፡ እለዳርዮስ ፡ ይረግጧ ታል ፤ ምክያደ ፣ የእነቂሮስ ፡ የእነዳርዮስ ፡ መገሳገሻ ፡ ትሆና ለች ፤ ወሀገረ ፡ ጻድቃን፡ዚአየ ፣ የትሩፋን ፡ ሀገር ፡ ለፈረሶቻቸው ፡ መሰናከል ፡ ትሆናለች ፤ ወያን ሥኡ ፡ ቀትለ ፣ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ እርስ በርሳቸው ፡ ይዋ ጋሉ ፤ አንድም ፡ የባቢሎንና ፡ የፋርስ ፡ ሰዎች ፡ ይዋጋሉ ፤ ሌላውን ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ይወጉ ፡ ነበረና ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አለ ፤ ወትጸንዕ ፣ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ያንዱ ፡ ሥልጣን ፡

፰፰ ፡ ወዝንቱ : ውእቱ : ተፍጻሜተ : ካልእ : ምሳሌ ፡
የሁለተኛው : ነገር : መጨረሻ ይህ : ነው ፡

፰፱ ፡ ወአንገዝኩ : እብል : ሣልሰ : ምሳሌ : በእንተ : ጻድቃን : ወበእንተ ኅሩያን ፨
የሕጋውያንን : የደናግልን : ነገር : ሦስተኛ : ነገር : እናገር : ዘንድ : ጀመርሁ ፡

፺ ፡ ብፁዓን : አንትሙ : ጻድቃን : ወኅሩያን : እስመ : ሰቡሕ : ክፍልክሙ ፡
ዕድላችሁ : መንግሥተ : ሰማያት የበራ ፨ የተመሰገነ ፨ ነውና ፡ እናንተ : ጻድቃን : የተመረጣችሁ : የተደነቃችሁ : ናችሁ ፡

፺፩ ፡ ወይከውኑ : ጻድቃን : በብርሃነ : ፀሐይ ፡
ሕጋውያን : ከክርስቶስ : በሚያገኙት : ብርሃን : ያበራሉ ፡ ወኅሩያን : በብርሃነ : ሕይወት : ዘለዓለም ፡
ደናግልም : ከመንፈስ : ቅዱስ : ባገኙት : ብርሃን : ያበራሉ ፡ ማካፈል : አይደለም ፡

፺፪ ፡ ወማኅለቅት : አልቦቱ : ለመዋዕለ : ሕይወቶሙ ፡ ወለቅዱሳን : ኊልቈ : መዋዕል : አልቦሙ ፨
በሕይወት : ለሚኖሩ : አነዋወር : ፍጻሜ : የለውም ፨ በቅዱሳንም : የተቈጠረ : ዘመን : የላቸውም ፡

፺፫ ፡ ወየኀሥሥዎ : ለብርሃን ፡
ከክርስቶስ : የሚያገኙትን : ዕውቀት : ይፈልጋሉ ፡
ወይረክቡ : ጽድቀ : በኀበ : እግዚአ : መናፍስት ፨
በመላእክት : ጌታም : ዘንድ : ጸጋውን : ክብሩን : ያገኛሉ ፡

፺፬ ፡ ወሰላም : ለጻድቃን : ይከውን : በኀበ : እግዚአ : መናፍስት ፡
ይህን : ዓለም : ከሚገዛ : ከሚያሳልፍ : አዙሮ : ካሳየኝ : ከመላእክት : ጌታ : ዘንድ : ፍቅር : አንድነት : ጸጋ : ክብር : አላቸው ፡

፺፭ ፡ ወእምድኅረዝ : ይትበሀል : ለቅዱሳን : ከመ : ይኅሥሡ : በሰማይ : ኅቡዓተ : ጽድቅ : ክፍለ : ሃይማኖት ፡
ከዚህ : በኋላ ፨ የሃይማኖት : ዕድል : የሚሆን : እውነተኛ : የተሠወረ : ምሥጢርን : በሰማይ : ይፈልጉ : ዘንድ : በእኔ : ቃል : ለቅዱሳን : በመጻሕፍት : ይነገራል ፡

፺፮ ፡ እስመ : ሠረቀ : ከመ : ፀሐይ : ዲበ : የብስ ፡
ዕውቀት : እንደ : ፀሐይ : ወጥቷልና ፡
ወጽልመት : ኀለፈ ፡
ድንቍርና አልፏልና ፡
ወብርሃን : ዘኢይትኌለቍ : ይከውን ፡
ስፍር : ቍጥር : የሌለው : ዕውቀት : ይሰጣል ፡

፴፰ ፤ ወይወድቁ ፡ ኵሎሙ ፡ ነገ
ሥት ፡ አዚዛን ፡ ወልዑላን ፤
ነገሥታቱ ፣ ኃያላኑ ፡ ሁሉ ፡
በዚያች ፡ ቀን ፡ በፊቱ ፡ ይወድ
ቃሉ ፤

ወእለ ፡ ይመልክዋ ፡ ለየብስ ፣
ይህችን ፡ ዓለም ፡ የሚገዟት ፡
ሰዎችም ፡ ሁሉ ፣

በቅድሜሁ ፡ በገጾሙ ፡ ወይሰግዱ ፤
እግር ፡ ከግንባር ፡ አድርገው ፡
በፊቱ ፡ ወድቀው ፡ ይሰግዳሉ ፤

፴፱ ፤ ወይሴፈውዎ ፡ ለዝኩ ፡ ወልደ ፡
ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወያስተበቍዕዎ ፤
ያን ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ ክርስ
ቶስንም ፡ ተስፋ ፡ ያደርጉታል ፡
ይማለዱታል ፤

ወይስእሉ ፡ ምሕረተ ፡ እምኀቤሁ ፣
ከእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታን ፡
ይለምናሉ ፤

፵ ፤ ወያጌጕእሙ ፡ እንከ ፡ ውእቱ ፡
እግዚእ ፡ መናፍስት ፡ ከመ ፡ ያፍጥኑ፡
ወይፃኡ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፤
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ የመላእክት
ጌታ፡ ከፊቱ ፡ ፈጥነው ፡ ይወጡ
ዘንድ ፡ ያስቸኩላቸዋል ፤

፵፩ ፤ ወገጾሙ ፡ ይመልዕ ፡ ኃፍረተ ፤
ፊታቸውም ፡ ኀፍረትን ፡ ይመላል ፤

ወጽልመተ ፡ ይትዌሰክ ፡ ገጾሙ ፤
ፊታቸው ፡ በጨለማ ፡ ላይ ፡
ጨለማን ፡ ይጨምራል ፤

፵፪ ፤ ወይትሜጠውዎሙ ፡ መላእ
ክተ ፡ መቅሠፍት ፤
ለመቅሰፍት ፡ የታዘዙ ፡ መላእ
ክት ፡ ይቀበሏቸዋል ፤

ከመ ፡ ይትፈደዩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘገፍ
ዕዎሙ ፡ ለደቂቁ ፡ ወለኅሩያኒ ፡
ዚአሁ ፤

ልጆች ፡ ደናግልን ፣ ሕጋውያ
ንን ፡ ከበደሏቸው ፡ ፍዳ ፡ ይከ
ፍሏቸው ፡ ዘንድ ፤ አንድም
በእነርሱ ፡ ፍዳ ፡ ያጸኑባቸው ፡
ዘንድ ፤

፵፫ ፤ ወይከውኑ ፡ አርአያ ፡ ለኅሩያ
ኒሁ ፤

ኃጥአን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለጻድ
ቃን ፡ አብነት ፡ ይሆናሉ ፤ እነ
ሱን ፡ ሲያጠፏቸው ፡ አይተው፡
ጻድቃን ፡ ይመለሳሉና ፤

፵፬ ፤ ወጻድቃነ ፡ ዚአሁ ፡ በሙ ፡
ይትፌሥሑ ፤

ወዳጆቹ ፡ በእነርሱ ፡ ጥፋት ፡
ደስ፡ ይላቸዋል ፡ አለ ፤ በኃጥአን ፡
ጥፋት ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ ሁነው ፡
አይደለም ፤ ፍርዱ ፡ ስላልቀረ ፡
ነው ፤

እስመ ፡ መዓቱ ፡ ለእግዚእ ፡ መናፍ
ስት ፡ ዲቤሆሙ ፡ ተአርፍ ፤
የመላእክት ፡ ጌታ ፡ ቍጣው ፡
በእነርሱ ፡ ትጸናለች ፤

ወመጥባሕቱ ፡ ለእግዚእ ፡ መናፍስት ፤
ትሰክር ፡ እምኔሆሙ ፤

ምን ፡ አየሁ ፤ አንድም ፡ ርኢ
ክዋ ፡ ለይእቲ ፡ ቈላ ፡ ወለተ
ሀውኮ ፡ ማየት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡
ተሀውኮ ፡ ማያትንም ፡ አየሁ ፤
፮ ፤ ወዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ሶበ ፡ ተገብረ ፡
እምውእቱ ፡ ነጠብጣበ ፡ እሳት ፤
ይህ ፡ ሁሉ ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡
ከነጠብጣበ ፡ እሳቱ ፡ የተነሣ ፤
ወሀውኮሙ ፡ ዘየሀውኮሙ ፤
ከሚያውካቸው ፡ ሁከት ፡ የተ
ነሣ ፤
በውእቱ ፡ መካን ፡ ተወልደ ፡ ጼና ፡ ተይ፣
በዚህ ፡ ቦታ ፡ የድኝ ፡ ሽታ ፡
ተወለደ ፣ ትኩሱ ፡ ውሀ ፡ እንደ
ድኝ ፡ ይሸታልና ፤
ወተነብረ ፡ ምስለ ፡ እልኩ ፡ ማያት ፤
ከሰማይ ፡ የወረደው ፡ ውሀ ፡
ከምድር ፡ ካለው ፡ ውሀ ፡ ጋር
ተባበረ ፡ አንድ ፡ ሆነ ፤
፯ ፤ ወይእቲ ፡ ቈላ ፡ እንተ ፡ መላ
እክት ፡ እለ ፡ አስሐቱ ፡ ትነድድ ፡
መትሕተ ፡ ይእቲ ፡ ምድር ፤
ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያሳቱ ፡ ደቂቀ ፡
ሴት ፡ የተጋዙበት ፡ ቦታ ፡ ከም
ድር ፡ በታች ፡ ትነዳለች ፤
፰ ፤ ወእንተ ፡ ቈላተ ፡ ዚአሃ ፡
አፍላገ ፡ እሳት ፡ ይወጽኡ ፤
በቈላነቷም ፡ የእሳት ፡ ፈሳሽ ፡
ይፈስሳል ፤ የሥጋው ፡ መከራ ፡
ከነፍስ ፡ ያደርሳልና ፤
በኀበ ፡ እለ ፡ ይትኴነኑ ፡ እልክቱ ፡
መላእክት ፡ እለ ፡ አስሐትዎሙ ፡
ለእለ ፡ የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ የብስ ፤

ደቂቀ ፡ ሴት ፡ በተጋዙበት ፡ ቦታ ፡
የእሳት ፡ ፈሳሽ ፡ ይፈስሳል ፤
አንድም ፡ እነዚያ ፡ ደቂቀ ፡ ሴት ፡
በሚኰነኑበት ፡ ቦታ ፡ ወደቈላ
ዎች ፡ የእሳት ፡ ፈሳሾች ፡ ይፈ
ስሳሉ ፤
፱ ፤ ወይከውኑ ፡ እልክቱ ፡ ማያት ፡
በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ለነገሥት ፡
ወለአዚዛን ፡ ወለልዑላን ፡ ወለእለ ፡
የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ የብስ ፡ ለፈውሰ ፡
ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ወለኵነኔ ፡ መንፈስ ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ እሊህ ፡ ማያት
ለነገሥታቱ ፣ ለጸኑ ፣ ለኃያላኑ ፡
ለመድኃኒተ ፡ ሥጋ ፡ ለመድኃኒተ ፡
ነፍስ ፣ ለኵነኔ ፡ ሥጋ ፡ ለኵነኔ
ነፍስ ፡ ይሆናሉ ፤ አንድም ፡ ማየ ፡
አይኅ ፡ ይመጣብናል ፡ ብለው ፣
በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸን
ተው ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ለሠሩ ፣
ለመድኃኒተ ፡ ሥጋ ፡ ለመድኃኒተ ፡
ነፍስ ፤ ማየ ፡ አይህ ፡ አይመጣ
ብንም ፡ ብለው ፡ ኃጢአት ፡ ለሚ
ሠሩ ፣ ጣዖት ፡ ለሚያመልኩ ፡
ለኵነኔ ፡ ሥጋ ፣ ለኵነኔ ፡ ነፍስ ፡
ይሆናሉ ፤ አንድም ፡ ሰብእ ፡ ትካ
ትን ፡ ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ብለው ፡
በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸን
ተው ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ለሚ
ሠሩ ፣ ለመድኃኒተ ፡ ሥጋ ፡ ለመ
ድኃኒተ ፡ ነፍስ ፤ ሰብእ ፡ ትካትን ፡
ያገኘ ፡ ያገኘናል ፡ ሳይሉ ፡ ኃጢ

ይህችን ፡ ምሥጢረ ፡ ኃጣውእን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሰው ሁሉ ፡ አስተምረዋልና ፤

፲ ፤ ወነዋ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለእልክቱ ፡ መላእክት ፤
የደቂቀ ፡ ሴት ፡ አለቆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ አስማቲሆሙ ፤
የአጋንንት ፡ አለቆች ፡ ስማቸው ይህ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ሁለት፡ አርስት ፡ ነው ፤ ለሁለቱም ፡ ያመጣል ፤

፲፩ ፤ ቀዳማዊ ፡ ዚአሆሙ ፡ ስምያዛ ፤ (ስማዝያ)
ለአንዱ ፡ አርእስት ፡ አመጣ ፤ የአለቃው፡ አለቃ ፡መጀመሪያው አለቃ ፡ ስምያዛ ፡ (ስማዝያ) ፡ ነው ፤

ወካልኡ ፡ አርስጢቁፋ ፤
ሁለተኛው ፡ አርስጢቁፋ ፡ ይባላል ፤

ወሣልሱ ፡ አርሚን ፤
ሦስተኛውም ፡ አርሚን ፡ ነው ፡

ወራብዑ ፡ ኮከብኤል ፤
አራተኛውም ፡ ኮከብኤል ፡ ይባላል ፤

፲፪ ፤ ወሐምሱ ፡ ጡርኤል ፤
አምስተኛውም ፡ ጡርኤል ፡ ነው ፤

ወሳድሱ ፡ ሩምያል ፤
ስድስተኛውም ፡ ሩምያል ፡ ነው ፤

ወሳብዑ ፡ ዳንኤል ፤
ሰባተኛው ፡ ዳንኤል ፡ ይባላል ፤

ወሳምን ፡ ኑቃኤል ፤
ስምንተኛውም፡ኑቃኤል፡ ነው ፤

ወታስዕ ፡ በራቅኤል ፤
ዘጠነኛውም ፡ በራቅኤል፡ ነው፤

ወዐሥር ፡ አዛዝኤል ፤
ዐሥረኛው ፡ አዛዝኤል ፡ ነው፤

ዐሥር ፡ ወአሐዱ ፡ አርማሮስ ፤
ዐሥራ ፡ አንደኛውም ፡ አርማሮስ ፡ ነው ፤

ዐሥር ፡ ወካልዕ ፡ በጠርያል ፤
አሥራ ፡ ሁለተኛውም ፡ በጠርያል ፡ ነው ፤

፲፫ ፤ ዐሥር ፡ ወሣልስ ፡ በሰላኤል፤
አሥራ ፡ ሦስተኛውም ፡ በሰላኤል ፡ ነው ፤

ዐሥር ፡ ወራብዕ ፡ አናንያል ፤
አሥራ ፡ አራተኛውም ፡ አናንኤል ፡ ይባላል ፤

ዐሥር ፡ ወሐምስ ፡ ጡርያል ፤
አሥራ ፡ አምስተኛውም ፡ ጡርያል ፡ ይባላል ፡

ዐሥር ፡ ወሳድስ ፡ ሲማሲፒኤል ፤
አሥራ ፡ ስድስተኛውም ፡ ሲማሲፒኤል ፡ ይባላል ፤

፲፬ ፤ ዐሥር ፡ ወሳብዕ ፡ ይትርኤል፤
አሥራ ፡ ሰባተኛውም ፡ ይትርኤል ፡ ይባላል ፤

ዐሥር ፡ ወሳምን ፡ ቱማኤል ፤
አሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ቱማኤል ፡ ነው ፤

አጋንንት ፡ ከዚህ ፡ ስም ፡ የተነሣ፡ ይርዱ ይንቀጠቀጡ ፡ ዘንድ ፤ በመሐላም ጊዜ ፡ ይጠሩት ፡ ዘንድ ፡ ያንን የተሠወረ ፡ ስሙን ፡ ግለጥላቸው ፡ አለው ፤

፬ ፤ ወዝንቱ ፡ ኃይሉ ፡ ለዝ ፡ መሐላ፤
የዚህ ፡ ስም ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ነው ፤

እስመ ፡ ኃያል ፡ ውእቱ ፡ ወጽኑዕ ፤
ኃይለኛ ፡ ነውና ፡ የጸናም ፡ ነውና ፤

፭ ፤ ወአንበሮ ፡ ለዝኩ ፡ መሐላ፤
አካዕ ፡ በእዴሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፤
ይህን፡ ስም ፡ አካዕ ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እጅ ፡ ጻፈው ፤ ስመ መሐላ ፡ ዘጸበጠ[፩] ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቃል እንዲነገር ፡ አደረገው ፤ አካዕ ፡ ማለት ፡ አምላክ ፡ ከሃሊ ማለት ፡ ነው ፤

ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ኅቡዓቲሁ ፡ ለዝ መሐላ ፤
የዚህም ፡ ስም ፡ የተሰወሩ ፡ ምሥጢሮቹ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፤

ወጽንዑ ፡ በመሐላሁ ፤
ፍጥረታቱም ፡ ሁሉ ፡ በመሐላው ፡ ጸኑ ፤

፮ ፤ ወሰማይ ፡ ተሰቅለ ፤
ሰማይ ፡ በዚህ ፡ ቃል፡ ጸና ፤

ዘእንበለ ፡ ይትፈጠር ፤ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፤
ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ዓለም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖር፡ ቃል ፡ ሰማይ ፡ ተፈጠረ ፤

ወቦቱ ፡ ምድር ፡ ተሣረረት ፡ ዲበ ፡ ማይ፤
ምድርም ፡ በእርሱ ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ ተፈጠረች ፤

፯ ፤ ወእምነ ፡ ኅቡዓተ ፡ አድባር ፡ ይመጽኡ ፡ ላህያት ፡ ማያት ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፤
ጽሩያን ፡ ማያት ፡ ሲል ፡ነው ፤ ከኅቡዓን ፡ አድባር ፡ ከተራሮችም ፡ ውስጥ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ የጣፈጡ ፡ ውሃዎች ፡ ጽሩያን ፡ ማያት ፡ ይፈስሳሉ ፤ አንድም ፡ ለሕያዋን ፡ ቢል ፡ በነፍስ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ሕያዋን ፡ ለሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ይፈስሳሉ ፤

፰ ፤ ወበውእቱ ፡ መሐላ ፡ ተፈጥረት ፡ ባሕር ፤
በዚህም ፡ ስም ፡ ባሕር ፡ ተፈጠረች ፤

ወመሠረታ ፤
ከታች ፡ ነፋስ ፤ ቀጥሎ ፡ እሳት ፤ ቀጥሎ ፡ ውሃ ፤ በዚያ ፡ ላይ ፡ መሬት ፡ አድርጎ ፡ በዚህ ፡ ቃል ተፈጠረች ፤

---

፩:- ደራሲ

ከዚያም ፡ ቤት ፡ ሚካኤልና ፡
ገብርኤል ፣ ሩፋኤልና ፡ ፋኑኤ
ልም ፣ ብዙ ፡ የሆኑ ፣ ቁጥር ፣
የሌላቸው ፡ ሌሎች ፡ የከበሩ ፡
መላእክትም ፡ ወጡ ፤

፴፪ ፤ ወምስሌሆሙ ፡ ርእሰ ፡ መዋዕል ፤
ብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ጌታ ፡ ከእነ
ርሱ ፡ ጋራ ፡ አለ ።
ወርእሱ ፡ ከመ ፡ ፀምር ፡ ጸዓዳ ፤
ራሱም ፡ እንደ ፡ ብዝት ፡ ነጭ
ነው ፤
ወንጹሕ ፤
ንጹሐ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፤
ወልብሱ ፡ ዘኢይተረጐም ፤
ባሕርዩ ፡ የማይመረመር፡ ነው ፤

፴፫ ፤ ወወደቁ ፡ በገጽየ ፡ ወኵሉ ፡
ሥጋየ ፡ ተመስወ ፤
እኔም ፡ በግምባሬ ፡ ፍግም ፡ ብዬ፡
ወደቅሁ ፣ ሥጋዬም ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ ሰም ፡ ቀለጠ ፤
ወመንፈስየ ፡ ተወለጠ ፤
አዕምሮዬም ፡ ተለወጠ ፤

፴፬ ፤ ወጸራኅኩ ፡ በቃል ፡ ዓቢይ ፡
በመንፈስ ፡ ኃይል ፤
ዕውቀትን ፡ በያዘ ፡ ልቡና ፣ ዕው
ቀትን ፡ በሚገልጽ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ አሰምቼ ፡ ተናገርኩ ፡
ወባረኩ ፡ ወሰባሕኩ ፡ ወአልዐልኩ ፤
ፈጽሜም ፡ እርሱን ፡ አመሰገንሁ
ስሙንም ፡ አከበርኩ ፤

፴፭ ፤ ወእላ ፡ በረከታት ፡ እለ ፡
ወፅአ ፡ እምነ ፡ አፉየ ፡ ኮና ፡ ሥሙ
ራተ ፡ በቅድመ ፡ ዝኩ ፡ ርእሰ ፡
መዋዕል ፤
ከአፌ ፡ የወጡ ፡ እሊህ ፡ ምስጋ
ናዎች ፥ ጸሎታት ፡ የተወደዱ ፡
ሆኑ ፤

፴፮ ፤ ወመጽአ ፡ ውእቱ ፡ ርእሰ ፡
መዋዕል ፡ ምስለ ፡ ሚካኤል ፡ ወገ
ብርኤል ፣ ሩፋኤል ፡ ወፋኑኤል ፣
ወአእላፍ ፡ ወትእልፊተ ፡ አእላፋት ፡
መላእክት ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ኍልቍ ፤
ጌታ ፡ ሚካኤልና ፡ ገብርኤልን ፣
ሩፋኤልና ፡ ፋኑኤልን ፣ ሌሎች
የብዙ ፡ ብዙ ፡ የሚሆኑ ፡ መላ
እክትን፡ አስከትሎ ፡ መጣ ፤

፴፯ ፤ ወመጽአ ፡ ኀቤየ ፡ ውእቱ ፡
መልአክ ፡ ወበቃሉ ፡ አምኃኒ ፤
ተናገረኒ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ያም ፡
መልአክ ፡ ወደእኔ ፡ መጣ ፣ በቃ
ሉም ፡ ተናገረኝ ፤

፴፰ ፤ ወይቤለኒ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡
ወልደ፡ ብእሲ፡ ዘተወለድከ ፡ ለጽድቅ፤
ለበጎ ፡ ሥራ ፡ የተወለድህ ፡ የባለ
አእምሮ ፡ ልጅ ፡ አንተ ፡ ነህ ፣
ወጽድቅ ፡ ላዕሌከ ፡ ኀደረ ፤
ረድኤት ፡ ክብር ፡ በላይህ ፡ ላይ ፡
አደረ ፤
ወጽድቁ ፡ ለርእሰ ፡ መዋዕል ፡
ኢየኀድገከ ፤
የብሉየ ፡ መዋዕል ፡ ክብሩ ፡
አይለይህም ፤ ረድኤቱ ፡ አይር
ቅህም ፤

፶፱ ፤ ወይቤለኒ ፡ ይጼውዕ ፡ ለከ ሰላመ ፡ በስሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ዘይከውን ፤

በስሙ ፡ ላመኑ ፡ ለጻድቃን ፡ የሚ ሰጠው ፡ ክብር ፡ ይሰጥሃል ፤

እስመ ፡ እምህየ ፡ ወፅአ ፡ ሰላም ፡ እምፍጥረተ ፡ ዓለም ፤

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ፍቅር ፡ ክብር ፡ አንድነት ፡ ከጌታ ፡ ተገኝቷልና ፤

፷ ፤ ወከመዝ ፡ ይከውን ፡ ለከ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፤

እንደዚሁም ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ሁሉም ፡ ይደረግልሃል ፤

ወኵሉ ፡ ይከውን ፡ ወየሐውር ፡ ዲበ ፍናትከ ፤

ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሥርዓትህ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤

እንዘ ፡ ጽድቅ ፡ ኢየኀድገከ ፡ ለዓለም ፤

ለዘለዓለሙ ፡ ረድኤት ፡ ሳይርቅህ ፡ ክብር ፡ ሳይለይህ ፤

፷፩ ፤ ወምስሌከ ፡ ይከውን ፡ ማኅደ ሪሆሙ ፤ ወምስሌከ ፡ ክፍሎሙ ፤

የጻድቃን ፡ ማደሪያዎች ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ይሆናል ፤

ወእምኔከ ፡ ኢይትሌለዩ ፡ ለዓለም ፡ ወለ ዓለመ ፡ ዓለም ፤

ለዘለዓለሙም ፡ ካንተ ፡ አይለዩም ፤

ወከመዝ ፡ ይከውን ፡ ኑኃ ፡ መዋዕል ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመ ሕያው ፤

ከዚያም ፡ ከአዳም ፡ ልጅ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ይሰጣ ቸዋል ።

፷፪ ፤ ወሰላም ፡ ይከውን ፡ ለጻድቃን ፡ ወፍኖቱ ፡ ርቱዕ ፡ ለጻድቃን ፡ በስመ ፡ እግዚአ ፡ መናፍስት ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፤

ለወዳጆቹ ፡ ለጻድቃን ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይደረግላቸዋል ፤ ሕጉም ፡ በመላእክት ፡ ስም ፡ ላመኑ ፡ ለሕ ጋውያን ፡ ለዘላለሙ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ አለ ።

## ምዕራፍ ፷፩
### ጉባኤ

፩ ፤ መጽሐፈ ፡ ሚጠተ ፡ ብርሃናተ ፡ ሰማይ ፤

በሰማይ ፡ የሚመላለሱ ፡ የብርሃ ናትን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ መጽ ሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

፪ ፤ ፩ዱ ፡ ፩ዱ ዘከመ ፡ ሀለዉ ፡ በበሕዘቢሆሙ ፤

አንዱም ፡ አንዱም ፡ በየወገና ቸው ፡ እንዳሉ ፡ መጠን ፤ የፀ ሐይ ፤ የጨረቃ ፤ አካሔዳቸውን ፡ ሥርዓታቸውን ፡ የሚናገር ፡ መጽ ሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

፩ዱ ፩ዱ ፡ በበሥልጣኖሙ ፤

አንዱም ፡ አንዱም ፡ በየምግብ ናቸው ፡ የሚመግቡ ፤

ወበበዘመኖሙ ፤

በየዘመናቸው ፡ የሚመግቡ ፡

፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ በበስሞሙ ፤

አንዱም ፡ አንዱም ፡ በየስማቸው ፡ የሚጠሩ ፤

ወሙላዳቲሆሙ ፤

ሥርቀታቲሆሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤

መውጣታቸውን ፡ የሚናገር ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ተንባላት ፡ ይበድላሉ ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ብርሃናት ፡ ይትቀነዩ ፡ በጽድቅ ፡ በምንባረ ፡ ዓለም ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አነዋወር ፡ በእውነት ፡ ያበራሉና ፡ ምንም ፡ ቢያበሩ ፡ ሰዎች ፡ የሉም ፡ ብለው ፡ ይበድላሉ ፤

፳ ፤ ፩ዱ ፡ በቀዳሚት ፡ ኖኅት ፤
አንዱ ፡ በመጀመሪያው ፡ መስኮት ፡ በጥቅምት ፤ በኅዳር ፤ በታኅሣሥ ፡ ኖኅት ፤

ወ፩ዱ ፡ በሣልስት ፡ ኖኅት ፤
አንዱ ፡ በሦስተኛው ፡ መስኮት ፡ በጥር ፤ በየካቲት ፤ በመጋቢት ፤

ወ፩ዱ ፡ በራብዕት ፡ ኖኅት ፤
አንዱ ፡ በአራተኛው ፡ መስኮት ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ በመስከረም ፤

ወ፩ዱ ፡ በሣድስት ፡ ኖኅት ፤
አንዱ፡ በስድስተኛው ፡ መስኮት ፡ በሚያዝያ ፡ በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ ኖኅት ፡ (መስኮት) ፡ ይወጣል ፤

ወይትፌጸም ፡ ጥንቃቄ ፡ ዓለም፤
ኍልቈ ፡ ዓለም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖርበትን ፡ ቀን ፡ ጠንቅቆ ፡ ቢቆጥሩት ፤

በበሠለስቱ ፡ ምእት ፡ ወስሳ ፡ ወረቡዕ ምንባረ ፡ ዓለም ፤
ይህ ፡ ዓለም ፡ ጸንቶ ፡ በሚኖርበት ፡ በ፫፻፷፬ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ የዓለም ፡ ቁጥር ፡ ይፈጸማል ፤

፳፩ ፤ እስመ ፡ ለትእምርት ፤
ለጳጕሜን ፤
ወለአዝማን ፤
ለ፬ቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፤
ወለዓመታት ፤
ለ፫፻፷፬ ፡ ቀን ፤

ወለመዋዕል ፡ አርአየኒ ፡ ዑርኤል ፡ መልአክ ፤
ለ፬ቱ ፡ ዕለታት ፡ ተሹሚልና ፡ መልአኩ ፡ ዑራኤል ፡ አሳየኝ ፤ አንድም ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኮከብ ተሹሚልና ፡ ዑራኤል ፡ አሳየኝ ፤

ዘአንበሮ ፡ እግዚእ ፡ ስብሐት ፡ ዘለዓለም ፤
ዘሤሞ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ የሾመው ፤

ዲበ ፡ ኵሉሙ ፡ ብርሃናተ ፡ ሰማይ፤
በሰማይ ፡ ባሉ ፡ በፀሐይ ፡ በጨረቃ ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፤

፳፪ ፤ ወበዓለም ፡ ከመ ፡ ይምልኩ ፡ በገጸ ፡ ሰማይ ፤
በሰማይ ፤ በምድር ፤ ያበሩ ፡ ዘንድ ፤

ወይትረአዩ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዓለምም ፡ ይመግቡ ፡ ዘንድ ፤

፳፫ ፤ ወይኩኑ ፡ መራሕያነ ፡ ለመዓልት ፡ ወለሌሊት ፡ ፀሐይ ፡ ወወርኅ ፡ ወከዋክብት ፤

# ምዕራፍ ፸፮

፩ ፡ ወበአጽናፈ ፡ ምድር ፡ ርኢኩ ፡ ዐሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ ኆዋኀወ ፡ ርኅዋተ ፡ ለኵሉሙ ፡ ነፋሳት ፡ እለ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳት ፡

እንደ ፡ አርእስት ፡ ተናግሮት ፡ ነበርና ፡ አመጣው ፡ ለነፋሶች ፡ ሁሉ ፡ መውጫ ፡ መግቢያ ፡ የሚሆኑ ፡ ነፋሶች ፡ ከእነርሱ ፡ የሚወጡባቸው ፡ የተከፈቱ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መስኮቶችንም በምድር ፡ ዳርቻ ፡ አየሁ ፡

፪ ፡ ወይነፍሑ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡

በዚህም ፡ ዓለም ፡ ይነፍሳሉ ፡

ወ፫ቱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ርኅዋት ፡ በገጸ ሰማይ ፡

፫ቱ ፡ በምሥራቅ ፡ የተከፈቱ ፡ ናቸው ፡

ወሠለስቱ ፡ በምዕራብ ፡ ወሠለስቱ ፡ በየማነ ፡ ሰማይ ፡

ሦስቱ ፡ በምዕራብ ፡ ሦስቱ ፡ በሰሜን ፡ የተከፈቱ ፡ ናቸው ፡

ወሠለስቱ ፡ በጸጋም ፡

ሦስቱ በደቡብ ፡ የተከፈቱ ፡ ናቸው ፡

፫ ፡ ወ፫ቱ ፡ ቀዳምያት ፡

በመጀመሪያ ፡ ያዩኋቸው ፡፫ቱ ፡

እለ ፡ መንገለ ፡ ጽባሕ ፡

በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡

ወ፫ቱ ፡ እለ ፡ መንገለ ፡ መስዕ ፡

ሦስቱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡

ወ፫ቱ ፡ በድኅር ፡ እለ ፡ በጸጋም ፡ እለ መንገለ ፡ አዜብ ፡

ወደ ፡ አዜብ ፡ በኩል ፡ የሚሆን በግራ ፡ ባለ ፡ በኋላ ፡ በደቡብ ፡ ናቸው ፡

ወ፫ቱ ፡ በዓረብ ፡

፫ቱ፡ በምዕራብ ፡ ናቸው ፡

፬ ፡ ወበ፬ቱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይወፅኡ ፡ ነፋሳተ ፡ በረከት ፡ ወሰላም ፡

በእሊህ ፡ በ፬ቱ ፡ መስኮቶች ፡ የፍቅርና ፡ የበረከት ፡ ነፋሳት ፡ ይወጣሉ ፡

ወእምእልኩ ፡ ሰመንቱ ፡ ይወጽኡ ፡ ነፋሳተ ፡ መቅሠፍት ፡

ከነዚያም ፡ ከስምንቱ ፡ መስኮቶች ፡ መቅሠፍት ፡ የሚያመጡ ነፋሶች ፡ ይወጣሉ ፡

፭ ፡ ወሶበ ፡ ይትፌነዉ ፡ ይደመስስዋ ፡ ለኵላ ፡ ምድር ፡

ወደዚህም ፡ ዓለም ፡ በተላኩ ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፉታል ፡

ወለማይ ፡ ዘዲቤሃ ፡

በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ፍጥረታትን ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡

## ምዕራፍ ፳፯
## ጉባኤ

፩ ፤ ወበመዋዕለ ፡ ኀጥአን ፡ ክራማት ፡ የኀጽራ ፤
በኀጥአን ፡ ወራት ፡ የኃጥአን ፡ ኃጢአት ፡ በበዛበት ፡ ወራት ፡ ክራማት ፡ (ዘመኖች) ያጥራሉ ፤
በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ የሚዘንመው በሐምሌ ፡በነሐሴ ፡ ይዘንማል ፤
ወዘርአ ፡ ዚአሆሙ ፡ ይከውን ፡ ደኃ ራዌ ፡ በምድሮሙ ፡ ወበሙፋሮሙ ፤
በሀገራቸው ፡ በመሰማሪያቸው ፡ ዘራቸው ፡ ወደኋላ ፡ ይሆናል ፤
በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ የሚዘራው ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ ይዘራል ፤
፪ ፤ ወኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ይትመየየጥ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይለዋወጣል ፤
ወኢያስተርኢ ፡ በዘመኑ ፤
በግንቦት ፤ በሰኔ ፡ የሚበቅለው ፡ በሰኔ ፡ በግንቦት ፡ በቅሎ ፤ በሐ ምሌ ፤ በነሐሴ ፡ የሚበቅለው ፡ በሐምሌ ፡ በነሐሴ ፡ በቅሎ ፡ አይታይም ፤
ወዝናም ፡ ይትከላእ ፡ ወሰማይ ፡ ታቀውም ፤
ሰማይ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ከመስጠት ፡ ትከለክ ላለች ፡ ትገታለች ፤

፫ ፤ ወበውእቱ ፡ አዝማን ፡ ፍሬ ፡ ምድር ፡ ይከውን ፡ ደኃራዌ ፤
በነሐሴ ፤ በመስከረም ፡ የሚደር ሰው ፡ በጥቅምት ፤ በኅዳር ፡ ይደ ርሳል ፤
ወኢይበቍል ፡ በዘመኑ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀ ይትከላዕ ፡ በዘመነ ፡ ዚአሁ ፤
በዘመኑም ፡ አይበቅልም ፡ የእን ጨቱም ፡ ፍሬ ፡ ከማፍራት ፡ ይከ ለከላል ፤
፬ ፤ ወወርኅ ፡ ይዌልጥ ፡ ሥርዓቶ፤
ጨረቃም ፡ ሥርዓቱን ፡ ይለው ጣል ፤
ወኢይትረአይ ፡ በዘመነ ፡ ዚአሁ ፤
በክረምት ፡ በደመና ፡ ተሸፍኖ ፡ ሲያበራ ፡ አይታይም ፤
፭ ፤ ወበእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ይትረ አይ ፡ ሰማይ ፤
በዚያ ፡ ወራት ፡ ሰማይ ፡ ጠርቶ ፡ ይታያል ፤ የደመና ፡ ምልክት ፡ አይታይበትም ፤
ወይበጽሕ ፡ አባር ፡ በጽንፈ ፡ ሠረገ ላት ፡ ዓቢይ ፡ በምዕራብ ፤
በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለ ፡ በጽንፈ ፡ ሠረገላ ፡ ድርቅ ፡ ይመጣል ፤

ወይበርህ ፡ ፈድፋደ ፡ እምሥርዓተ ፡ ብርሃን ፤
ከበጋው ፡ ሥርዓት ፡ ይልቅ ፡ በክረምት ፡ ያበራል ፤

፮ ፤ ወይስሕቱ ፡ ብዙኃን ፡ እርእስቲሆሙ ፡ ለከዋክብተ ፡ ትእዛዝ ፤
ወይዌልጡ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የወር ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ ፡ የዘጠና ፡ አንድ ፣ የሽሕ ፡ አለቆችን ፡ የሚመሩ ፡ የወር ፡ መጋቢዎች ፤ የዕለት ፡ መጋቢዎችን ፡ የሚመሩ፡ የሽሕ ፡ አለቆች ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይለውጣሉ ፤ አንድም ፡ ሌሎች ፡ ከዋክብትን ፡ የሚመሩ ፡ የዕለት ፡ መጋቢዎች ፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይለውጣሉ ፤
ወእሉ ፡ ይመይጡ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ወግብሮሙ ፤
ከዋክብት፡ ሥርዓታቸውን ፡ ይለውጣሉ፣ ሰዎች ፡ ይህን፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ (ምልክት) ፡ እያዩ ፡ ከኀጢአት ፣ ወደ ፡ ጽድቅ ፣ ከክህደት ፣ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ይመለሳሉና ፤
ወኢይትረአዩ ፡ በአዝማኒ ፡ ዘአሆሙ፡ እለ ፡ ተአዘዙ ፡ ሎሙ ፤
በደመና ፡ ተሸፍነው ፡ ሊታዩባቸው ፡ በታዘዙላቸው ፡ አዝማናት፡ (ዘመኖች) ፡ በደመና ፡ ተሸፍነው ፡ አይታዩም ፤ አንድም ፡ ምግባር፡ ትሩፋት ፡ ሊሠሩባቸው ፡ በታዘዙላቸው ፡ አዝማን ፡ (ወራት) ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሲሠሩ ፡ አይታዩም ፤

፯ ፤ ወኵሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ከዋክብት ፡ ይትዐፀው ፡ ላዕለ ፡ ኃጥአን ፤
የከዋክብት ፡ ሥርዓታቸው ፡ በኃጥአን ፡ ይለወጣል ፤
ወሕሊናሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ዲበ ምድር ፡ ይስሕቱ ፡ ዲቤሆሙ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሕሊናቸው ፡ በከዋክብት ፡ ይስታል ፣ ከዋክብትን ፡ ያመልኳቸዋል ፤

፰ ፤ ወይትመየጡ ፡ እምኵሉ ፡ ፍናዊሆሙ ፡ ወይስሕቱ ፤
ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ አምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ይመለሳሉ ፤ ይስታሉ ፤
ወያመስልዎሙ ፡ አማልክተ ፤
ከዋክብትን ፡ አማልክት ፡ ያስመስሏቸዋል ፤

፱ ፤ ወይበዝኅ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እከይ ፡ ወመቅሠፍት ፡ ይመጽእ ፡ ዲቤሆሙ ፤
መከራ ፡ ይበዛባቸዋል ፤ ሁሉንም ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ መቅሠፍት ፡ በእነርሱ ፡ ይመጣል፤
ከመ ፡ ያኅጕሎሙ ፡ ለኵሎሙ ፤
ሁሉንም ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፤

# ምዕራፍ ፹፪

፩ ፤ ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፡ ኵሎ ፡ እሉንተ ፡ ለከ ፡ እነግር፤
አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡ እነ ዚህን ፡ ሁሉ ፡ ለአንተ ፡ እነግራ ለሁ ፤
ወጸሐፍ፡ ለከ ፡ ወኵሎ ፡ ከሠትኩ ፡ ለከ ፤
ለአንተም፡ እጽፍልሃለሁ ፤ ሁሉ ንም፡ ገለጥሁልህ ፡ አለው ፤

፪ ፤ ወወሀብኩከ ፡ መጻሕፍቲሆሙ ፡ ለእሉ ኵሎሙ ፤
የእነዚህንም ፡ ሁሉ ፡ መጽሐፎ ቻቸውን ፡ ሰጠሁህ ፤
ወዕቀብ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ ፡ መጻሕ ፍተ ፡ እዴሁ ፡ ለአቡከ ፤
እኔ ፡ አባትህ ፡ በቃሌ ፡ ያስተማ ርሁህን ፤ በእጄ ፡ የጻፍኩልህን ጠብቅ ፤
ወከመ ፡ ተሀብ ፡ ለትውልደ ፡ ዓለም ፤
ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ታስተ ምር ፡ ዘንድ ፤
ጥበበ ፡ ወሀብኩከ ፡ ለከ ፡ ወለውሉድከ ፡ ወለእለ ፡ ይከውኑ ፡ ለከ ፡ ውሉደ ፤
ለአንተ ፡ ጥበብን ፡ አስተማርኩህ፡ ካንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችህ ፡ አስተማርኩ ፤

፫ ፤ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ለውሉዶሙ ፡ ወለትውልዳት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፤
እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ ለል ጆቻቸው ፡ ያስተምሩት ፡ ዘንድ ፡ አስተማርሁ ፤
ለዛ ፡ ጥበብ ፡ ዲበ ፡ ሕሊናሆሙ ፤
ይህ ፡ ጥበብ ፡ በልቡናቸው ፡ ይጻፍ ፡ ዘንድ ፤

፬ ፤ ወኢይነውሙ ፡ እለ ፡ ይሌብዉ ፡ ወያጸምዑ ፡ በእዝኖሙ ፡ ከመ ፡ ይት መሀርዋ ፡ ለዛ ፡ ጥበብ ፤
የመምህራን ፤ የመጻሕፍትን ፡ ቃል ፡ ልብ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ አያርፉም ፡ አያንቀላፉም ፤
ወትደልዎሙ ፡ እመባልዕት ፡ ሠናያት ለእለ ፡ ይበልዑ ፤
ይህችን ፡ ጥበብ ፡ ለሚማሩ ፡ ሰዎች ፡ ከጣዐ ፡ ከግዐ ፡ ይልቅ፡ ትስማማቸዋለች ፤

፭ ፤ ብፁዓን ፡ ጻድቃን ፡ ኵሎሙ ፤
ተምረው ፤ ከግብር ፡ ገብተው ፤ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ንዑ ዳን ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ፤
ወብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ በፍኖተ ፡ ጽድቅ ፤
በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ባለ ፡ ዘመና

የሰውንም : ገንዘብ : (ከብት) :
ሁሉ : ይበላል ፤
ወይትረዐይ : ማእከለ : እልኩ :
አልሕምት ፤
በእነዚያ : ላሞች : መካከል :
ይሰማራል ፤ ከአዋልደ : ቃየል :
ጋራ : ይኖራል ፤
፲፮ ፤ ወእምዝ : ርኢኩ : አልሕ
ምተ : ዓቢያነ : ወጸሊማነ ፤
ከዚያም : በኋላ : ጥቋቁሮች :
ታላላቆችን : ላሞች : አየሁ ፤
ደቂቀ : ሴትን ፤
ወናሁ : ኵሎሙ : ወለጡ : ምዕያ
ሞሙ ፤
ሕገ : ስብሳባቸውን ፤
ወምርዓዮሙ ፤
ሥርዓታቸውን፡ለወጡ ፤
ወአጣዕዋሆሙ ፤
ልጅ : አስወለዷቸው ፤ ደቂቀ :
ሴት : አዋልደ : ቃየልን : ኃጢ
አት : አሠሯቸው ፤
፲፯ ፤ ወአኀዙ : የአወይዉ : ፩ዱ :
ምስለ : ካልኡ ፤
አንዱም : ካንዱ : ጋር : አዋ
ልደ : ቃየል : ይጮኹ :ጀመር ፤
ወካዕበ : ርኢኩ : በራእይ : ወነጸ
ርክዎ : ለሰማይ ፤
ዳግመኛም : በራእይ : ደብር :
ቅዱስን : አየሁት ፤
፲፰ ፤ ወነዋ : ርኢኩ : ከዋክብተ :
ብዙኃነ : ወወረዱ ፤

እነሆ : ብዙ : ኮከቦችን : አየሁ ፤
ወረዱም ፤ ደቂቀ : ሴት : ከደብር :
ቅዱስ ወደስምያዛ : ወረዱ ፤
ወተገድፉ : እምሰማይ : ኀበ : ዝኩ :
ኮከብ : ቀዳማዊ : ወማእከለ : እልኩ:
ጣዕዋ ፤
ወደዚያ : ወደ : መጀመሪያው :
ኮከብ : ወረዱ ፤ በእነዚያም :
ጥጆች : መካከል : ተጣሉ ፤ ወደ :
ስምያዛ : ወደ : ደቂቀ : ሴት ፤
፲፱ ፤ ወአልሕምት : ኮኑ : ምስሌ
ሆሙ : ይትረዐዩ : ማእከሎሙ ፤
ላሞችም : ከእነሱ : ጋር : በመካ
ከላቸው : የሚሠማሩ : ሆኑ ፤
ማለት : ደቂቀ : ሴት : ከአዋ
ልደ : ቃየል : ጋራ : ይኖሩ :
ጀመረ ፤
ወነጸርክዎሙ : ወርኢኩ ፤
እነሱንም : ፈጽሜ : አየኋቸው ፤
፳ ፤ ወነዋ : ኵሎሙ : አውፅኡ :
ኀፍረታቲሆሙ : ከመ : አፍራስ ፤
እነሆ : ሁሉም : እንደ : ፈረ
ሶች : ኀፍረታቸውን : አውጥ
ተው ፤
ወአኀዙ : ይዕርጉ : ዲበ : ዕጓላተ :
አልሕምት ፤
በላሞች : ጊደሮች : ላይ : ይንጠላ
ጠሉ : ጀመር ፤ ማለት : ደቂቀ :
ሴት : እንደ : አለሌ ፤ አዋልደ :
ቃየል : እንደባዝራ : ሁነው :
ይንጠላጠሉባቸው : ጀመረ ፤

ወይትወሐጡ ፡ ወይትነኰሉ ፡ በው
እቱ ፡ ማይ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም
ሁሉ ፡ ተሰብስበው ፡ እስኪሰጥሙ ፤
ተውጠውም ፡ በዚያ ፡ ውሀ ፡
እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፤
፹፫ ፤ ወውእቱ ፡ መስቀር ፡ ይጸቢ ፡
ዲበ ፡ ማይ ፤
ያም ፡ መርከብ ፡ በውሀው ፡ ላይ ፡
ይዋኝ ፡ ነበር ፤
ወኵሎሙ ፡ አልሕምት ፡ ወነጌያት ፡
ወአግማል ፡ ወአዕዱግ ፡ ተሰጥሙ ፡
ውስተ ፡ ምድር ፡ ወኵሉ ፡ እንስሳ ፤
ዝኖኖችና ፡ ላሞች ፤ አህዮችና ፡
ግመሎች፤ ከብቶችም ፡ ሁሉ ፡
በዚህ፡ ዓለም ፡ ተሰጠሙ ፤
፹፬ ፤ ወኢክህልኩ ፡ ርእዮቶሙ፤
እኔም ፡ እነርሱን ፡ ማየት ፡ አል
ቻልኩም ፤
ወእሙንቱሂ ፡ ስእኑ ፡ ወጺአ ፤
እነርሱም ፡ መውጣት ፡ ተሣና
ቸው ፤
ወተነኰሉ ፡ ወተሰጥሙ ፡ ውስተ ፡
ቀላይ ፤
በጥልቁም ፡ ባሕር ፡ ተሰጥመው፡
ጠፉ ፤
፹፭ ፤ ወካዕበ ፡ ርኢኩ ፡ በራእይ ፡
እስከ ፡ ሰሰሉ ፡ እልኩ ፡ አስራብ ፡
እምዝኩ ፡ ናሕስ ፡ ልዑል ፤

እሊህ ፡ መሸረቦች ፡ /ሻሻቴዎች/ ፡
ከጠፈር ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡
ደርሼ ፡ አየሁ ፤
ወንቅዐተ ፡ ምድር ፡ ዐረየ ፤
በምድር ፡ የተከፈተው ፡ ተካከለ ፡
ተገጠመ ፤
፹፮ ፤ ወማዕምቃት ፡ ካልአት ፡ ተፈ
ትሑ ፡ ወአኀዘ ፡ ማይ ፡ ይረድ ፡
ውስቴቶሙ ፡ እስከ ፡ ተከሥተ ፡
ምድር ፤
ሌሎች ፡ ሰባ ፡ ጕድጓዶችም ፡
ተከፍተው ፡ ውሀው ፡ ወደታች ፡
ይወርድ ፡ ጀመር ፤
፹፯ ፤ ወውእቱ ፡ መስቀር ፡ ነበረ ፡
ውስተ ፡ ምድር ፤
ያ ፡ መርከብም ፡ በምድር ፡ ላይ
ተቀመጠ ፡ (አራራት) ፤
ወተግሕሠት ፡ ጽልመት ፡ ወኮነ ፡
ብርሃን ፤
ጨለማዪቱ ፡ ራቀች ፤ ብርሃንም፡
ሆነ ፤
፹፰ ፤ ወውእቱ ፡ ላሕም ፡ ፀዓዳ ፡
ዘኮነ ፡ ብእሴ ፡ ወፅአ ፡ እምዝኩ ፡
መስቀር ፤
ባለ ፡ አእምሮ ፡ የሆነ ፡ ያም ፡
ኖኅ ፡ ከዚያ ፡ ከመርከቡ ፡ ወጣ ፤
ወሠለስቱ፡አልሕምት፡ ምስሌሁ ፤
ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ወጡ ፤

ቈናጽል ፤
አማሌቃውያን ፤
ወግሔያት ፤
ያልታወቁ ፡ አሕዛብ ፤
፫ ፤ ወሐንዘር ፤
አነር ፤ (ያልታወቁ ፡ አሕዛብ) ፤
ወሲሲት ፡ ወአንሥርት ፤
ውዳቂ ፡ አንሣ ፡ አሞራ ፤
ወአውስት ፤
ዘማች ፡ አሞራ ፤
ወሆባይ ፤
አንጭት ፡ አሞራ ፤
ወፎንቃስ ፤
ጉሬዛ ፤ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ ያልታ
ወቁ ፡ አሕዛብ ፡ ናቸው ፤
ወቋዓት ፤
ሮማውያን ፡ ሁሉ ፡ ከእነዚህ ፡ ተወለዱ ፤
፬ ፤ ወተወልደ ፡ ማእከሎሙ ፡ ላሕም ፀዓዳ ፤
በመካከላቸው ፡ ላም ፡ ተወለደ ፡ አለ ፤ ባለአእምሮ ፡ አብርሃም ፡ በመካከላቸው ፡ ተወለደ ፤
ወአኀዙ ፡ ይትናሰኩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ፡ካልኡ ፤
አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋር ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጣሉ ፡ ጀመር ፤
፭ ፤ ወዝኩ ፡ ላሕም ፡ ፀዓዳ ፡ ዘተ
ወልደ ፡ ማእከሎሙ ፡ ወለደ ፡ አድገ ፡ ገዳም ፤
በመካከላቸው ፡ የተወለደው ፡ ያ ፡ ነጭ ፡ ላም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አድግ ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ በመካከላ
ቸውም ፡ የተወለደ ፡ ባለአእምሮ ፡ የሚሆን ፡ አብርሃም ፡ እስማኤልን፡ ወለደ ፤
ወላሕመ ፡ ፀዓዳ ፡ ምስሌሁ ፤
እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ነጭ ፡ ላም ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ እንደርሱም ፡ ያለ ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ፤
፮ ፤ ወበዝኀ ፡ አዕዱገ ፡ ገዳም ፤
አዕዱገ ፡ ገዳም ፡ በዙ ፡ አለ ፤ የእስማኤል ፡ ልጆች ፡ በዙ ፤ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትን ፡ ወልዷልና ፤
ወውእቱ ፡ ላሕም ፡ ዘተወልደ ፡ እምኔሁ ፡ ወለደ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ጸሊመ ፤
ከእርሱ ፡ የተወለደ ፡ ያ ፡ ላም ፡ ጥቁር ፡ እርያን ፡ ወለደ ፤ ከአብር
ሃም ፡ የተወለደ ፡ ይስሐቅ ፤ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ኤሳውን ፡ ወለደ ፤
ወበግዐ ፡ ፀዓዳ ፤
ነጭ ፡ በግንም ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ፤
፯ ፤ ወውእቱ ፡ ሐራውያ ፡ ገዳም ፡ ወለደ ፡ ብዙኃነ ፡ አሕርወ ፤
ያም ፡ እርያ ፡ ብዙ ፡ እርያዎችን ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ ኤሳው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ መሳፍንትን ፡ ወለደ ፤ የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤

ወውእቱ ፡ በግዕ ፡ ወለደ ፡ አሠርተ ፡ ወክልኤተ ፡ አባግዐ ።

ያም ፡ በግ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ በጎችን ፡ ወለደ ፡ አለ ፤ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ያዕቆብ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱን ፡ ነገደ ፡ እሥራኤል ፡ ወለደ ።

፰ ። ወሶበ ፡ ልሕቁ ፡ እሙንቱ ፡ እሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አባግዕ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ መጠውዎ ፡ ለአዕዱግ ፡ ገዳም ።

እኒያ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ በጎችም፡ ካደጉ ፡ በኋላ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱን ፡ ለአዕዱግ ፡ ገዳም ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡት ፡ አለ ፤ እነዚህ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ እስራኤልም ፡ ካደጉ ፡ በኋላ ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ዮሴፍን ፡ ለእስማኤላውያን ፡ ለ፳ብር ፡ ሸጡት ።

፱ ። ወእልኩ ፡ አዕዱግ ፡ ገዳም ፡ ካዕበ ፡ መጠውዎ ፡ ለዝኩ ፡ በግዕ ፡ ለአዝእብት ።

እኒያ ፡ አዕዱግ ፡ ገዳም ፡ ያን ፡ በግ ፡ ለአዝብዕት ፡ ሰጡት ፡ አለ ፤ እነዚህም ፡ እስማኤላውያን ፡ ዳግመኛ ፡ ዮሴፍን ፡ ለግብፃውያን ፡ ለ፴ ፡ ብር ፡ ሸጡት ።

ወልህቀ ፡ ዝኩ ፡ በግዕ ፡ ማዕከለ ፡ አዝእብት ።

ያም ፡ በግ ፡ በአዝብዕት ፡ መካከል ፡ አደገ ፡ አለ ፤ ዮሴፍ ፡ በግብጻውያን ፡ መካከል ፡ አደገ ።

፲ ። ወእግዚእ ፡ አምጽአሙ ፡ ለእሥርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ አባግዕ ፡ ከመ ፡ ይኅድሩ ፡ ምስሌሁ ።

ጌታው ፡ ዐሥራ ፡ አንዱን ፡ በጎች፡ ከእርሱ ፡ አብረው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አመጣቸው ፡ አለ ፤ አሥራ ፡ አንዱ ፡ ወንድሞቹን ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ አመጣቸው ።

ወይትረዐዩ ፡ ምስሌሁ ፡ ማዕከለ ፡ አዝዕብት ።

በግብጻውያንም ፡ መካከል ፡ ከሱ ጋር ፡ አብረው ፡ ይሠማሩ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ አመጣቸው ።

፲፩ ። ወበዝኁ ፡ ወኮኑ ፡ መራዕየ ፡ ብዙኃነ ፡ ዘአባግዕ ፤

እነርሱም ፡ ብዙ ፡ የበጎች ፡ መንጋ፡ ሆኑ ፡ አለ ፤ እነዚህ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ልጅነት ፤ ወገንነት ፡ ያላቸው ፡ ብዙ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ።

ወወጠኑ ፡ አዝዕብት ፡ እንዘ ፡ ያፈርህዎሙ ፡ ወአጠወቅዎሙ ፡ እስከ ፡ የኃልቁ ፡ ደቂቆሙ ።

ግብጻውያን ፡ ጡቡን ፡ እያሠሩ ፡ እያስረገጡ ፡ ኖራ ፡ እያስወቀጡ ፡

ወካልእ : በግዕ : ተራከቦ : ለውእቱ :
በግዕ : ወሖረ : ምስሌሁ ፤
አሮን : ከራምሴ ፤ ከምድያም :
ሙሴ ፤ ተራከቡ ፤ በፈቃደ :
እግዚአብሔር : ተገናኝተው ፤
፲፯ ፤ ወቦኡ : ክልኤሆሙ : ኅቡረ :
ውስተ : ማኅበሮሙ : ለእልክቱ : አዝ
እብት ፤
ሁለቱም : ወደግብፃውያን : ሸንጎ:
(አደባባይ) : ገብተው :
ወተናገርዎሙ ፤
ተናገሯቸው ።
፲፰ ፤ ወአስምዑ : ዲቤሆሙ : ከመ :
እምይእዜ : ኢይግሥሥዎሙ : ለአባ
ግዕ ፤
እንግዲህ : ወዲህ : እስራኤልን
እንዳይነኳቸው : ሁለቱም : ሁሉ:
አንድ : ሁነው : አዳኙባቸው ፤
፲፱ ፤ ወእምኔሁ : ርኢክዎሙ :
ለአዝእብት : ወእፎ : ፀንዑ : ፈድፋደ :
ዲበ : አባግዕ : በኵሉ : ኃይሎሙ ፤
ከዚያም : በኋላ : ግብፃውያን :
ከሠራዊቶቻቸው : ጋራ : በእስራ
ኤል : ላይ : ፈጽመው : መከራ :
እንዳጸኑባቸው : አየሁ ፤
፳ ፤ ወጸርሑ : አባግዕ : ወእግዚ
እሙ : መጽአ : ኀቤሆሙ : ለአባግዕ ፤
እስራኤልም : ጮሁ ፤ ጌታቸውም :
ወደ : እስራኤል : መጥቶ ፤
ወአኃዘ : ይዝብጦሙ : ለእልኩ :
አዝዕብት ፤
እነዚህ : ግብጻውያንን : በዘጠኝ:
መቅሠፍት : በ፲ኛ : ሞተ : በኵር:
ያጠፋቸው : ጀመር ፤
፳፩ ፤ ወአዝዕብት : አኀዙ : የአወይዉ፤
ግብፃውያንም:ይጮሁ :ጀመር ፤
ወአባግዕ : አርመሙ ፤
እስራኤል : ግን : ዝም : አሉ ፤
ወእምሶቤሃ : ኢጸርሑ ፤
ከዚያም : ቀን : ጀምሮ : አል
ጮሁም ፤
ወርኢክዎሙ : ለአባግዕ : እስከ :
ወጽኡ : እምአዝዕብት ፤
ከግብፃውያንም : ተለይተው : እስ
ኪወጡ : ድረስ : ደርሼ : እስራኤ
ልን : አየኋቸው ፤
፳፪ ፤ ወለአዝእብት : ተጸለሉ : አዕይ
ንቲሆሙ ፤
የግብጻውያንም : ዓይነ : ልቡና
ቸው : በድንቁርና : ተሸፈነ ፤
ወወፅኡ : እንዘ : ይተልውዎሙ :
ለአባግዕ : እልኩ : አዝእብት : በኵሉ :
ኃይሎሙ ፤
እኒህም : ግብፃውያን : ከሠራዊ
ቶቻቸው : ሁሉ : ጋራ : እስራ
ኤልን : ተከተሏቸው ፤
፳፫ ፤ ወእግዚእሙ : ለአባግዕ : ሖረ :
ምስሌሆሙ : እንዘ : ይመርሖሙ ፤

የእስራኤልም : ጌታ : እየመራ
ቸው : ከእነርሱ : ጋራ : ሄደ ፤
ወዙሉሙ : አባግዒሁ : ተሰውዎ ፤
እስራኤልም : ሁሉ ፣ ቀን :
ዓምደ: ደመናውን ፣ ሌሊት :
ዓምደ : እሳቱን : እያዩ :
ይከተሉት : ነበር ፤
ወገጹ : ስቡሕ ፤
ፊቱ : ብሩህ : ነው ፤
ወግሩም : ራእዩ : ወክቡር ፣
በባሕርይ : ክብሩ : የከበረ : ነው ፣
ያየዋልና : ስቡሕ : ክቡር : ግሩም :
አለ ፤
፳፬ ፤ ወአዝእብትስ : አኀዙ : ይት
ልውዎሙ : ለእልኩ : አባግዕ : እስከ
ተራከብዎሙ : በአሐቲ : አይገ :
ማይ ፤
ግብፃውያን : ግን : በአንዲት : ኤር
ትራ : በተጠራቀመች : ውሀ : እስ
ኪገናኟቸው : ድረስ : እኒህ : እስ
ራኤልን : ይከተሏቸው : ጀመር ፤
፳፭ ፤ ወውእቱ : አይገ : ማይ
ተሰጠ ፣
ያም : የተጠራቀመ : ውሀ : ከሦ
ስት : ከአራት : ተከፈለ ፤
ወቆመ : ማይ : እምዝየ : ወእምዝየ
በቅድመ : ገጾሙ ፤
ውሀውም : ግራ : ቀኝ : ተከፍሎ
በፊታቸው : ጸና ፤
ወእግዚአሙ : ለአባግዕ : ይመርሖሙ ፣
የእስራኤልም : ጌታ : ይመራ
ቸው : ነበር ፤
ወቆመ : ማእከሌሆሙ : ወማእከለ :
አዝዕብት ፤
በግብጻውያንና : በእስራኤል :
ፊት : ይሔድ : የነበረው : ደመና:
እስራኤል : ግብጻውያንን : አይ
ተው : ቢፈሩ : ደመናውን : መልሶ:
ከመካከላቸው : ጋርዶታልና ፤
፳፮ ፤ ወዓዲሆሙ : እልኩ : አዝእ
ብት : ኢርእይዎሙ : ለአባግዕ ፤
ዳግመኛ : ግብጻውያን : ፳ኤልን
አላዩዋቸውም ፤
ወሖሩ : ማእከለ : ዝኩ : አይገ:
ማይ ፤
በዚህ : በተጠራቀመውም : ውሃ
መካከል : ሄዱ ፤
፳፯ ፤ ወአዝእብት : ተለውዎሙ :
ለአባግዕ ፤
ግብፃውያንም : እስራኤልን :
ተከተሏቸው ፤
ወሮጹ : ድኅሬሆሙ : እልኩቱ : አዝ
እብት : በዝኩ : አይገ : ማይ ፤
ያገራችን : ውሀ : ፳ኤልን : ያላሰ
ጠመች : እኛን : ታስጥማለችን :
ብለው : ወደ : ውሀው : ሮጡ ፤
፳፰ ፤ ወሶበ : ርእይዎ : ለእግዚአሙ :
ለአባግዕ : ገብኡ : ከመ : ይጕየዩ :
እምቅድመ : ገጹ ፤

ኵሉ ፡ አሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምኔክሙ ፡
እምይእዜ ፡ ይርዐይዎሙ ፡ ለአባግዕ ፤
ከእናንተ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ከዛሬ ፡
ጀምሮ ፡ እስራኤልን ፡ ይጠብቋ
ቸው ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፡ አለ ፤
ወኵሎ ፡ ዘእኤዝዘክሙ ፡ አነ ፡ ግበሩ ፤
እኔም ፡ የማዝዛችሁን ፡ ሁሉ ፡
አድርጉ ፡ አላቸው ፤

፫ ፤ ወእሜጥወክሙ ፡ አነ ፡ በጐ
ልቍ ፤
ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፤ አንድም ፡
ሕዝቡን ፡ በቍጥር ፡ እሰጣ
ችኋለሁ ፤
ወእነግረክሙ ፡ ዘይትኀጐል ፡ እምኔ
ሆሙ ፤
ከነርሱም ፡ የሚጠፋውን ፡ እኔ ፡
እነግራችኋለሁ ፤
ወኪያሆሙ ፡ አኀጕሉ ፤
እነርሱንም ፡ አጥፉ ፤
ወመጠወ ፡ ሎሙ ፡ እልክተ ፡ አባግዐ ፤
እነዚህ ፡ እስራኤልንም ፡ ጠብቁ
ብሎ ፡ ሰጣቸው ፤

፬ ፤ ወለካልዕ ፡ ፀውዖ ፤
ቅዱስ ፡ ሚካኤልን ፡ ጌታ ፡ ጠራው ፤
ከሰው ፡ በግብርም ፡ በባሕርይም ፡
ልዩ ፡ ነውና ፡ ካልዕ ፡ አለው ፤
ወይቤሎ ፡ ለቡ ፡ ወርኢ ፡ ኵሎ ፡
ዘይገብሩ ፡ ኖሎት ፡ ዲበ ፡ እሉ ፡
አባግዕ ፤
በእኒህ ፡ እስራኤል ፡ ላይ ፡
መምህራኑ ፡ የሚያደርጉትን ፡
ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ አይተህ ፡ ልብ
አድርገው ፡ አለው ፤
እስመ ፡ ያኀጕሉ ፡ እምውስቴቶሙ ፡
ፈድፋደ ፡ እምዘአዘዝክዎሙ ፤
ካዘዝኋቸው ፡ ወጥተው ፤ አንድም ፡
ካዘዝኋቸው ፡ አትርፈው ፡ መም
ህራኑን ፡ ነገሥታቱን ፡ ከሕዝቡ ፡
ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ይልቅ ፡ አጥ
ፍተዋልና ፤

፭ ፤ ወኵሎ ፡ ጽጋበ ፡ ወኀጕለ ፡
ዘይትገበር ፡ በኖሎት ፡ ጸሐፍ ፤
የሚደረገውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡
በነገሥታቱ ፡ በመምህራኑ ፡ ዕዳ
ይሆናል ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፤
ሚመጠነ ፡ የኃጕልዎሙ ፡ በትእዛዝየ ፤
አዝዣቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ያጠ
ፏቸው ፡ እንደሆን ፤
ወሚመጠነ ፡ የኀጕሉ ፡ በርእሶሙ ፡
ሳላዝዛቸው ፡ ምን ፡ ያህል ፡
በራሳቸው ፡ ያጠፉ ፡ እንደሆን ፤

፮ ፤ ወኵሎ ፡ ኀጕሎሙ ፡ ለለአሐዱ ፡
አሐዱ ፡ ኖላዊ ፡ ጸሐፍ ፡ ዲቤሆሙ ፤
አንዱም ፡ አንዱም ፡ ንጉሥ ፡
የሚያጠፉትን ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡
በእነሱ ፡ ላይ ፡ ጻፈው ፤
ወበኍልቍ ፡ አንብብ ፡ በቅድሜየ ፤
በፊቴም ፡ በቍጥር ፡ አንብብ ፤
ወሚመጠነ ፡ የኀጕሉ ፤
ምን ፡ ያህል ፡ ያጠፏቸው ፡
እንደሆነ ፤

ወነበረ ፡ ዲቤሁ ፡ እግዚአ ፡ አባግዕ ፤
ጌታ ፡ በረድኤት ፡ ተቀመጠባት ፤
አንድም ፡ በንጽሕና ፤ በድንግልና ፡
በተዘጋጀች ፡ ክብርት ፡ በሆነች ፡
በእመቤታችን ፡ በማሕፀነ ፡ ማር
ያም ፡ ሲዘጋጅ ፡ አየሁ ፤ ወነበረ ፡
ጌታ ፡ አደረ ፤ አንድም ፡ በማዕ
ከለ ፡ ምድር ፤ በቀራንዮ ፡ መስ
ቀል ፡ ሲዘጋጅ ፡ አየሁ ፤ ወነበረ ፡
ጌታ ፡ ተሰቀለበት ፤ አንድም ፡
ባማረ ፡ በተወደደ ፡ በሰማይ ፡ መካ
ከል ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ተዘ
ጋጅቶ ፡ አየሁ ፤ ወነበረ ፡ ጌታ ፡
ጻድቃንን ፡ ይዞ ፡ ተቀመጠ ፤
፪ ፤ ወነሥአ ፡ ኵሎን ፡ መጻሕፍተ ፡
ኀቱማተ ፤
የታተሙ ፡ /የተጻፉ/ ፡ መጻሕ
ፍትን ፡ ያዘ ፤
ወፈትሖን ፡ ለእማንቱ ፡ መጻሕፍት ፡
በቅድመ ፡ እግዚአ ፡ አባግዕ ፤
እነዚህን ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍ
ትን ፡ በእስራኤል ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡
ገለጻቸው ፤ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡
ብሉያት ፤ ሐዲሳት ፡ እየተነበቡ
እየተተረጐሙ ፤ በዚያ ፡ የተጻ
ፈውን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖት
የሠራ ፤ በዚያ ፡ የተጻፈውን ፡
ዋጋ ፤ በዚያ ፡ የተጻፈውን ፡
ኃጢአት ፡ የሠራ ፤ በዚያ ፡ የተ
ጻፈውን ፡ ፍዳ ፡ ይቀበላልና ፤
በዚያስ ፡ ጊዜ ፡ መነበብ ፡ መተ
ርጐም ፡ የለም ፡ ብሎ ፤ ዛሬ ፡
የሚነበበው ፤ የሚተረጐመው ፤
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ዋጋው ፡ የሚፈ
ጸም ፡ ስለሆነ ፤ አንድም ፡ ወነ
ሥአ ፤ ምሥጢራቸው ፡ የተሰ
ወረ ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያትን ፡ ገን
ዘብ ፡ አደረገ ፤ ወፈትሖን ፡ ፈጸ
ማቸው ፤ አንድም ፡ ወነሥአ ፤
ምግባረ ፡ ኃጥአንን ፤ ምግባረ ፡
ጻድቃንን ፡ መረመረ ፤ ወፈት
ሖን ፡ ገለጻቸው ፤
፫ ፤ ወጸውዖሙ ፡ እግዚእ ፡ ለእልኩ
፯ቱ ፡ ጸዓድው ፡ ቀዳማውያን ፤
ጌታ ፡ በክብር ፡ የሚበልጡ ፡ ሰባ
ቱን ፡ ሊቃነ ፡ መላእክት ፡ ጠራ
ቸው ፤
ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ያምጽኡ ፡ ቅድሜሁ
እምኮከብ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘይቀድም ፡
እምእልኩ ፡ ከዋክብት ፡ እለ ፡ ኀፍረ
ቶሙ ፡ ከመ ፡ ኀፍረተ ፡ አፍራስ ፤
ኀፍረታቸው ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡
ኀፍረት ፡ የሆነ ፡ ከእነዚህ ፡ ከደ
ቂቀ ፡ ሴት ፡ የሚቀድም ፡ ቀዳ
ማዊ ፡ ከሚሆን ፡ /መጀመሪያ/

ወኵሎሙ ፡ እንስሳ ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ የቀሩ ፡ ምዕመ
ናን ፡ እስራኤል ፡ ሁሉ ፤
ወኵሎሙ ፡ እንስሳ ፡ ዘዲበ ፡ ምድር ፡
በምድር ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ እን
ስሳ ፤ ምዕመናን ፡ አሕዛብ ፤
፲፰ ፡ ወኵሎሙ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡
ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡
ሁሉ ፤
ይወድቁ ፡ ወይሰግዱ ፡ ለእልኩ ፡
አባግዕ ፤
በዓፀደ ፡ ነፍስ ፡ ላሉ ፡ ጻድቃን ፡
ይሰግዳሉ ፤
ወያስተበቍዕዎሙ ፡ ወይሰምዕዎሙ ፡
በኵሉ ፡ ቃል ፤
ኹሉ ፡ ቃለ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የለመ
ኗቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይሰሚቸዋል ፤
፲፱ ፡ ወእምኔሁ ፡ እልክቱ ፡ ፫ቱ ፡
እለ ፡ ይለብሱ ፡ ጸዓድወ ፡ ወእለ ፡
ቀዲሙ ፡ አዕረጉኒ ፡ አኀዙኒ ፡ በእዴየ ፤
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነጭ ፡ ልብስ
የለበሱ ፡ አስቀድመውም ፡ ወደ
ሰማይ ፡ ያወጡኝ ፡ ሦስቱ ፡ መላ
እክት ፡ እጄን ፡ ያዙኝ ፤
፳ ፡ ወእዴሁ ፡ ለውእቱ ፡ ዳቤላ ፡
እንዘ ፡ ትእኀዘኒ ፡ አዕረጉኒ ፤
የዚያም ፡ የጌታ ፡ ሥልጣኑ ፡
ይዞኝ ፡ አወጡኝ ፤
ወአንበሩኒ ፡ ማዕከሎሙ ፡ ለእልኩ ፡
አባግዕ ፡ እንበለ ፡ ትኩን ፡ ኰነኔ ፤
ፍርድ ፡ ሳትደረግ ፡ አውጥተው ፡
በእኒህ ፡ ሐዋርያት ፡ መካከል ፡
አኖሩኝ ፤
፳፩ ፡ ወእልኩ ፡ አባግዕ ፡ ኵሎሙ ፡
ኮኑ ፡ ጸዓዳ ፤
እነዚያም ፡ ሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡
ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሆኑ ፤
ወጸጕረ ፡ ዚአሆሙ ፡ ዓቢይ ፡ ወንጹሕ ፤
ጸጋ ፡ ክብራቸው ፡ ደግ ፡ ነው ፤
ብዙ ፡ ነው ፤
፳፪ ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ተኀጕሉ ፤
የሞቱት ፤
ወተዘርዘሩ ፤
የተበተኑ ፤
ወኵሉ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፤
በምድረ ፡ በዳ ፡ የጠፉ ፤ አራዊት ፡
የበሏቸው ፡ ሁሉ ፤
ወኵሉ ፡ አዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ተጋብኡ
በውእቱ ፡ ቤት ፤
በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩ ፡ እስራኤ
ልም ፡ ሁሉ ፤ በዚህ ፡ ቤተ ፡ መቅ
ደስ ፤ አንድም ፡ በምጽአት ፡ ይት
ጋብኡ ፡ ይሰበሰባሉ ፤
፳፫ ፡ ወእግዚእሙ ፡ ለአባግዕ ፡ ተፈ
ሥሐ ፡ ዓቢየ ፡ ፍሥሓ ፤
የእስራኤል ፡ ገዥ ፡ እግዚአብሔ
ርም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አለው ፤
እስመ ፡ ኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ኄራነ ፤
ሁሉም ፡ ደጋግ ፡ ሆነዋልና ፤

በዕውቀት ፡ እስከ ፡ ተለወጠ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፤

ወኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ አልሕምት ፡ ፀዓድወ ፤

ሐዋርያት ፡ ያስተማሯቸው ፡ ምዕመናን ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ እስቲሆኑ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፤ አንድም ፡ ከመ ፡ ተወልደ ፣ በሐሳዊ ፡ መሲሕ፡ ጊዜ ፡ አምላክነቱን ፡ እስኪገልጽ ፡ ድረስ ፡ ደርሼ ፡ አየሁ ፣ ወአቅርንቲሁ ፣ ሄኖክ ፡ ኤልያስ ፡ ባለ አእምሮ ፡ ደጋጎች ፡ ናቸው ፣ አራዊት ፡ ምዕመናነ ፡ እሕዛብ ፤ ወአዕዋፍ ፤ እነርሱ ፡ ያስተማሯቸው ፤ ምዕመናን ፡ እስራኤል ጌታን ፡ ያመልኩታል ፤ እስከ ፡ ተወለጠ ፡ አዝማዲሆሙ ፣ የምዕመናን ፡ ወገኖቻቸው ፡ በአዕምሮ ፡ እስከ ፡ ተለወጡ ፡ ድረስ ደርሼ ፡ አየሁ ፣ ወኮኑ ፡ ጸዓድወ ፣ ሄኖክ ፡ ኤልያስ ፡ ያስተማሯቸው ፡ ምዕመናን ፡ ባለ ፡ አእምሮ ፡ ሆኑ ፤

፹፱ ፤ ወቀዳማዊ ፡ ኮነ ፡ በማእከሎሙ፡ ነገረ ፣

ይኸውም ፡ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ዲያብሎስ ፡ በጸድቃን ፡ ዘንድ ፡ ዋዛ ፣ በኃጥአን ፡ በመናፍቃን ፡ ዘንድ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ሆነ ፣

ወውእቱ ፡ ነገር ፡ ኮነ ፡ አርዌ፡ ዓቢየ፣ ሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚያስት ፡ ታላቅ ፡ አውሬ ፡ ሆነ፣

ወቦ ፡ ውስተ ፡ ርእሱ ፡ አቅርንት ፡ ዓቢያት ፡ ወጸሊማት ፣

ኃጥአን ፡ የሚሆኑ ፡ ሐሳዊ ፡ ሄኖክ ፣ ሐሳዊ ፡ ኤልያስ ፡ ለሐሳዊ ፡ መሲሕ ፡ አሉት ፤

፺ ፤ ወእግዚእ ፡ አባግዕ ፡ ተፈሥሐ ፡ ዲቤሆሙ ፣

የእስራኤል ፡ ገዢ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሐሳዊ ፡ ሄኖክ ፡ በሐሳዊ ፡ ኤልያስ ፡ ሞት ፡ ደስ ፡ አለው ፤ አንድም ፡ በምዕመናን ፡ ሞት ፡ ደስ ፡ አለው ፣ ዋጋ ፡ የሚያገኙበት ፡ ነውና ፤

ወዲበ ፡ ኵሎሙ ፡ አልሕምት ፣

በወገኖቻቸው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አለው ፤

፺፩ ፤ ወአነ ፡ ሰከብኩ ፡ ማእከሎሙ፣ እኔም ፡ በመካከላቸው ፡ በሰማዕትነት ፡ ሞትኩ ፤

ወነቃሕኩ ፡ ወርኢኩ ፡ ኵሎ ፣

ተነሥቼ ፡ ሁሉን ፡ አየሁ ፤

፺፪ ፤ ወዝንቱ ፡ ራእይ ፡ ዘርኢኩ ፡ እንዘ ፡ እሰክብ ፣

በቤተ ፡ መላልኤል ፡ ተኝቼ ፡ ሳለሁ ፡ ያየሁት ፡ ራእይ ፡ ይህ ነው ፤

ወነቃሕኩ ፡ ወባረክዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ጽድቅ፡ ወሎቱ ፡ ወሀብኩ ፡ ስብሐተ ፤

ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፣ ኵናኔ ፡ በርትዕ ፣ የሚሆን ፡ የክብር ፡

ባለቤት ፡ ጌታን ፡ ተነሥቼ ፡ አመ
ሰገንኩት ፤

፴፫ ፤ ወእምኔሁ ፡ በከይኩ ፡ ብካየ ፡
ዓቢየ ፤
ይህን ፡ ከማየቴ ፡ የተነሣ ፡ ፊጽሜ ፡
አለቀስሁ ፤
ወአንብዕየ ፡ ኢቆመ ፡ እስመ ፡ ኢክህ
ልኩ ፡ ተዐግሦተ ፡ ሶበ ፡ እሬኢ ፡ እንዘ ፡
ይወርዱ ፡ ዲበ ፡ ዝኩ ፡ ዘርኢኩ ፤
ወዳየሁት ፡ ወደዚህ ፡ ገሃነም ፡
ሲወርዱ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ መታ
ገሱን ፡ አልቻልኩምና ፡ እንባዬ
አልተገታም ፤

፴፬ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ይመጽእ
ወይትፌጸም ፤
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ያየሁት ፡ የነፍስ
መከራ ፡ ይመጣልና ፤ ይፈጸ
ማልና ፡ አለቀስሁ ፤
ወኵሉ ፡ በበክፍሉ ፡ ምግባረ ፡ ሰብእ ፡
ተርእየ ፡ ሊተ ፤
የሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ በየክፍሉ ፤
በየክፍሉ ፡ በየወገን ፡ በየወገኑ ፡
ታይቶኛልና ፤

፴፭ ፤ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ተዘከርክዎ ፡
ለሕልምየ ፡ ቀዳማዊ ፤
የእነርሱን ፡ መከራ ፡ ባየሁበት ፡
ሌሊት ፡ ቀድሞ ፡ ያየሁትን ፡ ማየ ፡
አይኅ ፡ አስቤ ፡ ስለእነርሱ ፡ አለቀ
ስሁ ፤
ወበእንቲአሁ ፡ በከይኩ ፡ ወተሐወኩ ፤
ይህንን ፡ ራእይ ፡ አይቻለሁና ፡ ስለ
ዚህ ፡ ነገር ፡ አለቀስሁ ፡ ታወክሁ ፤
እስመ ፡ ርኢኩ ፡ ውእተ ፡ ራዕየ ፤
ይህንን ፡ ራእይ ፡ አይቻለሁና ፤

፴፮ ፤ ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ማቱሳላ
ጸውዕ ፡ ሊተ ፡ ኵሎሙ ፡ አኃዊከ ፤
አሁንም ፡ ልጄ ፡ ማቱሳላ ፡
ወንድሞችህን ፡ ሁሉ ፡ ጥራልኝ፤
ወአስተጋብእ ፡ ሊተ ፡ ኵሎ ፡ ደቂቀ ፡
እምከ ፤
የእናትህንም ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡
ሰብስብልኝ ፤
እስመ ፡ ቃል ፡ ይጼውዐኒ ፤
አስተምር ፡ የሚል ፡ ቃል ፡
ይጠራኛልና ፤

፴፯ ፤ ወመንፈስ ፡ ተክዕወ ፡ በላዕ
ሌየ ፤
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተሠጥቶኛል ፤
ዕውቀት ፡ በዝቶ ፡ ተገልጾልኛልና ፤
ከመ ፡ አርኢክሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘይበ
ጽሐክሙ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፤
እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ገልጬ ፡ አስተ
ምራችሁ ፡ ዘንድ ፡ እውቀቱ ፡ በእኔ፡
ላይ ፡ በዝቶ ፡ ተሰጠኝ ፤

፴፰ ፤ ወእምኔሁ ፡ ሖረ ፡ ማቱሳላ ፤
እምኔየ ፡ ሖረ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ከእኔ ፡ ተለይቶ ፡ ማቱሳላ ፡ ሄደ ፤
ወጸውዖሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አኃዊሁ ፡
ኀቤሁ ፡ ወአስተጋብኦሙ ፡ ለአዝማደ ፡
ዚአሁ ፤
ወንድሞቹን ፡ ሁሉ ፡ ወደእርሱ ፡
ጠራቸው ፤ ዘመዶቹንም ፡ ሁሉ
ወደእርሱ ፡ ሰበሰባቸው ፤

፲ ፤ ወይእዜኒ ፡ ስምዑኒ ፡ ደቂቅየ ፡
ወሑሩ ፡ በፍናዊተ ፡ ጽድቅ ፣
አሁንም ፡ ልጆቼ ፡ ስሙኝ ፡ በበጎ ፡
ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፤

፲፩ ፤ ወኢትሑሩ ፡ በፍናዊተ .
ግፍዕ ፣
በግፍ ፡ ሥራዎች ፡ ጸንታችሁ ፡
አትኑሩ ፡ እላችኋለሁ ፤
እስመ ፡ ይትኀጐሉ ፡ ለዓለም ፡
ኵሎሙ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በፍኖተ ፡
ዓመፃ ፣
በግፍ ፡ ሥራ ፡ ጸንተው ፡ የሚ
ኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ይጠፋሉና ፤

፲፪ ፤ ዘተጽሕፈ ፡ እምሄኖክ ፡ ጸሐፈ ፡
ዝ ፡ ኵሉ ፡ ትምህርተ ፡ ጥበብ ፡ እም
ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ስቡሕ ፡ ወመኰንነ ፡
ኵሉ ፡ ምድር ፤
የዓለም ፡ ሁሉ ፡ መምህር ፡
የምሆን ፣ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ክቡር
ከምሆን ፡ ከእኔ ፡ ከሄኖክ ፡ የተ
ጻፈ ፤ አንድም ፡ የዓለም ፡ ሁሉ
መምህር ፡ ከሚሆን ፡ ከዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ ክቡር ፡ ከሚሆን ፡ ከጌታ
ተገልጾልኝ ፣ ከእኔ ፡ ከጸሐፊ ፡
ሄኖክ ፡ ተጻፈ፣ ይህ ፡ ሁሉ ፡
የጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፤ ይህ ፡
ሁሉ ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡
ከጸሐፊ ፡ ከእኔ ፡ ከሄኖክ ፡ የተገኘ ፤
አንድም ፡ ከጸሐፊ ፡ ከእኔ ፡ ከሄኖክ ፡
የተገኘ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የጥበብ ፡
ትምህርት ፡ ነው ፤

፲፫ ፤ ለኵሎሙ ፡ ውሉድየ ፡ እለ ፡
የኀድሩ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወለት
ውልድ ፡ ደኃራውያን ፡ እለ ፡ ይገብሩ
ርትዐ ፡ ወሰላመ ፤
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለል
ጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ፍቅርንና ፡ የቀና ፡
ነገርን ፡ ለሚሠሩ ፡ ኋላም ፡ ለሚ
ወለዱ ፡ ለልጆቼ ፡ ሁሉ ፡ ትድ
ረስ ፤

፲፬ ፤ ኢትኀዝን ፡ መንፈስክሙ ፡ በአ
ዝማን ፡ እስመ ፡ መዋዕለ ፡ ወሀበ
ቅዱስ ፡ ወዓቢይ ፡ ለኵሉ ፣
ክቡር ፡ ገናና ፡ የሚሆን ፡ ንጹሕ
ጌታ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አዝማነ
ንስሓን ፡ ሰጥቷልና ፣ ኃጢአት ፡
ሠርታችሁ ፡ ገሃነም ፡ ወርዳችሁ ፡
በአዝማኑ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡
ነፍሳችሁ፡ እንዳታዝን ፡ ትሁን ፤

፲፭ ፤ ወይትነሣእ ፡ ጻድቅ ፡ እምን
ዋም ፣
ጻድቅ ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ ከን
ዋመ ፡ ኃጢአት ፡ ይነሣል ፣
ይትነሣእ ፡ ወየኀልፍ ፡ በፍኖተ ፡
ጽድቅ ፣
በእውነት ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖ
ራል ፤

ወባቲ ፡ ይዘረዉ ፡ ኵሉ ፡ ዘመደ ፡ ሥርው ፡ ኅሩይ ፤
የተመረጠ ፡ የመንግሥት ፡ ወገን፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡ ይበተናል ፤ ጎቶልያ ፡ አስፈጅታቸዋለችና ፤
፴ ፤ ወእምድኅሬዝ ፡ በሳብዕ ፡ ሰንበት ፡ ትትነሣእ ፡ ትውልድ ፡ ዕሉት ፤
ከዚህ ፡ ከ፮ተኛው ፡ ሱባዔ ፡ በኋላ ፡ በ፯ኛው ፡ ሱባዔ ፡ አሉተኛ ፤ ወን ጀለኛ ፡ ትውልድ ፡ ትነሣለች ፤
ወብዙኅ ፡ ምግባራቲሃ ፤
ሥራዋ ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፤
ወኵሉ ፡ ምግባራቲሃ ፡ ዕልወት ፤
ሥራዋ ፡ ብዙ ፡ ውንጀላ ፡ የሆነ ሥራዋ፡ ሁሉ ፡ ወንጀል ፡የሆነ ፤ ኢዮስያስ ፡ ብሎ ፡ ቁሟል ፤ አሜ ስያስ ፤ አዝያን ፤ ኢዮአታም ፤ አካዝ ፤ ሕዝቅያስ ፤ ምናሴ ፤ አሞጽ ፤ ከመጀመርያው ፡ ሱባዔ፡ ገጠመ ፤ አሞፅ ፡ ኢዮስያስን ፡ ይወልዳል ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወእ ምድኅሬዝ ፡ ትከውን ፡ ካልእት ፡ ሰንበት ፡ ሳምኒት ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበር ፤
፴፩ ፤ ወበተፍጻሚታ ፡ ይትኀረዩ ፡ ኅሩያን ፡ ጻድቃን ፡ እምተክለ ፡ ጽድቅ ዘለዓለም ፤
ዘለዓለም ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፤ ሕግ ፡ ከመጠበቃቸው ፡የተነሣ ፡ ደናግል ፡ ሕጋውያን ፡ በ፯ኛይቱ ሱባዔ፡በመጨረሻዋ፡ይመረጣሉ፤

እለ ፡ ይትወሀብ ፡ሎሙ ፡ ፯ቱ፡ ምክዕቢታተ ፡ ትምህርት ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረተ ፡ ዚአሁ ፤
ፍጥረቱን ፡ ሁሉ ፡ ለማስተማር ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ትምህርት ፡ የሚ ሰጣቸው ፡ ብሎ ፡ ለደናግል ፡ ለሕ ጋውያን ፡ ቀጸለ፤
፴፪ ፤ እስመ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ እም ኵሉ ፡ ውሉደ ፡ ሰብእ ፡ ዘይክል ሰሚዐ ፡ ቃሉ ፡ ለቅዱስ ፤
የንጹሕ ፡የክቡር ፡የእግዚአብሔር፡ ቃሉን ፡ መስማት ፡ የሚችል ፡ ማነው ? ማነውና ፡ እርሱ ፡ ካልገ ለጸለት ፡ ማለት ፡ ነው ፤
ወኢይትሀወክ ፤
የመጻሕፍትንስ ፡ ቃል ፡ ሰምቶ የማይታወክ ፡ማነው ? ማነውና ፤
ወመኑ ፡ ዘይክል ፡ ከመ ፡ የሐሊ ፡ ሕሊናሁ ፤
አሳቡን ፡ ያስብ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ማነው ? ማነውና፤
፴፫ ፤ ወመኑ ፡ ዘይክል ፡ ነጽሮቶ ፡ ለሰማይ ፡ ወኵሉ ፡ ምግባራቲሃ ፤
ሰማይን ፡ ሥራዋንም ፡ ሁሉ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ የሚችል ፡ ማነው?
፴፬ ፤ ወምንት ፡ ውእቱ ፡ ዘይክል ፡ አእምሮ ፡ ግብረ ፡ ሰማይ ፤
በሰማይ ፡ ያለውን ፡ ፍጥረት ፡ ማወቅ ፡ የሚችል ፡ ማነው ? ማነውና ፤

ወትእኅዙ ፡ በሕሊና ፡ ልብክሙ ።
እኔ ፡ የነገርኋችሁን ፡ ከሰማችሁ ፡ በልቡናችሁ ። ዕውቀት ፡ ትይዛላችሁ ። ተእኀዙ ፡ ቢል ፡ ዕውቀትን ፡ ትይዙ ፡ ዘንድ ፤
ሑሩ ፡ በፍኖተ ፡ ሰላም ። ከመ ፡ ትሕየዉ ፤
ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ጸንታችሁ ፡ ኑሩ ፤
፩ ፤ ወኢይደምሰስ ፡ ነገርየ ፡ እምል ብክሙ ፤
ነገሬ ፡ ከልቦናችሁ ፡ አይጥፋ ።
እስመ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ ያሜክር ምሙ ፡ ኃጥአን ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ጥበበ ፡ እኩየ ።
ክፉ ፡ ጥበብን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ደጋጎች ፡ ሰዎችን ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ እንዲፈትኗዋቸው ፡ አው ቃለሁና ።
ወኵሉ ፡ መካን ፡ ኢይትረከብ ፡ ላቲ ።
ለኃጢአት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ አይገ ኝላትም ፤
ወኵሉ ፡ መከራ ፡ ኢየሐፅፅ ።
መከራ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሷ ፡ አይር ቅም ፤
፪ ፤ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ የሐንጽዋ ፡ ለዓመፃ ፡ ወለግፍዕ ፡ ወይሣርርዋ ፡ ለጕሕሉት ፤
ሐሰት ፡ ነገርን ። ግፍንም ፡ ተን ኰልንም ፡ አጥንተው ፡ ለሚሠ ሯት ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ፤
እስመ ፡ ፍጡነ ፡ ይትነሠቱ ፡ ወአል ቦሙ ፡ ሰላም ።
እነርሱ ፡ ፈጥነው ፡ ይጠፋሉና ፤
ፍቅር ፡ አንድነትም ፡ የላቸውምና ፤
፫ ፤ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ የሐንጹ አብያቲሆሙ ፡ በኃጢአት ።
የድሀ ፡ ከብት ፡ ቀምተው ፤ እን ድም ፡ ደመወዝ ፡ ቀምተው ። ቤታ ቸውን ፡ ለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላ ቸው ፤
እስመ ፡ እምኵሉ ፡ መሠረቶሙ ፡ ይትነሠቱ ፤
ከሥር ፡ መሠረታቸው ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉና ፤
ወበሰይፍ ፡ ይወድቁ ።
በሰይፍም ፡ ተቀራድደው ፡ ያል ቃሉና ።
ወእለ ፡ ያጠርይዋ ፡ ለወርቅ ፡ ወለብ ሩር ፡ በኵነኔ ፡ ፍጡነ ፡ ይትኀጐሉ ።
ወርቅን ፡ ብርን ፡ የሚሰበስቧት ፡ ሰዎች ፡ በፍርዱ ፡ ፈጥነው ፡ ይጠ ፋሉና ፤
፬ ፤ አሌ ፡ ለክሙ ፡ አብዕልት ።
እናንተ ፡ ባለጸጎች ፡ ወዮላችሁ ፤
እስመ ፡ ዲበ ፡ ብዕልክሙ ፡ ተወከ ልክሙ ፤
በባለጸግነታችሁ ፡ ላይ ፡ ታምና ችኋልና ።
ወእምነ ፡ ብዕልክሙ ፡ ትወጽኡ ።
ከባለጸግነታችሁም ፡ ትለያላችሁና ፡
እናንተ ፡ ባለጸጎች ፡ ወዮላችሁ ፤

እስመ ፡ ብዙኃ ፡ ትሬእዩ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፧
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ታያላችሁና ፧
፲፪ ፧ እስመ ፡ ስነ ፡ ትወድዩ ፡ ላዕሌክሙ ፡ እንትሙ ፡ ዕደው ፡ ፈድፋደ እምአንስት ፧
እናንተ ፡ ወንዶች ፡ ከሴቶች ፡ ይልቅ ፡ ጌጥ ፡ ታጌጣላችሁ ፤
ስለሆነም ፡ ብዙ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ታደርጋላችሁና ፧
ወኅብረ ፡ ፈድፋደ ፡ እምድንግል ፡
በመንግል ፧ በጌጥ ፡ ሲል ፡ ነው ፧
ከድንግሊቱ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ በጌጥ ፡ ላይ ፡ ጌጥ ፡ ታጌጣለችሁና፧ አንድም ፡ በመንገለ ፡ አንስት ፡ ይላል ፤
በሴቶች ፡ ዘንድ ፡ አጊጣችሁ ፡ አምራችሁ ፡ ትታዩ ፡ ዘንድ ፡ ታጌጣላችሁና፧
፲፫ ፧ በመንግሥት ፧
በመንግሥት ፡ ያላችሁ ፡ ይመስ ላችኋልና ፧
ወበዕበይ ፡ ወበሥልጣን ፧
በገናንነት ፡ በሥልጣን ፡ ያላችሁ ይመስላችኋልና፧
ወበብሩር ፡ ወወርቅ ፡ ወሜላት ፡ ወክብር ፧
በወርቅና ፡ በብር ፡ በነጭ ፡ ሐርም ፡ የከበርን ፡ ይመስላች ኋልና ፧
፲፬ ፧ ወመባልዕት ፡ ከመ ፡ ማይ ይትከዓዉ ፤
መብሎችም ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ በዝ ተው ፡ በፊታችሁ ፡ ይቀርባሉ ፧
ወበእንተዝ ፡ ትምህርት ፡ ወጥበብ ፡ አልቦሙ ፧
ስለዚህም ፡ በዝተው ፡ ስለቀረቡ ፡ ትምህርት ፤ ጥበብ ፤ የላቸውም፧
፲፭ ፧ ወቦቱ ፡ ይትኀጉሉ ፡ ኅቡረ ፡ ምስለ ፡ ንዋያቲሆሙ ፡ ወምስለ ፡ ኵሉ ፡ ስብሐቶሙ ፡ ወክብሮሙ ፧
መባልዕት ፡ በዝተው ፡ ስለቀረቡ ፤ ጥበብ ፤ ትምህርት ፡ ስለሌላቸው፡ ከገንዘባቸው ፡ ከክብራቸውና ፡ ከጌትነታቸው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ይጠፋሉ ፧
፲፮ ፧ ወበጽእለት ፡ ወበንዴት፧
በጽዕለተ ፡ ነፍስ ፡ (በስድብ) ፡ በንዴተ ፡ ነፍስ ፡ ሊሆኑ ፧
ወበቀትለ ፡ ነፍስ ፧
በቀትለ ፡ ነፍስ ፡ ወበቀል ፡ ቢል ፤
በጽኑ ፡ በቀልም ፡ ሆነው ፡ ሊኖሩ ፧
ወበንዴት ፡ ዓቢይ ፧
በፍጹም ፡ ንዴተ ፡ ነፍስ ፡ ሊኖሩ፤

ትትወደይ ፡ መንፈሶሙ ፡ ውስተ ፡ እቶነ ፡ እሳት ፤
ነፍሳቸው ፡ በገሃነም ፡ ትወድ ቃለች ፤

፲፯ ፤ መሐልኩ ፡ ለክሙ ፡ ኃጥአን ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፤ ተራራ ፡ በባሕርዩ ፡ ተገኝቶ ፡ እንዳልነበረ ፤ ወኢይከውን ፤ እን ግዲህም ፡ መገዛት ፡ እንደሌለ በት ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋለሁ ፤
ወኢወግር ፡ ለብእሲት ፡ አመተ ፤
ኮረብታም፡ ለሴት ፡ ተገኝቶ ፡ እን ዳይደለች ፡ ምዬ ፡ እነግራችኋ ለሁ ፤

፲፰ ፤ ከመዝ ፡ ኃጢአትኒ ፡ ኢተፈ ነወት ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ተራራ ፡ ኮረብታ ፡ በባሕርያ ቸው ፡ መገዛት ፡ እንደሌለባቸው፡ ኃጢአትም ፡ የባሕርይ ፡ ሁና ፡ አልተፈጠረችም ፤
አላ ፡ሰብእ ፡ እምርእሶሙ ፡ ፈጠርዋ፤
አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ከልቦናቸው፡ አንቅተው ፡ ሠሯት ፡ እንጂ ፤
ወለመርገም ፡ ዓቢይ ፡ ይከውኑ ፡ እለ ገብርዋ ፤
አዳምና ፡ ሔዋንም ፡ ለፍጹም ፡ ጥፋት ፡ ይሆናሉ ፤ አንድም ፡ ኢኮነ ፡ ደብር ፡ ገብረ ፤ ዓበይት ፡ ነቢያት ፡ አሪትን ፤ ነዋሪት ፤ ቀዋሚት፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ እንዳላስተማሩ ፤
ወኢወግር ፤ ለብእሲት ፡ አመተ፤
ደቂቅ ፡ ነቢያትም ፡ አምሳል ፡ መርገፍ፡ የምትሆን ፡ አሪትን ፡ ነዋሪት ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ እንዳላስተማሩ ፡ ምዬ ፡ እነግራ ችኋለሁ ፤ ከመዝ ፡ ኃጢአት ፡ ኢተፈነወት ፡ አሁን ፡ እንደተ ናገርሁት ፡ ኃጢአትም ፡ ነዋሪት ሕግ ፡ ሁና ፡ አልተሠራችም ፤
አላ ፡ ሰብእ ፡ እምርእሶሙ ፡ ፈጠርዋ ፤ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ልብ ወለድ ፡ አንቅተው ፡ ቀዋሚት ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ብለው ፡ አስተማሯት ፡ እንጂ ፡
ወለመርገም ፡ ዓቢይ ፡ ይከውኑ ፤
ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ለጽኑ ፡ መር ገም ፡ ይሆናሉ፤ (ሑሩ ፡ እምኔየ ፡ ይባላሉ ፤)

፲፱ ፤ ወምክንት ፡ ለብእሲት ፡ ኢተ ውህባ ፤
ለሴት፡ ምክንት፡ አልተሰጣትም፤
አላ ፡ በግብረ ፡ እዴሃ ፡ትመውት ፡ ዘእንበለ ፡ ውሉድ ፤

በእጇ ፡ ይዛ ፤ በቃሏ ፡ ተናግራ ፤ በሠራችው ፡ ኃጢአት ፡ ያለልጅ ትሞታለች ፡ እንጂ ፤ ኢሳይያስ፡ አነ ፡ እግዚአብሔር ፡ዘእፈጥር፡ መካነ ፡ ወአወልድ ፡አለ ፤ከዚህ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ አይጣላም? ቢሉ ፡ አይጣላም ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሄኖክ ፡ ነው ፤ ምክንት ፡ በደዌ ፡ በኃጢአት ፡ ነው ፤ አኑ ፡ ዘእፈጥር ፡ መካነ ፡ አለሳ ፡ ቢሉ ፡ እስከት ወልድ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፤ አነ ፡ ዘእፈጥር ፡ መካነ፡ አለ ፤ አንድም፡ አዝኖ፡ ተከዞ ፡ የወለዱት ፡ ልጅ፡ ይጠቅማልና ፡ እስኪወልዱ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ዘእፈጥር ፡ መካነ ፡ አለ ፤ አንድም ፡ መጻእ ያትን ፡ አለማወቅ ፡ ለነፍስ ፡ አልተሰጣትም ፤ አላ ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ እደዊሃ ፤ በኃጢአቷ ፡ ምክንያት ፡ መጻእያትን ፡ ሳትና ገር ፡ ትሞታለች ፡ እንጂ ፤

፮ ፤ መሐልኩ ፡ ለክሙ ፡ ኃጥአን ፡ በቅዱስ ፡ ወዓቢይ ፤ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግብርክሙ ፡ እኩይ ፡ ክሡት ፡ ውእቱ ፡ በሰማያት ፤

ኃጥአን፡ ክፉ ፡ ሥራችሁ ፡ ሁሉ ፡ በሰማይ ፡ የተገለጸ ፡ እንደሆነ ፤

ወአልብክሙ ፡ ግብረ ፡ ግፍዕ ፡ ክዱን፡ ወኢኅቡዕ ፤

የተሠወረ ፡ የግፍ ፡ ሥራም ፡ እንደሌላችሁ ፡ በገናና ፡ በክበረ ስሙ ፡ ምዬ ፡ ነገርኋችሁ ፤

፯ ፤ ወኢታምስሉ ፡ በመንፈስክሙ ፤

በልቡናችሁ ፡ የሚሰወር አታስ መስሉት ፤

ወኢትበሉ ፡ በልብክሙ ፡

በልቡናችሁ ፡ ይሰወርልናል ፡ አትበሉ ፤

እስመ ፡ ኢተአምሩ ፡ ወኢትሬእዩ ፡ ኵሎ ፡ ኃጢአተክሙ ፡ ዘበሰማይ ፡ ይጸሐፍ ፡ ሀሎ ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ በቅድሜሁ ፡ ለልዑል ፤

በሰማይ ፡ በጌታ ፡ ፊት ፡ ይጻፍ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ አታዩም ፤ አታውቁምና ፤

፰ ፤ ወእምይእዜ ፡ ተአምሩ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግፍዕክሙ ፡ ዘት ገፍዑ ፡ ይጸሐፍ ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ኵነኔክሙ ፤

ፍርድ ፡ እስከሚፈረድባት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ የበደላችሁት ፡ በደል ፡ በየቀኑ ሁሉ ፡ እንዲጻፍባችሁ ፡ ታውቃ ላችሁ ፤

፱ ፤ አሌ ፡ ለክሙ ፡ አብዳን ፡ እስመ ፡ ትትኃጉሉ ፡ በዕበድክሙ ፤

የማይገታ ፡ የማይፈጸም ፡ ደም ለሚፈስስበት ፡ ቀን ፡ ኃጢአት ፡ ተዘጋጅቷልና ፡ ለእናንተ ፡ ለኃጥአን ፡ ጻግመኛ ፡ እምልላችኋለሁ ፤ እነግራችኋለሁ ፤

፰ ፤ ወይሰግዱ ፡ ለዕብን ፤
ወለእለ ፡ ይሰግዱ ፡ ሲል ፡ ነው ፣
ለደንጊያ ፡ ለሚሰግዱ ፡ ሰዎች ፤
ወእለ ፡ ይገልፉ ፤
ወለእለ ፡ ይገልፉ ፡ ሲል ፡ ነው ፣
ለጣዖት ፡ ለሚሰግዱ ፤ ጣዖት ፡ ለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፤
ምስለ ፡ ዘወርቅ ፡ ወዘብሩር ፤
የወርቅ ፡ የብር ፡ ምስል ፡ ለሚሠሩ ፤
ወዘዕፅ ፡ ወዘልሕኵት ፤
ከእንጨትና ፡ ከሸክላ ፡ ተቀርጾ ለሚሠራ ፡ ምስል ፤
፱ ፤ ወእለ ፡ ይሰግዱ ፡ ለነፍሳት ፡ ርኩሳን ፤
ለረከሱ ፡ ለረቂቃን ፡ለግዙፋን ፤
ወለአኩያን ፡ አጋንንት ፤
ለክፉዎችም ፡ አጋንንት ፡ ለረቂቃን ፤ አንድም ፡ ለነፍሳት ፡ ለርኩሳን ፡ ሰዎች ፤ ወለአጋንንት ፡ በቁሙ ፡ ለአጋንንት ፡ ለሚሰግዱ ሰዎች ፤
ወለኵሉ ፡ ጣዖት ፡ ወለምሕራማት ፤
ለጣዖቱም ፡ ለመስገጃው ፡ ሁሉ ፡ ይሰግዳሉ ፤
፲ ፤ ወኵሉ ፡ ረድኤት ፡ ኢይትረከብ ፡ እምኔሆሙ ፤
እምኔሆሙ ፡ ለጣዖታት ፡ ነው ፣
ከእነርሳቸውም ፡ ከጣዖታት ፡ ረድኤት ፡ ሁሉ ፡ አይገኝም ፤
ወይትረስዑ፡ በእንተ ፡ ዕበደ ፡ ልቦሙ፤
ከልቦናቸውም ፡ ድንቁርና፡ የተነሣ ፡ ከሥላሴ ፡ ልቡና ፡ ይዘነጋሉ ፤
ወይጼለላ ፡ አዕይንቲሆሙ ፡ በፍርሀተ ልቦሙ ፣
በልቦናቸው ፡ ፍርሀት ፡ የልቡናቸው ፡ ዓይኖች ፡ በድንቁርና ፡ ይያዛሉ ፤
፲፩ ፤ ወበርእየ ፡ አሕላሞሙ ፡ በሙ ይረስዑ ፤
የሐሰት ፡ ሕልም ፡ አለምን ፣ አለ ምን ፡ በማለታቸው ፡ ሕገ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ ይዘነጋሉ ፤
ወይፈርሁ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግብሮሙ ፡ በሐሰት ፡ ገብሩ ፤
ሥራቸውን ፡ ሁሉ ፡ በሐሰት ፡ ሠርተዋልና ፡ ይፈራሉ ፣
ወሰገዱ ፡ ለዕብን ፡ ወይትነሥቱ ፡ በምዕር ፤
ለደንጊያውም ፡ ሰግደዋልና ፡ ፈጥነው ፡ ይጠፋሉ ፤

ወኢይሔልዩ ፡ ዲበ ፡ ኃጢአትክሙ ፤
በኃጢአታችሁ ፡ ምክንያት ፡ ይወ ርዱ ፡ ዘንድ ፡ አያስቡምና ፤
፻፫ ፤ ወይእዜኒ ፡ ሀቡ ፡ አምኃ ለዝናም ፡ ከመ ፡ ኢይትከላእ ፡ ወሪደ ዲቤክሙ ፤
አሁንም ፡ ዝናም ፡ ወደ ፡ እና ንተ ፡ መውረዱን ፡ እንዳይከለ ከል ፤
ወጠል ፤
ጠልም ፡ ከእናንተ ፡ መውረድን እንዳይከለከል ፤
እመ ፡ ተመጠወ ፡ እምኔክሙ ፡ ወርቀ ፤ ወብሩረ ፤ ከመ ፡ ይረድ ፤
ከእናንተ ፡ ብርንና ፡ ወርቅን ፡ ተቀብሎ ፡ ይወርድ ፡ እንደሆነ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ስጡ ፤
፻፲ ፤ ወሶበ ፡ ይወድቅ ፡ እምኔክሙ ፡ አስሐትያ ፤ ወሐመዳ ፤ ወቍረ ፡ ዚአ ሆሙ ፤
ውርጭ ፤ ዋግ ፡ በእናንተ ፡ ቢወ ድቁባችሁ ፡ የእነርሱም ፡ ቅዝቃዜ ፡ ቢደረግባችሁ ፤
ወኵሉ ነፋሳተ ፡ ሐመዳ ፤
ዋግን ፡ የሚያመጡ ፡ ነፋሳትም ፡ ሁሉ ፤
ወኵሎ ፡ ፃዕራተ ፡ ዚአሆሙ ፡
እሊህ ፡ የሚያመጡት ፡ ጭንቀ ትም ፡ ቢያገኛችሁ ፤
በእማንቱ ፡ መዋዕል ፡ ኢትክሉ ፡ ቀዊመ ፡ ቅድሜሆሙ ፤
በእነዚያ ፡ ወራት ፡ በእነርሱ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይቻላችሁም ፡፡

## ምዕራፍ ፻፬

### ጉባኤ ፤

፩ ፤ ጠይቅዋ ፡ ለሰማይ ፡ ኵልክሙ ውሉደ ፡ ሰማይ ፤ ወኵሎ ፡ ግብሮ ፡ ለልዑል ፤
በሰማያዊ ፡ ግብር ፡ የምትኖሩ ፤ ሰማያዊ፡ ሕግን ፡ የምትጠብቁ ፤ ሰማይን ፡ መርምሯት ፤ ተረዷት ፤
እንድም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማ ያት፡ የምትኖሩ ፡ ተረዷት ፤ እን ድም ፡ ውሉድ ፡ ሰማያውያን ፡ ይላል ፤ ሰማያውያን ፡ ውሉድ ፡ ሰማያዊ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቡ ፤
ደግ ፡ መጽሐፍ ፡ የሆነ ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በጀመረበት ፡ ይጨርሳል ፤
ወፍርሁ ፡ እምኔሁ ፤ ወኢትግበሩ ፡ እኩየ ፡ በቅድሜሁ ፤
በፊቱ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ እንዳ ትሠሩ ፡ ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ ፍሩ ፤
፪ ፤ እመ ፡ ዐጸወ ፡ መስኮተ ፡ ሰማይ፡ ወከልአ ፡ ዝናመ ፤ ወጠለ ፤ ከመ ፡ ኢይረድ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በእንቲ አክሙ ፤
ሰማይ ፡ መስኮቱን ፡ ቢዘጋ ፤
እንድም ፡ መስኮተ ፡ ሰማይ ፡ ቢል ፡ ጌታ ፡ የሰማይን ፡ መስኮት ፡

፲፫ ፡ ወሶበ ፡ ይወጺ ፡ ቃሉ ፡ ዲቤ
ከሙ ፡
የመዓቱን ፡ ቃል ፡ ወደእናንተ ፡
ባመጣው ፡ ጊዜ ፡
አኮኑ ፡ ትትማህከው ፡ ወትፈርሁ ፡ ትደ
ነግፁ ፡
ትወድቁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ የምት
ፈሩ ፡ የምትደነግጡ ፡ የምትወ
ድቁ ፡ አይደለምን ?
ወኵሉሙ ፡ ብርሃናት ፡ ይትማህ
ከዉ ፡ ወይትሀወኩ ፡ በፍርሀት ፡
ዓቢይ ፡
ብርሃኖችስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ ፡
ፍርሀት ፡ ተይዘው ፡ የሚፈሩ ፡
የሚደነግጡ ፡ አይደለምን ፡
፲፬ ፡ ወኵላ ፡ ምድር ፡ ትትማህከው ፡
በፍርሀት ፡ ዓቢይ ፡
ትፈርህ ፡ ትደነግፅ ፡ ሲል ፡
ነው ፡ ምድርስ ፡ ሁሉ ፡ በጽኑ
ፍርሀት ፡ ተይዛ ፡ የምትን
ቀጠቀጥ ፡ አይደለምን፤
ወትርዕድ ፡
ለጎልፈት ፡ ትቀርባለች ፡
ወትጌጉዕ ፡
ለጎልፈት ፡ ትቸኩላለች ፡
፲፭ ፡ ወኵሉሙ ፡ መላእክት ፡ ይፌ
ጽሙ ፡ ትእዛዞሙ ፡
መላእክትም ፡ ሁሉ ፡ የታዘዙ
ትን ፡ ይፈጽማሉ ፡

ወይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይትኀብኡ ፡
እምቅድመ ፡ ዓቢየ ፡ ስብሐት ፡
ከክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታ ፡ ፊት
ሊሰወሩ ፡ ይወዳሉ ፡
፲፮ ፡ ወይርዕዱ ፡ ደቂቀ ፡ ምድር ፡
ወይትሀወኩ ፡
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ ሰዎችም ፡
ይርዳሉ ፡ (ይንቀጠቀጣሉ) ፡ ይታ
ወካሉ ፡
ወአንትሙ ፡ ኃጥአን ፡ ርጉማን ፡ ለዓ
ለም ፡
እናንተ ፡ ኃጥአን ፡ ግን ፡ ለዘለዓ
ለሙ ፡ የተረገማችሁ ፡ ናችሁ ፡
ወአልብከሙ ፡ ሰላም ፡
ፍቅር ፡ አንድነትም፡ የላችሁም ፡
፲፯ ፡ ኢትፍርሁ ፡ አንትሙ ፡ ነፍ
ሳተ ፡ ጻድቃን ፡
እናንተ ፡ የጻድቃን ፡ ሰውነቶች
አትፍሩ ፡
ወተሰፈዉ ፡ እለ ፡ ሞትከሙ ፡ በጽ
ድቅ ፡
በእውነት ፡ ነገርም ፡ የሞታችሁ
ሰዎች ፡ ዋጋችሁን ፡ እንድታገኙ
ተስፋ ፡ አድርጉ ፡
፲፰ ፡ ወኢትኅዝኑ ፡ እስመ ፡ ወረደት ፡
ነፍስከሙ ፡ ውስተ ፡ ዓቢይ፡ ምን
ዳቤ ፡
ሰውነታችሁ ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡
ሳለች ፡

ወራት ፡ ለእናንተ ፡ ድካምን ፡
ደከምን፡ አትበሏቸው ፤ አንድም ፡
ዕጣን ፡ በምንወግርበት ፣ ዝክር፡
በምንዘክርበት ፡ ወራት ፡ ደከምን ፡
አትበሏቸው ፤

፲፫ ፤ ወኵሎ ፡ ሥራሐ ፡ ርኢነ፤
መከራውን ፡ ሁሉ ፡ አየን ፤
ወእኩያተ ፡ ብዙኃተ ፡ረከብነ ፤
ብዙ ፡ መከራዎችንም ፡ ተቀበ
ልን ፤
ወተወጻእነ ፡ ወውኅድነ ፤
ጨርሰን ፡ ጠፋን ፤
ወንእሰተ ፡ መንፈስነ ፡ ወተኀጕልነ ፤
ሰውነታችን ፡ እንስንስ ፡ አለች ፣
በዚህም፡ ጠፋን ፡ አትበሏቸው ፤

፲፬ ፤ ወአልቦ ፡ ዘረድአነ ፤
በነገር ፡ በጸሎት ፡ የረዳን ፡
የለም ፡ አትበሏቸው ፤
ወበምግባር ፡ ሰእነ ፤
በምናቀርበው ፡ ዕጣን ፣
በምንዘክረው ፡ ዝክር ፡ መዳን
ተሳነን ፡ አትበሏቸው ፤
ወኢምንተኒ ፡ ኢረከብነ ፤
በእነርሱም ፡ ሥራ ፡ ስንደክም ፡
ምንም ፡ ምን ፡ ተስፋ ፡ አላገኘ
ንም ፤
ወተጽዕርነ ፡ ወተኀጕልነ ፤
በመከራውም ፡ ተጨነቅን ፡ ጠፋን፡
አትበሏቸው ፤

፲፭ ፤ ወኢተሰፈውነ ፡ ከመ ፡ ንርአይ ፡
ሕይወተ ፡ ዕለተ ፡ እምዕለት ፤
ከዛሬ ፡ ነገ ፣ ከነገ ፡ ሣልስት ፣
ሕይወትን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡
ተስፋ ፡ አላደረግንም ፡ አት
በሏቸው ፤
ወተሰፈውነ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ርእሰ ፤
ገዥ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡
አደረግን ፤
ወኮነ ፡ ዘነበ ፤
ተገዥ ፡ ሆነ ፤
ፃመውነ ፡ እንዘ ፡ ንትጌበር ፤
ሥራውን ፡ ስንሠራ ፡ ደከምን ፤

፲፮ ፤ ወኢሠለጥነ፡ ዲበ ፡ ፃማነ፤
በገንዘባችን ፡ አልሠለጠንም ፤
ወኮነ ፡ መባልዕተ ፡ ለኃጥአን ፤
ለኃጥአንም ፡ መብሎችን፡ ሆንን ፣
ለነገሥታቱ፡ ለመኳንንቱ ፡ምግብ
ሆንን ፤
ወዓማፅያን ፡ አክበዱ ፡ ላዕሌነ ፡ አር
ዑተ ፡ ዚአሆሙ ፤
በደለኞች ፡ ሰዎችም ፡ በእኛ ፡
ላይ ፡ አገዛዛቸውን ፡ አጸኑብን ፤

፲፯ ፤ ወተሠልጡ ፡ ዲቤነ ፡ እለ ፡
ይጸልኡነ ፤ ወእለ ፡ ይደጕፅነ ፤
እኛን ፡ የሚጠሉን ፣ የሚወጉን ፡
ሰዎች ፡ በእኛ ፡ ሠለጠኑብን ፤

ወለእለ ፡ ይጸልእዎነ ፡ አትሐትነ ፡ ክሣደነ ፤
ለሚጠሉንም ፡ ለጠላቶቻችን ፡ አንገታችንን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደ ረግን ፤
ወኢመሐሩነ ፤
እነርሱ ፡ ግን ፡ አልራሩልንም ፡ አትበሏቸው ፤
፲፰ ፤ ወፈቀድነ ፡ ንሑር ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ንንፍጽ ፡ ወናዕርፍ ፤
ከእነርሱ ፡ ሸሽተን ፡ ከመከራው፡ ልናርፍ ፡ ወደድን፤
ወኢረከብነ ፡ ኀበ ፡ ንጕይይ ፡ ወንድ ኀን ፡ እምኔሆሙ ፤
ከነሱም ፡ ሸሽተን ፡ የምንድንበት ቦታ ፡ አላገኘንም፤
፲፱ ፤ ወሰከይናሆሙ ፡ ኀበ ፡ መላእ ክት ፡ በምንዳቤነ ፤
በመከራችን ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻ ችነን ፡ ከአለቆች ፡ ከሰስናቸው ፤
አንድም ፡ ከመላእክት ፡ ዘንድ ፡ ከሰስናቸው ፡
ወጸራሕነ ፡ ዲበ ፡ እለ ፡ ይበልዑነ ፤
ገንዘባችነን ፡ በሚበሉብን ፡ በጠ ላቶቻችን ፡ ወደ ፡ አለቆች ፡ ጮኽን ፤ አንድም ፡ ወደ ፡ መላእክት ፡ ጮኽን ፤ አንድም፡ ወሰከይናሆሙ ፡ ልመናችንን ፡ አድርሱልን ፡ ብለን ፡ ጻድቃንን፡ ወደ መላእክት ፡ አካሰስናቸው፤
ወጸራሕነ ፤ በሚበድሉን ፡ በጠላ ቶቻችን ፡ ጩኸታችንን ፡ ወደ ፡ መላእክት ፡ አድርሱልን ፡ ብለን፡ ለጻድቃን ፡ ጮኽነ ፤
ወጽራሐ ፡ ዚአነ ፡ ኢይርእዩ ወኢይ ፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይስምዑ ፡ ቃለነ ፤
ኢይሬእዩ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ልመና ችንን ፡ ጻድቃን ፡ መላእክት ፡ አይሰሙም ፤
፳ ፤ ወይረድዕዎሙ ፡ ለእለ ፡ የሀይ ዱነ ፡ ወይበልዑነ ፤
ለሚቀሙን ፡ ገንዘባችንንም ፡ የሚበሉብንን ፤
ወለእለ ፡ አውኀዱነ ፤
ያሳነሱንን ፤
ወየኀብኡ ፡ ግፍዖሙ ፤
ግፋቸውንም ፡ ይሰውሩላቸዋል እንጂ ፤
ወኢያወጽኡ ፡ እምኔነ ፡ አርዑቶሙ ፤
አገዛዛቸውን ፡ ከእኛ ፡ አያጠፉል ንም ፤
እለ ፡ ይበልዑነ ፤
ገንዘባችንን፡የሚበሉብንን፡ሰዎች፡ አገዛዛቸውን ፡ ከእኛ ፡ አያጠፉል ንም ፤

እስመ ፡ እምነ ፡ መላእክት ፡ ይትኀሠሥ ፡ ኵሉ ፡ ምንዳቤክሙ ፤
ወደ ፡ መላእክት ፡ ከመካሰሳችሁ የተነሣ ፤እንድም ፡ መላእክትን ፡ አድርሱልን ፡ ከማለታችሁ ፡ የተነሣ ፡ ከመላእክት ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ መከራችሁን ፡ ይመረምራሉ ፤
ወእምኵሎሙ ፡ እለ ፡ አርድዕምሙ ፡ ለእለ ፡ የኀይዱክሙ፤
የሚቀማችሁን ፡ ሠራዊቱን ፡ ከሚረዱ ፡ ከነገሥታቱ ፡ የተነሣ ፤ እንድም ፡ የሚቀማችሁ ፡ ነገሥታቱን ፡ ከሚረዱ ፡ ከሠራዊቱ ፡ የተነሣ፤
፳፮ ፤ ተሰፈዉ ፡ ወኢትኅድጉ ፡ ተስፋክሙ ፡ እስመ ፡ ትከውን ፡ ለክሙ ፡ ፍሥሓ ፡ ዓባይ ፡ ከመ ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፤
እንደ ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፡ ታደርጓት ፡ ዘንድ ፡ ያላችሁን ፡ ብዙ ፡ ደስታ፡ እንድታደርጉ ፡ ተስፋ፡ አድርጉ ፤ አለኝታችሁን ፡ አትተዉ ።
እንተ ፡ ሐለወክሙ ፡ ትግበሩ ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ ትትኀበኡ ፡ ሀለወክሙ ፡ በዕለተ ፡ ኵነኔ ፡ ዓባይ ፤
ጽኑ ፡ ፍርድ ፡ በሚደረግበት ፡ ቀን፡ ትሰወሩ ፡ ዘንድ ፡ ያላችሁ ፡ አይደለም ?

፳፯ ፤ ወኢትትረከቡ ፡ ከመ ፡ኃጥአን፤
እንደ ፡ ኃጥአንም ፡ ሁናችሁ ፡ አትገኙ ፤
ወኵነኔ ፡ እንተ ፡ ለዓለም ፡ ትከውን ፡ እምኔክሙ ፡ ለኵሉ ፡ ትውልደ ፡ ዓለም ፤
እናንተን ፡ ከመበደላቸው ፡ የተነሣ ፤ አንድም ፡ ከእናንተ ፡ ተለይተው ፡በኃጥአን ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ የምትኖር ፡ ፍርድ ፡ ትደረጋለች ፤ አንድም ፤ ወጽርሐ ፡ ዚአክሙ ፡ ኵነኔ ፡ ጽርሑ ፤
በኃጥአን ፡ መቻያ ፡ የሚሆን ፡ ጸሎታችሁን ፡ ጨኹ ፤ ወያስተርኢ ፡ ለክሙ ፤ በረድኤት ፡ ይገለጽላችኋል ፤
፳፰ ፤ ወይእዜኒ ፡ ኢትፍርሁ ፡ ጻድቃን፡ ሶበ ፡ ትሬእይዎሙ ፡ ለኃጥአን ፡ ይጸንዑ ፡ ወይዴለዉ ፡ በፍትወቶሙ ፤
ጻድቃን ፡ ኃጥአንን ፡ ጸንተው ፤ በፈቃዳቸው ፡ ተዘጋጅተው ፤ ባያችኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አትፍሩ ፤
፳፱ ፤ ወኢትኩኑ ፡ ሱቱፋነ ፡ ምስሌሆሙ ፡ አላ ፡ ረሐቁ ፡ እምግፍዐ ፡ ዚአሆሙ ፤
እነርሱ ፡ ከሚሠሩት ፡ ግፍ ፡ ራቁ ፡ እንጂ ፤ ከእነርሱ ፡ ጋራ፡ የተባበራችሁ ፡ አትሁኑ ፤

፲፱ ፤ ወይከውን ፡ መቅሠፍት ፡ ዓቢይ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ጽኑ ፡ መቅሠፍትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይደረጋል ፤
ወትትሐፀብ ፡ ምድር ፡ እምኵሉ ፡ ሙስና ፤
ምድርም ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ትነጻለች ፤
፳ ፤ ወይእዜኒ ፡ አይድዕ ፡ ለወልድከ ፡ ላሜህ ፤
አሁንም ፡ ለልጅህ ፡ ለላሜህ ፡ ንገረው ፤
እስመ ፡ ዘተወልደ ፡ ወልዱ ፡ ውእቱ፡ በጽድቅ ፤
ይህ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ በእውነት ፡ የእርሱ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ፡ ንገረው ፤
ወጸውዕ ፡ ስሞ ፡ ኖኅ ፡ እስመ፡ ውእቱ፡ ይከውን ፡ ለከሙ ፡ ተረፈ ፤
ኖኅ ፡ ማለት ፡ ተረፍ ፣ ትፍሥሕት ፣ ዕረፍት ፡ ማለት ፡ ነው፣ እርሱ ፡ ከጥፋት፡ የቀረ ፡ ይሆንላችኋልና ፡ ስሙንም ፡ ኖኅ ብለህ ፡ ጥራው ፤
ወውእቱ ፡ ወደቂቁ ፡ ይድኅኑ እሙስና ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ እምኵሉ ፡ ኃጢአት ፤
በእርሱ ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡ ትጨረስ ፡ ዘንድ ፡ ካላት ፡ በደል ፡ ሁሉና ፡ ከኃጢአትም ፡ ሁሉ ፡ የተነሣ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ከምትመጣ ፡ ጥፋት ፡ ልጆቹና ፡ እርሱ ፡ ይድናሉ ፤
ወእምኵሉ ፡ ዓመፃ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ትትፈጸም ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ በመዋዕሊሁ ፤
በእርሱ ፡ ዘመን ፡ ከምትመጣ ፡ ጥፋት ፡ ልጆቹና ፡ እርሱ ፡ ይድናሉ ፤
ወእምድኅረዝ ፡ ትከውን ፡ ዓመፃ ፡ ፈድፋደ ፡ እምእንተ ፡ ተፈጸመት ፡ ቀዳሚ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፤
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ከአለፈችው ፡ ኃጢአት ፡ ይልቅ ፡ ፈጽማ ፡ የምትበልጥ ፡ ግፍ ፡ ትደረጋለች ፤ ሰብአ ፡ ትካት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንውጋ ፡ አላሉም ፣ ሰብአ ፡ ሰናዖር ፡ ግን እግዚአብሔርን ፡ እንውጋ ፡ ብለዋልና ፤ አንድም ፡ ሰው ፡ እየበዛ ፡ ሲሄድ ፣ ኃጢአትም ፡ ይበዛልና ፤ አንድም ፡ ሰብአ ፡ ትካት፡ የጠፉት ፡ ሕግ ፡ ተሠርቶላቸው ፡ ከሕግ ፡ ወጥተው ፡ የበደሉ ፤ አብነት ፡ ባይኖራቸው ፡ ነው ፤ እሊህ ፡ ሰብአ ፡ ሰናዖር ፡ ግን ፡ሕግ ፡ ተሠርቶላቸው ፣ ከሕግ ፡ ወጥተው ፣ የጠፉት ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ አብነት ፤ እያሏቸው ፡ ነውና ፤

እስመ ፡ አአምር ፡ ምሥጢራተ ፡ ቅዱሳን ፤
እርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገልጦ ልኛልና ፤ ነግሮኛልና ፤
እስመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእ ፡ አርአየኒ፡ ወአይድዐኒ ፡ ወበጸፍጸፈ ፡ ሰማይ ፡ አንበብኩ ፡ ወለበውኩ ፤
እርሱ እግዚአብሔር አሳይቶ ኛልና ፤ ነግሮኛልና ፤ በሰማይ ፡ ሰሌዳነት ፡ የተጻፈውን ፡ አወቅሁ፤ አነበብሁ ፤
፹፩ ፤ ወርኢኩ ፡ ጽሑፈ ፡ በላዕ ሌሆሙ ፤
በእነርሱ ፡ የተጻፈውን ፡ አየሁ፤
እስመ ፡ ትውልድ ፡ እምትውልድ ፡ ትኤብስ ፤
ትውልድ ፡ ከትውልድ ፡ ይልቅ፡ አብልጣ ፡ ትበድላለችና ፤
እስከ፡ ትትነሣእ ፡ ትውልደ ፡ ጽድቅ፤
የጽድቅ ፡ ልጅ ፡ አብርሃም ፡ እስ ክትነሣ ፡ ድረስ ፡ የምትበድል ፡ ትውልድ፡ ትነሣለችና ፤ በእርሳ ቸው የተጻፈባቸውን ፡ አየሁ ፤
ወአበሳ ፡ ትትኀጐል ፤
በደል ፡ ትጠፋለች ፤
ወኃጢአት ፡ ትትገኀሥ ፡ እምዲበ ፡ ምድር ፤
ኃጢአትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሰው፡ ትርቃለች ፤ እንድም ፡ ትትለሐስ ፡ ይላል ፤ ትደመሰስ ፡ ትጠፍዕ ፡ ሲል ፡ ነው ፤
ወዙሉ ፡ ሠናይ ፡ ይመጽእ ፡ ዲቤሃ ፤
በጎውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእርሷ ፡ ይመጣል ፤
ወይእዜኒ ፡ ወልድየ ፡ ሑር ፡ ወአይድዖ ፡ ለወልድከ ፡ ላሜህ ፤
አሁንም ፡ ልጄ ፡ ሂደህ ፡ ለል ጅህ ፡ ለላሜህ ፡ ንገረው ፤
እስመ ፡ ዝ ፡ ወልድ ፡ ዘተወልደ ፡ ወልደ ፡ ዚአሁ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፤
ይህ ፡ የተወለደ ፡ ልጅ ፡ በእው ነት፡ የእርሱ ፡ ልጅ፡ ነውና ፤
ወኢኮነ ፡ ሐሰተ ፤
ሐሰትም ፡ አይደለምና ፤
ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ማሳቱላ ፡ ነገረ ፡ አቡሁ ፡ ሄኖክ ፤
ማቱሳላም ፡ የአባቱ ፡ የሄኖክን ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፤
እስመ ፡ በኅቡዕ ፡ አርአዮ ፡ ኵሎ ፡ ግብረ ፤
የተሠወረውን ፡ ምሥጢር ፡ ሁሉ ፡ አሳይቶታልና ፤
ወገብዐ ፡ ርእዮ ፤
ነገሩን ፡ ሰምቶ ፡ ተመለሰ፤
፹፪ ፤ ወሰመዮ ፡ ስሞ ፡ ለዝኩ ወልድ ፡ ኖኅ ፤
የዚህን ፡ ልጅ ፡ ስሙን ፡ ኖኅ ፡ አለው ፤

፲፮ ፤ ወየሐውሩ ፡ እሙንቱሂ ፡ በኀበ ተጽሕፈ ፡ ሎሙ ፡ መዋዕል ፡ ወአዝማን ፤
እነርሱም ፡ በተጻፈላቸው ፡ ዘመኖ ችና ፡ ቀኖች ፡ ጸንተው ፡ ይኖ ራሉ ፤ አንድም ፡ በኀበ ፡ ኢተ ጽሕፈ ፡ ሎሙ ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ቀን ፤ ይህንን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ኑራችሁ ፡ ትመጣላችሁ ፣ ተብሎ ፡ ወዳልተጻፈላቸው ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ገነት ፣ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፣ ጻድ ቃን ፡ ይሔዳሉ ።

ተፈጸመ ፡ ራእየ ፡ ሄኖክ ፡ ነቢይ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፤
ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስ ጋና ፡ ይግባውና ፡ ነቢዩ ፡ ሄኖክ ፡ ያየው ፡ ራእይ ፡ ተፈጸመ ።

ጉባዔ ፡ ሄኖክ ፡ ፴ ፡ ወ፩ዱ ፡ ዘጉለቄ ፣
ሄኖክ ፡ የቆጠረው ፡ ሠላሳ ፡ አንዱ ፡ ጉባኤ ፤

ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡
እነሣሥት ፡ ለአስጀመረን ፣ እተጋግት ፡ ለአስፈጸመን ፡
ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፤
አሜን ።